# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 4ኛ ክፍል

**አዘጋጆች**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ አየለ

**አርታኢዎች**

እሸቱ አጋ

አንበሴ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ**

ጆናታን ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ማውጫ ..... iii
መግቢያ ..... iv
ምዕራፍ አንድ ..... 1
የአካባቢ ጥበቃ ..... 1
ምዕራፍ ሁለት ..... 14
የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ..... 14
ምዕራፍ ሶስት ..... 27
መረዳዳት ..... 27
ምዕራፍ አራት ..... 40
ሥርዓተጸታ ..... 40
ምዕራፍ ስድስት ..... 67
ስፖርት ..... 67
ምዕራፍ ሰባት ..... 79
ውሃ ..... 79
ምዕራፍ ስምንት ..... 93
ድርድር ..... 93
ምዕራፍ ዘጠኝ ..... 106
የመገናኛ ብዙሃን ..... 106
ምዕራፍ አስር ..... 117
ንግድ ..... 117
አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ 4ኛ ክፍልመርሀትምህርት ..... 130
መግቢያ ..... 130

## መግቢያ

ይህ ለአራተኛ ክፍል ማስተማሪያነት የተዘጋጀው 'የመምህር መምሪያ' በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን አጠቃላይ የክፍል ውስጡን የመማር ማስተማር ሂደት እንዲመሩበት ታስቦ ነው። መምሪያው መነሻ ያደረገው አዲስ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርትና ለዚሁ ደረጃ ለተማሪዎች ተብሎ የተዘጋጀውን መማሪያ መፅሐፍነው።በመሆኑም ተማሪዎች እንዲሚሯው የተቀረፁትን ይዘቶች፣ ይዘቶቹን መሰረት አድርገውም የተሰናዱትን ተግባራትና መልመጃዎች አሳታፊ በሆነ መልኩ በመማሪያ ክፍል ውስጥና ከመማሪያ ክፍል ውጪ እየተገበሩ የትምህርቱን ግብ ማሳካት የሚቻልባቸውን ሁኔታዎችና አካሄዶችን በተመለከተ አጠቃላይነት ያለው ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መምሰል እንዳለበት፣ ምዘናው እንዴት ሊከናወንእንደሚችልና መሰረታዊ የቋንቋ ክህሎቱቹ እንዴት መቀናጀት እንዳለባቸው መነሻ ሀሳብ ይሰጣል። እነዚህን ጥቆማዎችና መነሻ ሀሳቦችም መምህራን የሚያገኟቸውን ሌሎች ግብዓቶች፣ጥሩ ተሞክሮዎች እና አዳዲስ አሰራሮችን እየቀመሩ በመጠቀም እያጎለበቷቸው የሚጠበቀውን ውጤት ተማሪዎቻቸው እንዲያሳኩ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይታመናል። ለዚህም መምህራን የየአካባቢያቸውን፣ የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መፅሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካትተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎች የሚሆኑ ምላሾችና ለየተግባራቱ አፈፃፀም የሚረዱ አማራጭ ሀሳቦች እንዲካተቱበት ሆኗል። እነዚህ አማራጭ ምላሾችና ሀሳቦች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየ ሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችና አካሄዶችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

**ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች**

- የየትኛውም ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነ (በተቀናጀ) መልኩ ያካተተ ይሆናል
- የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴን መርህ የተከተለ መሆን ይገባዋል
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ የትምህርት አቀራረብ ሁልጊዜም እንዲተገበር ይመከራል፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ (መልመጃ) ሲቀርብ
- ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ይገባል
- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጁን በመምጣት ማትጋት ይገባል
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባናል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ፣ የአካል ጉዳተኝነት ወዘተ ጉዳዮች አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት

# ምዕራፍ አንድ

# የአካባቢ ጥበቃ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብአዳምጠው መልእክቱን እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ከሚደመጥ ፅሑፍ የሚወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያተጋሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች አያያገሮችን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በማቅረብአቅጣጫ ይጠቁማሉ
- ተማሪዎች ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡ ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።**

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፣
- ከሚደመጥ ፅሑፍ የሚወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣
- ምንባብ አንብበው ዝርዝር ጉዳዮችን ይለያሉ፣
- ለቃላት አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ መስጠት ይችላሉ፣
- አያያዞችን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- አካባቢ ጥበቃን የተመለከተ ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ መናገር
- በስዕል ላይ የተገለጸ ሀሳብን መሰረት አድርጎ መናገር
- የመስክ ጉብኝት አድርጎ የቃል ዘገባ ማቅረብ
- የደን ጭፍጨፋ የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ መናር

### 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- ዝርዝር ጉዳዮችንለመለየት ማንበብ

### 2.4. መፃፍ

- የተሰጡ ቃላትን እየተጠቀሙ አረፍተነገር መመስረት
- የተዛቡ ቃላትን አስተካክሎ አረፍተነገሮች መፃፍ
- አጫጭር አረፍተነገሮችን መፃፍ

### 2.5. ቃላት

- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ቃላትን ከፍቺያቸው ጋር ማዛመድ
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም

### 2.6. ሰዋስው

- አያያዥ ቃላትንመጠቀም

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

**የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ**

**እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው**

## ምዕራፍ አንድ (የአካባቢ ጥበቃ)

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች አዳምጠውና ያዳመጡትንም መሰረት አድርገው የተለያዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ

## የአካባቢ ጥበቃ ጀግኒት

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ ወደ ማዳመጥ ተግባር ከመገባቱ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስና ከዕለቱ ትምህርት ጋር ለማስተሳሰር የሚያግዙ ናቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ

እባክዎ መምህር ምንባቡን **ትክክለኛነትን፣ ተገቢውን ፍጥነትና አገላለፅን** በተከተለ መልኩ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው።ተማሪዎቹ እያዳመጡም መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ሰንጠረዥ እንዲያሟሉ ይንገሯቸው። ምንባቡን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው።

## የአካባቢ ጥበቃ ጀግኒት

ጥሩነሽ የደን መመናመን በጣም ያሳስባታል። ይህንን ጉዳይ ለትምህርት ቤት ጓደኞቿ ሁሉ አጫውታለች። ብዙዎቹ ጓደኞቿም ሀሳቧን **ተጋርተዋታል**። ይሁን እንጂ ደጋግመው እሷ ምንም ልታደርግ እንደማትችል ነግረዋታል። ጥሩነሽ ግን ተስፋ አልቆረጠችም። አንድ ቀን ጓደኞቿን "ለምን የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አናቋቁምም?" አለቻቸው። ጓደኞቿ "ምን ሊያደርግልን ነው የምናቋቁመው?" አሏት። "መጀመሪያ እናንተ ብቻ ተስማሙልኝ እንጂ እኔ ዝርዝር ዕቅዱን አውጥቼ አቀርባለሁ" አለች። ጓደኞቿም እስኪ ይሁን ተስማምተናል አንቺ እቅዱን አቅርቢ አሏት።

ጥሩነሽም **በቃሏ መሰረት** በቀጣዩ ቀን እቅዷን ይዛ ቀረበች። ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ፣ የትና መቼ እንደሚያከናውኑና እንዴት ሊያከናውኑት እንደሚችሉም አስረዳቻቸው። ጓደኞቿም በስራዋ በጣም ተገረሙ። እንደዚህ በፍጥነት ሁሉን ነገር በዝርዝር ታቀርባለች ብለው አልጠበቁም ነበር።

ጥሩነሽና ጓደኞቿ ተያይዘው ወደ ትምህርት ቤቷ ርዕሰ መምህርት ዘንድ ሄዱ። የአካባቢ ጥበቃ ክበብ ሊያቋቁሙ እንደሚፈልጉና ለዚህም ዝርዝር ዕቅድ እንዳዘጋጁ አስረዱ። እቅዳቸውም መጀመሪያ ከትምህርት ቤታቸው ግቢ እንደሚጀምርና ወደ አካባቢያቸው እንደሚሸጋገር ገለፁ። የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሶችና ሌሎች እገዛዎችንም ተናገሩ። ርዕሰ መምህርቷ የጥሩነሽና ጓደኞቿ ሀሳብ እጅግ የሚያስደስት መሆኑን ተናገሩ። “አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እናደርግላችኋለን” በማለትም ቃል ገቡ።

በሚቀጥለው ቀን ርዕሰ መምህርቷ መምህራንን ሰብስበው የነጥሩነሽን ሀሳብ **አጋሯቸው**። መምህራኑም የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ ደስተኛ መሆናቸውን አሳወቁ። ከነጥሩነሽ ጋር በመሆንም በየክፍሉ እየዞሩ የክበቡን አላማና ዝርዝር ተግባራት አስረዱ። ተማሪዎቹም በፈቃደኝነት አባል ሆነው እንዲመዘገቡ ጠየቁ። በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችም የክበቡ አባል በመሆን ተመዘገቡ። ጥሩነሽም “አሁን የእቅዴ አንዱ እርምጃ ተጀመረ” አለች።

እነጥሩነሽ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የትምህት ቤቱን ማህበረሰብ በማስተባበር ብዙ አገር በቀል ችግኞችን በቅጥር ግቢው ውስጥ እንዲተከል አደረገች። የተራቆተው ግቢም በአረንጓዴ ተክሎች **አሸበረቀ**። የአቧራውና የቆሻሻው ክምር ተወገደ። የአበቦቹና የተክሎቹ መዓዛ ቅጥር ግቢውን **አወደው**። ትምህርት ቤቱም በሴሚስቴሩ መጨረሻ ላይ “የአካባቢ ጥበቃ ጀግኖች” ሲል ጥሩነሽንና ጓደኞቿን ዋንጫ ሸለማቸው። የጥሩነሽ ቤተሰቦችም በልጃቸው ስራ ኮሩ። የአካባቢው ማህበረሰብም የነጥሩነሽንና ጓደኞቿን አስደናቂ ተግባር በመስማት አደነቁ። ከነጥሩነሽ ጋር በመሆንም በአካባቢው የነበረ **የተራቆተ**ቦታን ለማልማት ይችሉ እንደሆነ ጥያቄ አቀረቡ። እነጥሩነሽም ከትምህርት ቤታቸው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ መስማማታቸውን አሳወቁ። ስራው ወዲያው ተጀመረ። በሺዎች የሚቆጠሩ **አገር በቀል** ችግኞች ተተከሉ። ከአመታት በኋላ ተራራው ወደ ቀድሞው ውበቱ ተመለሰ፣ የዱር እንስሳትና አዕዋፍት በውስጡ **መቦረቅ** ጀመሩ። በአካባቢው የነበረው ከፍተኛ ሙቀት እየቀነሰ ሄደ። ብዙ ሰዎች ለጉብኝትና ለመዝናናት ወደ ተራራው **ጎረፉ**። እነጥሩነሽ

የአካባቢ ጥበቃ ጀግኖች መሆናቸውን በድጋሚ አስመሰከሩ። ጥሩነሽ ህልሚ ስለተሳካላት እጅግ በጣም ደስ አላት።

**ክፍለጊዜ፡ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

*መምህር ተማሪዎችዎ በመልመጃ አንድ በ'ሀ' ስር ያሉትን ጥያቄዎች መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ ደግሞበአነስተኛ ቡድን (4/5) ሆነው መልሶቻቸውን እንዲያነፃፅሩ ካደረጓቸው በኋላ ጥያቄዎቹን እያነበቡ በተወካያቸው በኩል ቃላዊ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። በመቀጠል ደግሞ በየግላቸው በ'ለ'ስር ያሉትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲመልሱ ይጋዟቸው።*

**ክፍለ ጊዜ፡ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍልተማሪዎች የቀረበ ስዕልን እየተመለከቱ ገለፃ ያቀርባሉ፤ ምልከታ አካሂደው የቃል ዘገባ ያቀርባሉ

## ተግባር አንድ

*መምህር በተማሪው መጽሐፍ በተግባር አንድ የተገለጸዉን ስዕልተማሪዎችበመመልከት ስለ ስዕሉ ገለፃ እየሰጡ እንዲናገሩ ያትጓቸዉ። (በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ይከውኑ፤ ሁሉም የመናገር ዕድል ያግኝ፤ የሚታቀቡ ተማሪዎች ሲያጋጥምዎ ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን ስለስዕሎ እየጠየቁ ተሳታፊ ያድርጓቸው፤ 'አየኸው/አየሺው ይሄን? ምን ይመስልሻል/ይመስልሃል?' ወዘተ)*

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ተግባር ሁለት

*በቀረቡት ነጥቦች ዙሪያ መረጃ አጠናቅረው እንዲመጡ አስቀድመው በየቤት ስራ መልክ በመስጠት (ባለሞያ፣ ቤተሰብ ወይም የአካባቢ ሰው የመረጃ ምንጫቸው ሊሆን ይችላል) ይዘው የመጡትን መረጃ በቃል ዘገባ እንዲያቀርቡት ያበረታቷቸው።*

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሶስት

ስለ ደን ጭፍጨፋ እና መፍትሄዎቹ ንግግር በቡድን ተወያይተው በተወካይ አማካኝነት የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታቱ።

## ክፍለ ጊዜ፡ስድስት

### ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

*መምህር! ተማሪዎችዎ በዚህ ክፍለጊዜ የመጀመሪያውን ምዕራፍ የመጀመሪያ ምንባብ በራሳቸው ያነባሉ! የማንበብ ተግባሩም አስደሳች ይሆንላቸው ዘንድ የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎቹን አሳታፊ በሆነ ሁኔታ በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ንባቡን በንቃት እንዲያከናውኑም ያበረታቷቸው።*

### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

አንዴ መፅሐፋቸው ላይ ያለ ስዕልን ቃኘት እንዲያደርጉ ያሳስቧቸው፤ በመቀጠል የቅድመንባብ ጥያቄዎች እያነበቡ በቃል እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፤ ጥቂት ተማሪዎች ምላሻቸውን ለክፍሉ ያቅርቡ።

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

አሁን ሁሉም ተማሪዎች ምንባቡን ከመፅሐፋቸው ላይ እንዲያነቡ ይጋበዙ። የንባብ ጊዜ ጥያቄዎቹንም እየመለሱ ይሂዱ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

*ሀ. እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ በቀረቡት ሦስት ሀሳቦች ዙሪያ በቡድን በቡድን እየሆኑ ሃሳብ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፤ በውይይታቸው ወቅትም እየተዘዋወሩ በመቃኘት የንግግር ችሎታቸውን ይመዝኑ።*

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

ይህ ክፍለጊዜ በክፍለጊዜ 7 እንደቀረበው ሁሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ እድል የሚፈጥር ነው። በመሆኑም ተማሪዎችዎ በመጀመሪያ ጥንድ ጥንድ ሆነው ጥያቄዎቹን እየተነጋገሩ ይስሩ፣ በመቀጠልም በአነስተኛ ቡድን በጥንድ ሆነው ያነሷቸውን ሀሳቦች መልሰው በማንሳት ለቡድን አባላቶቻቸው እያቀረቡ እንዲነጋገሩ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

*መምህር! በዚህ ትምህርት ክፍል የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ተማሪዎች እንዲጽፉ የሚያግዙ መልመጃዎችና ተግባራት ስለቀረቡ በትእዛዛቱ መሰረት ያሰሯቸው።*

### መልመጃ ሶስት

እባክዎ መምህር አስቀድመው ሰሌዳ ላይ ሁለት ወይም ሦስት ምሳሌዎችን በመፃፍ ሰርተው ያሳዮአቸው፤ ይህንንም መሰረት አድርገው ተማሪዎችዎ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጠውን መልመጃ እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስር

*መምህር! ተማሪዎችዎ ተዛብተው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በማስተካከል መልሰው እንዲጽፏቸው ይንገሯቸው። አስቀድመውም ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት ምሳሌዎችን ሰርተው ያሳዩአቸው። በአጨራረሳቸው ቅደም ተከተልም ደብተራቸውን ያርሙላቸው፤ የክፍሉንም ተማሪዎቹን እያሳተፉ አጠቃላይ ግብረ መልስ ይስጡ።*

ምሳሌ፡ 1. *ኮረና ነው የወረርሺኝ በሽታ አደገኛ።*

**ኮረና አደገኛ የወረርሺኝ በሽታ ነው።**

2. ላኩላት ለእህቴ ዕፌ ደብዳቤ።

**ለእህቴ ደብዳቤ ዕፌ ላኩላት።**

**ደብዳቤ ለእህቴ ዕፌ ላኩላት።**

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ይህንን ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ለቃላት አገባባዊና ከአገባብ ውጪ የሆነ ፍቺን መስጠት ይችላሉ

### መልመጃ አራት

እባክዎ መምህር በ 'ሀ' ስር ለተሰጡት ቃላት የሚሆኑ ፍቺዎችን ተማሪዎቹ ከ'ለ' ስር እየመረጡ በደብተራቸው ላይ በመፃፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ምላሻቸውን ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር እንዲያስተያዩ ይዘዟቸው። ምላሾቹ ላይ እንደክፍል ከተነጋገራችሁ በኋላ ስለቃላቱ ፍቺ የጠራ ግንዛቤ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ያግባቧቸው። አፈፃፀማቸውን እያዩም ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

በ'ለ' እና በ'ሐ' ስር ያሉ ጥያቄዎችን ደብተራቸው ላይ በመፃፍ በትዕዛዛቱ መሰረት እንዲሰሩ ይንገሯቸው። ትዕዛዛቱን መረዳት የሚቸገሩ ተማሪዎች ካጋጠሙዎት ከሁለቱም መልመጃዎች አንድ አንድ ምሳሌዎችን ይስሩላቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

እባክዎ መምህር አንድን ቃል በተለያየ አውድ መጠቀምን የሚያሳየውን ምሳሌ ከተማሪዎቹ መፅሐፍ በማየት ሰሌዳ ላይ ፅፈው ቃሉ(**ቆረጠች**) በሁለቱ አረፍተነገሮች ውስጥ የያዘውን ፍቺ ያስረዷቸው። የተሰጡትን ቃላትም በተመሳሳይ መንገድ እንዲሰሯቸው ይንገሯቸው፤ እንደአፈፃፀም ቅደምተከተላቸውም እርማት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ነዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ይጠበቃል።

መምህር ይህንን ክፍለጊዜ ስለነጠላና ድርብ አረፍተነገሮች ገለፃ፣ ማስታወሻና ምሳሌዎችን በመስጠት ይጠቀሙት። ለዚህም በተማሪዎቹ መፅሐፍ ላይ ያለውን ማስታወሻ ይጠቀሙት፤ ሌሎች ማጣቀሻ መፅሐፍትንም መቃኘት ጠቃሚ ነው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## መልመጃ አምስት

እባክዎ መምህር በዚህ መልመጃ ስር ያሉ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ መለማመጃ ደብተሮቻቸው ላይ እንዲፅፉ ይጠቁሟቸው። በመቀጠልም አረፍተነገሮቹ ነጠላ ወይም ድርብ ስለመሆናቸው እየለዩ ያመልክቱ በግላቸው ሲጨርሱም መልሶቻቸውን ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ያመሳክሩ። በመጨረሻ እንደ ክፍል መልሶቹ ላይ ተነጋገሩ ወይም ደብተሮቻቸውን ሰብስበው እርማትና ምጋቤ ምላሽ ይስጡበት።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

መምህር አስቀድመው በተማሪዎቹ መፅሀፍ ላይ ያለውን ማስታወሻ መሰረት አድርገው አጠር ያለ አሳታፊ ገለፃ ሰሌዳውን እየተጠቀሙ ይስጡ። ስለአያያዦቹ ግንዛቤ መፈጠሩን ካረጋገጡ በኋላ በ‘ለ’ ስር ያለውን መልመጃ ተማሪዎቹ ፅፈው እንዲሰሩ ይዘዟቸው። አፈፃፀሙን እየተመለከቱም ምዘና ያካሂዱ።

## ክፍለጊዜ ፡ አስራ ሰባት

በ‘ሐ’ ስር አያያዦችን በተመለከተ ተጨማሪ መለማመጃ ለተማሪዎቹ ቀርቧል። ይህንንም መለማመጃ ደብተራቸው ላይ በመፃፍ መጀመሪያ በግላቸው እንዲሰሩት ያድርጉ፤ በመቀጠል ጥንድ ጥንድ እየሆኑ መልሶቻቸውን ያነፃፅሩ፤ እንደክፍልም ተማሪዎችን ጋብዘው አረፍተነገሮቹን እያስነበቡ አያያዦቹን ለዩ፤ ለምን ተግባርም ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተነጋገሩ (ተጨማሪ ሀሳብ ለማቅረብ፣ ተቃርኖን ለመግለፅ…ወዘተ)።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መምህር በዚህ የምዕራፍ አንድ የመጨረሻ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ የተሰጧቸውን አያያዦች ተጠቅመው የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ። ስለሆነም እባክዎ አስቀድመው እንዴት እንደሚሰራ ምሳሌዎችን በመስጠት ተማሪዎችዎን ያዘጋጇቸውና አረፍተነገሮቹን እንዲፅፉ ያበረታቷቸው።

# የመልመጃዎችና ተግባራት አማራጭ ምላሾች

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

**ሀ.** ማናቸውም ከጥያቄዎቹ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና የተማሪዎቹን አካባቢያዊ ልምዶች የሚያንፀባርቁ መልሶች

**ለ. የአካባቢ ጥበቃ** ብለው እንዲመልሱ ይጠበቃል

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

እያዳመጣችሁ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ጥሩነሽ እና ጓደኞቿ | ያከናወኗቸው ተግባራት |
|---|---|
| መጀመሪያ | ርዕሰ መምህርቷ ጋር ተወያዩ |
| በቀጣይ | መምህራንና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር |
| መጨረሻ | ት/ት ቤት ግቢ ውስጥ ችግኞች ተክለው ግቢውን አስዋቡት |

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1.ከጓደኞቿ ጋር

2. የትምህርት ቤቷ ርዕሰመምህርት

3. የተመናመነው/ ተክሎች የሌሉበት

4. ትምህርት ቤቱ

5. አካባቢ መንከባከብን/እቅድ ማቀድና መፈፀምን/አላማ ማሳካትን

**ለ.** 1. ሀሰት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሀሰት /እሷንና ጓደኞቿን/

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

የቀረበውን ስዕል እያዩ ያደረጉት ንግግር

**ተግባር ሁለት**

ከመስክ ምልከታ በኋላ የሚቀርብ የቃል ዘገባ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

ከተራ ቁጥር 1-3ከተነሱት ጥያቄዎች ይዘቶች ጋር የተገናኙና ማናቸውም የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት/ተሞክሮ/ ከግምት ያስገቡ ምላሾች ተቀባይነት አላቸው።

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. አንቀፅ 1 እና 2ን ተረድተው ተማሪዎቹ የሚመልሱት ማንኛውም ከአንቀፆቹ ይዘት ያልወጣ መልስ

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. ደን ለማገዶነት መቆረጥ፣ የእርሻ ቦታ ፍለጋ፣ የግጦሽ ቦታ ፍለጋ
2. የአፈር መሸርሸር፣ የዱር እንስሳት ስደት፣ በረሃማነት፣ ድርቅና ጎርፍ፣ ስነምህዳር መናጋት
3. ዛፎችን አለመቁረጥ፣ ሰደድ እሳት እንዳይከሰት መጠንቀቅ፣ ችግኞችን መትከል

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ለ.** 1. የደኖች መመናመን/ የአካባቢ ጥበቃ አለመኖር
2. የሚከሰት ጎርፍ
3. የአየር ጠባይ ለውጥ ይከሰታል ወዘተ
4. ለማዳን/ለማትረፍ
5. በረሃማነት፣ ድርቅ ወይም የጎርፍ አደጋ

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**ሀ.** ሁለቱንም ጥንድ ጥንድ ሆነው በህዝባር ተከፍለው የቀረቡ ቃላትን ተጠቅሞ የተመሰረተ ማንኛውም ተቀባይነት ያለው አረፍተነገር /ሰዋስዋዊ ተቀባይነት ያለው/ ምላሽ ይሆናል

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ለ.**1. ሔዋን ችግኝ ተከለችና ተንከባከበች።
2. ናኦል ስራ አግዘን ወይም አጥና። /ናኦል አጥና ወይም ስራ አግዘን።/

3.ገመቹ ጥናት ያጠናል ነገር ግን ፈተና አላለፈም።

4. አልማዝ ታመመች በመሆኑም ወደሀኪም ቤት ሄደች።

5. ሰፈራችን ቆሽሿል ስለዚህ ማፅዳት አለብን።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ አራት**

**ሀ. አዛምድ** 1. **ሰ** 2. **ረ** 3. **ሀ** 4. **ለ** 5. **መ** 6. **ሐ** 7. **ሸ** 8. **ሠ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ.** 1. ውድመት 2. ለመታደግ 3. በመሸርሸር 4. ጥቅጥቅ ያለ 5. ደኖችን

**ሐ.** 1. **ይጠበቅብናል** - ይገባናል/ የግድ ይለናል

2. **መዛባትን** - መለዋወጥን

3. **የድርሻውን** - የበኩሉን/የራሱን

4. **መራቆት** - መመናመን/መጋለጥ

5. **ውጣ ውረድ** - ተግዳሮት/መውደቅ መነሳት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**መ.** የቀረቡትን ቃላት የተለያዩ ፍቺዎች የሚያመለክቱ ማናቸውም ሰዋስዋዊ የሆኑ አረፍተነገሮች ተቀባይነት አላቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ አምስት**

1.ድርብ 2. ነጠላ 3.ድርብ 4.ነጠላ 5. ነጠላ

**ለ.** 1.ወይም 2. ነገር ግን/ግን 3. ስለዚህ 4. እና 5. ስለዚህ/በመሆኑም

**ክፍለጊዜ ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ.** 1. ወይም 2. ነገር ግን 3. ስለዚህ 4. እና/ና 5. ስለሆነም

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መ.** ማናቸውም የተሰጡትን አያያዦች ተጠቅመው የተመሰረቱ አረፍተነገሮች ተቀባይነት አላቸው ሰዋስውን እስከጠበቁ ድረስ

# ምዕራፍ ሁለት
# የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች የመንገድ ላይ ጥንቃቄን በተመለከተ መዝሙር እንዲዘምሩ ያለማምዳሉ
- ተማሪዎች ምንባብን በአግባቡ (አቀላጥፈው) እንዲያነቡ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ቃላትን ከነባር ሁኔታዎች ጋር እንዲያዛምዱ ምሪት ይሰጣሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊና መዝገበቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች አያያዦችን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ፥ ምሳሌዎችን በማቅረብ አቅጣጫ ይጠቁማሉ
- ተማሪዎች ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለ መንገድ ላይ ጥንቃቄ  የተዘጋጅን መዝሙር አዳምጠው ይዘምራሉ፤
- በሚጠበቀው ደረጃ የቀረበውን አንቀጽ ድምጻቸወን ከፍ አድርገው ያነባሉ፤
- የቃላትን ከነባሪ ሁኔታዎች ጋር ያዛምዳሉ፤
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ድርብ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ከሚደመጥ ፅሑፍ የሚወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- መዝሙር ተለማምዶ ለመዘመር ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- የመንገድ ላይ ጥንቃቄን በተመለከተ መናገር
- የቀረበ መዝሙርን መነሻ አድርጎ መናገር
- የመንገድ ላይ አደጋ የሚያስከትሉ ክስተቶችን በተመለከተ መናገር

### 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- ዝርዝር ጉዳዮችን ለመለየት ማንበብ

### 2.4. ቃላት

- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ቃላትን ከፍቺያቸው ጋር ማዛመድ
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም

### 2.5. መፃፍ

- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ አያያዦችን ለይቶ በማውጣት መጻፍ
- መስተጻምሮችን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን መመስረት
- ማስታወሻ መያዝ

### 2.6. ሰዋስው

- አያያዥ ቃላትን መጠቀም
- ነጠላ እና ድርብ አረፍተነገሮችን መለየት
- የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- መዝሙርን ለማስተማሪያነት መጠቀም፣
- ምሳሌ ሰጥቶ የማሰራትን ስልት መከተል
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- መዝሙር አጥንቶ የመዘመር አቅማቸውን መፈተሽ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

**እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው**

## ምዕራፍ ሁለት (የመንገድ ላይ ጥንቃቄ)

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ንዑስ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎታቸውን ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናሉ፤ መዝሙር አዳምጠው ምልሰው ይዘምራሉ፣ አዳምጠው የውይይት ተሳታፊ ይሆናሉ።

### ክፍለጊዜ፡ አንድ

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

እባክዎ መምህር ወደ ማዳመጥ ተግባሩን ከማካሄድዎ በፊት ተማሪዎችዎ ሁለቱን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ልምዳቸውን መሰረት አድርገው እንዲመልሱ ይጠይቋቸው። ከሶስት ወይም አራት ተማሪዎችም ቃላዊ ምላሽ ይቀበሉ።

የዛሬው ክፍለጊዜ የተማሪዎችን ከትራፊክ አደጋ ጋር የተያያዘ ተሞክሮ/ገጠመኝ/ በማቅረብና በዚሁ ጉዳይ ላይ ሀሳብ በመለዋወጥ እንዲካሄድ ተወጥኗል። እርስዎ ፎቶግራፎችን ወይም ስዕሎችን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ።

### ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### የማዳመጥ ጊዜ

በዚህ ክፍለጊዜ የመንገድ ደህንነትን በተመለከተ የተዘጋጀውን የመዝሙር ግጥም ከነዜማው ያቅርቡላቸው (በሞባይልዎ ዜማውን አውርደውና አስቀድመው አሰናድተው ሊያቀርቡላቸውም ይችላሉ)። ተደጋጋሚ ልምምዶችን በማድረግ ተማሪዎችዎ የመዝሙሩን ግጥሞች ከነዜማው አጥንተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ሙሉ ክፍለጊዜው ለዚሁ ተግባር ይውላል። ከመዝናኛነቱ ባለፈ ተማሪዎችዎ ከመዝሙሩ መልዕክት ስለትራፊክ አደጋ አስከፊነት ግንዛቤ ያገኛሉ ተብሎ ይታሰባል።

<u>**አሽከርክር ረጋ ብለህ**</u>

ሁሌም ረጋ ብለን በትዕግስት እንንዳ
ህይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ
ከባድ ኃላፊነት እንዳለብን አውቀን
ሁል ጊዜ ስንጓዝ ይሁን ተጠንቅቀን
መፍጠንና መቅደም አይደለም ችሎታ
ትዕግስት እንላበስ ይኑረን እርጋታ
ሁሌም ረጋ ብለን በትዕግስት እንንዳ
ህይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ
ለእግረኛ ቅድሚያ እንስጥ በየመታጠፊያው
አደጋው ይቀንስ የሰው ህይወት መጥፊያው
ሴቶች እና ህጻናት አረጋውያኑ
በመኪና አደጋ ከማለቅ ይዳኑ
አሽከርክር ረጋ ብለህ ረጋ ብለህ
አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ
እያሽከረከርን እንዳንዘናጋ
በቸልተኝነት ይደርሳል አደጋ
አይገኝምና ህይወት እንደዋዛ
መቼም ቢሆን የትም ለህግ እንገዛ
ከአልኮል ከአደንዛዥ እጽ ከሱስ ሁሉ ጸድተን
ድካም እናስወግድ በቂ እንቅልፍ አግኝተን
ፋታ ያጣ ሹፌር ሁሌም ይዘናጋል
ሰላማዊ ኑሮን በድንገት ያናጋል
አሽከርክር ረጋ ብለህ ረጋ ብለህ
አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ

*ገጣሚያን፡ <u>ሞገስ ተካ እና ይልማ ገብርአብ</u>*

**ድህረ ማዳመጥ**

ተማሪዎችዎ መዝሙሩን በትክክል ስለመያዛቸው መመዘን ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

### መልመጃ አንድ

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ 'አሸከርክር ረጋ ብለህ' የሚለውን መዝሙር አንድ ጊዜ ተማሪዎችዎ እንዲዘምሩት በማድረግ ይጀምሩ፤ ግጥሙ የሚጠፋባቸው ካሉም እያነበቡ ያስታውሷቸው። በመቀጠል **እውነት/ ሀሰት** ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲመልሱ ይጋብዟቸው። የምርጫ ጥያቄውን ደግሞ እያነበቡ ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያበረታቷቸው። የቃላቱን ፍቺ የተመለከተውን መልመጃንም መጀመሪያ በቃል ቀጥሎ ከክፍል ውይይት በኋላ በመፃፍ እንዲመልሱ ያትጓቸው። ተማሪዎችዎ አድካሚ ግን አስደሳች ጊዜ እንዳሳለፉ እንገምታለን!

## ክፍለጊዜ፡ አራት

### ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ይህንን የትምህርት ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎችዎ የትራፊክ አደጋን በተመለከተ ራሳቸውን ችለው ንግግር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል

### ተግባር አንድ

**አሽከርክር ረጋ ብለህ** ከሚለው መዝሙር የተወሰዱ ሀሳቦችን ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በቃል በክፍል በተወካያቸው አማክኝነት ዘገባ ተራ በተራ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ሲወያዩ እየተዘዋወሩና የቃል ዘገባ ሲያቀርቡ የተነሳውን ሀሳብ ፍሬያማነት እያዩ የመናገር ችሎታ ምዘናም ያካሂዱ።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍለጊዜም ተማሪዎች የ**አሽከርክር ረጋ ብለህ** ግጥሞችና ዜማን ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲለማመዱና እንዲዘምሩ ይደረጋል። በመሆኑም እባክዎ መምህር ሞዴል ሆነው ተግባሩን ያስጀምሯቸው። ጣፋጭና አይረሴ ግዜ እንደሚሆናቸው ተስፋ አለን!

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር ሦስት

መምህር የመንገድ ላይ አደጋዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ ቢሆኑም በአገራችን በአመዛኙ የሚደረሱ ጉዳቶች መነሻቸውን የሚያደርጉት በአሽከርካሪና እግረኞች ተግባራቸውን በአግባቡ አለመወጣት እንደሆነ ዘገባዎች ያመለክታሉ። ይህንን ችግር ከስሩ ለመቅረፍ ደግሞ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል። ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም ከዚህ የክፍል ደረጃ ጀምሮ ተማሪዎች ስለጉዳዩ እንዲወያዩ ይደረጋል። ስለሆነም በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ አሽከርካሪና መንገደኞች የአደጋ መንስኤ የሚሆኑባቸውን ጉዳዮች እያነሱ እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ውይይታቸውን እየቃኙም ምዘናና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን ያከናውኑ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ማንበብ በሚለው ንዑስ ትምህርት ክፍል ሲጠናቀቅ ተማሪዎች ምንባብን አቀላጥፈው ያነባሉ፤ እንዲሁም ምንባብ አንብበው የተለያዩ የተረድኦት ተግባራትን ያከናውናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

መምህር እባክዎ ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበብን እንዲለማመዱ ጥንድ ጥንድ በመሆን'የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት' የሚለውን ምንባብ አንቀፆች ተከፋፍለው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው። አንዳቸው ሲያነቡም ሌሎቹ በትክክል ያልተነበቡ ቃላትን እንዲመዘግቡ ይጠይቋቸው። የአቀላጥፎ ማንበብ (ፍጥነት፣ ትክክለኛነትና ገለፃ) አቅም ደረጃቸውንም ይመዝኑ፤ ደቂቃ በመያዝ!

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ተግባር አራት

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜም አስደሳቹን ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ተግባርን ያከናውናሉ። ዛሬ እንዲያነቡ የሚደረገው ግን ባለፈው ክፍለጊዜ ያላነበቡትን አንቀፅ ይሆናል። ወደ ማንበብ ተግባሩ ከመሸጋገራቸው በፊት ግን በስህተት ተነበቡ ብለው የመዘገቧቸውን ቃላት እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸው፤ ቃላቱም ሰሌዳ ላይ ይፃፉ (እርስዎ ፃፏቸው)፤ ስህተቶቹ ዛሬ መደገም አይጠበቅባቸውም።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ተግባር አምስት

በተግባር 5 ከየትራፊክ ደህንነት ጋር የተያያዙ ሀሳቦችን የያዙ ቃላትና ሀረጋት ቀርበዋል። ተማሪዎቹ ሀሳቦቹን በተመለከተ ሀሳብ አቅርበው እዲወያዩም ይጠበቃል። እባክዎ መምህር ለዚሁ ተግባር ማስፈፀሚያነት እንዲያመች ተማሪዎችዎን በአነስተኛ ቡድን (4/5 አባላት) ያደራጁቸውና ወደ ውይይት ያስገቧቸው። ውይይቱን ሲያጠናቅቁምበተወካያቸው አማካኝነት ፅብረቃ ያካሂዱ፤ ቡድኑን የሚወክለው ተማሪ ቋሚ መሆን የለበትም፤ ሚናው ለሁሉም እንዲዳረስ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

የዚህን ንዑስ ትምህርት ይዘት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የተለያዩ አያያዦችን በመጠቀም የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## መልመጃ አራት

ሀ. መምህር ተማሪዎችዎ በዚህ መልመጃ የመጀመሪያ ክፍል ስር ካሉት አረፍተነገሮች ውስጥ አያያዦችን ለይተው በማውጣት እንዲናገሩ ይዘዟቸው። የምላሾቹን ልክነት ወይም አለመሆንም ከሌሎች ተማሪዎች እያረጋገጡ ያስኪዱት።

ለ. በዚህ ክፍል ያሉትን አረፍተነገሮች ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ እየፃፉና አረፍተነገሮቹን እንዲያያይዙ በማድረግ ያሰሯቸው፤ ለመነሻም እርስዎ በምሳሌነት አረፍተ ነገሮች አቅርበው ይስሩላቸው። ተማሪዎቹ ሰርተው ሲጨርሱ እንደአጨራረስ ቅድም ተከተላቸው ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ የትምህርት ክፍል ይዘት ተምረው ሲጨርሱ ለቃላት አገባባዊና ነባራዊ(መዝገበ ቃላዊ) ፍቺ መስጠት ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## መልመጃ አምስት

ሀ. በዚህ መልመጃ የመጀመሪያ ክፍል የቀረቡትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ ጽፈው ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያትጓቸው። ስራቸውንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ። በመቀጠል ጥንድ ጥንድ በመሆን የሰጡትን የቃላትና ሀረጋት ፍቺ እንዲያነጻጽሩ ያድርጉ፤ ሰፊ ልዩነት የታየባቸው ፍቺዎች ካሉም እንዲያቀርቡ ያድርጉና በጋራ ተወያዩባቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ለ. የትራፊክ መብራቶችን የተመለከቱ ቀለማትን የሚገልፁ ቃላት ቀርበዋል፤ እባክዎ መምህር ቀለሞቹን በወረቀት ላይ አስፍረው ወይም በሦስቱ ቀለማት የተሰናዱ ነገሮችን ይዘው በመምጣት (ለምሳሌ በሞባይልዎ የተቀረፀ) ለተማሪዎቹ ውይይት መነሻ ያቅርቡ። ተማሪዎቹ የቀለማቱን ስያሜ፣ ቀለማቱን ሲያዩ ቶሎ ወደ አዕምሯቸው የሚመጡት ነገሮች ምን እንደሆኑ፣ በመንገድ አጠቃቀም ወቅት ቀለሞቹ ለአሽከርካሪዎች እና ለእግረኞች ያላቸውን አንድምታ በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው። ድጋፍ ለሚሹም ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው። ሲጨርሱ ቀለሞቹን ደብተራቸው ላይ አቅልመው (ቀብተው) እንዲመጡ ይዘዟቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

ሰዋስው በተሰኘው ንዑስ ትምህርት ይዘት ስር የቀረበውን ትምህርት ይከታተላሉ፡፡

መምህር የተማሪዎቹ መፅሐፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌ መነሻ በማድረግ ለተማሪዎችዎ ገለፃ ያቅርቡ፤ ሰርተው ያሳዩ! የቀረበውን ማስታወሻም ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩት ያበረታቷቸው፤ ተፈፃሚነቱንም እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ ስድስት

በዚህ መልመጃ ስር የቀረቡ አረፍተነገሮችን ተማሪዎችዎ ደብተራቸው ላይ እነዲፅፉና ነጠላ ወይም ድርብ እያሉ እንዲለዩአቸው ያድርጉ። ለምን ነጠላ ወይም ድርብ እንዳሉም ከጎናቸው ላሉ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው። በመጨረሻም ደብተራቸውን በማረምና በጥያቄዎቹ ላይ የጋራ ውይይት በማድረግ ይቋጩ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ተግባር ስድስት

መምህር ተማሪዎችዎ ስለነጠላና ድርብ አረፍተነገሮች መፅሐፍት አንብበው ያገኙትን ሀሳብና የአረፍተ ነገር አይነቶቹም ምሳሌዎች የሚሆኑትን በማቅረብ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተወያዩ እንዲጋሯቸው ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የሚያነቡትን መፅሐፍ በመጠቆምና ተግባሩን አስቀድመው በመስጠት እገዛ ያድርጉላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## መልመጃ ሰባት

ሀ. እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሯቸው ይዘዟቸው። (በግል ቀጥሎ በጥንድ ከዚያም በቡድን/በጋራ)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

ለ. ከላይበ 'ሀ' ስር በተከናወነው መሰረት ይተግበር።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ተግባር ሰባት

እባክዎ መምህር አስቀድመው ምሳሌ የሚሆኑ ነጠላና ድርብ አረፍተነገሮችን ያቅርቡላቸው። ከዚያም ተማሪዎቹ የየራሳቸውን ጽፈው ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ይጋብዟቸው።

**ምሳሌ፡** ታሲሳ ገበያ ሄደ። (ነጠላ)

ታሲሳ ገበያ ሄደና ሽንኩርት ገዛ። (ድርብ)

አስቴር መኪና ተሳፈረች። (ነጠላ)

አስቴር መኪና ተሳፍራ ነበር ነገር ግን ሀሳቧን ቀይራ ወረደች። (ድርብ)

## የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

### ትምህርት አንድ ማዳመጥ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ማንኛውም ከጥያቄ ይዘቶች ጋር የተያያዙና የተማሪዎቹን ልምዶች የሚያንጸባርቁ መልሶች ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የማዳመጥ ጊዜ ክንውኖች**

መዝሙሩን አዳምጦ በመለማመድ መዘመር

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1. እውነት 2. ሀሰት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. እውነት

**ለ.** 1. ለ 2. ሀ 3. መ 4. ለ 5. መ

**ሐ.** 1. ትዕግስት - አለመቸኮል/መረጋጋት 2. መዳን - መትረፍ

3. አትቸኩል - አትፍጠን 4. አካል - ሰውነት

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ትዕዛዙን መሰረት ያደረገ ምላሽ ይጠበቃል፤ የተለያየ ግን ስለተመሳሳይ ይዘት።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሁለት**

ትዕዛዙን መሰረት ያደረገ ምላሽ ይጠበቃል፤ ስለመዝሙሩ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሶስት**

በተግባሩ የተገለፀውን ይዘት የተመለከተ ንግግር

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

ምንባቡን ጥንድ ጥንድ በመሆን ተራ በተራ ጮክ ብሎ ማንበብ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ተግባር አራት**

1. የተመዘገቡት ቃላት ይቀርባሉ
2. አንቀፆቹ ተደግመው ሲነበቡ የተባሉት ቃላት እየተስተካከሉ ይጠራሉ

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ተግባር አምስት**

በትዕዛዙ መሰረት ማንኛውም ከርዕሰ ጉዳዩ ያልወጣ የተማሪዎች ምላሽ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**መልመጃ አራት**

**ሀ.** 1. እና 2. ወይም 3. ከሆነ ግን 4. ስለዚህ (ድርብ ሰረዞቹም አያያዥ ሆነው ገብተዋል)

**ለ.** 1. የመኪና አደጋ ህያወትን ያሳጣል እንዲሁም/በተጨማሪም/ ንብረትን ያወድማል።

2. ዋቆ እራቱን በላና ተኛ።

3. ቶልቱ በትርፍ ጊዜዋ ታጠናለች ወይም ትጫወታለች።

4. በለጠ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ተፈተነ ይሆን እንጂ ፈተናውን ማለፍ አልቻለም። (ከነዚህ ውጪ ያሉ ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮችም በአማራጭነት ይታያሉ)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ.** 1. ጠርዝ - ጥግ/ዳር

2. በሚመላለሱባቸው - በተደጋጋሚ በሚሄዱና በሚመጡባቸው

3. እግረኞች - መንገደኞች/በእግር ተጓገዦች

4. ለማቋረጥ - ለማለፍ/ለመሻገር

5. ማሳለፍ - ማሻገር/ማስኬድ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ.** ማንኛውም ተቀባይነት ያለው ተማሪዎቹ የሚያቀርቡት ገለፃ/ንግግር

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው**

ገለፃ ማዳመጥ/ማስታወሻ መውሰድ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ.** 1. ድርብ 2. ነጠላ 3. ነጠላ 4. ነጠላ 5. ድርብ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ተግባር ስድስት**

ማንኛውም ተቀባይነት ያለውና ተያያዥ ገለፃ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**መልመጃ ሰባት**

**ሀ.** 1. እና 2. ምክንያቱም 3. ስለዚህ 4. ነገር ግን 5. ያለበለዚያ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ለ.** 1. ሄደች 2. ሮጠ 3. ተከለች 4. አጨደ 5. ጠጣ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ተግባር ሰባት**

ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም ድርብ አረፍተ ነገሮች

# ምዕራፍ ሶስት

# መረዳዳት

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ቅጥያ ያላቸውን ቃላት እየተጠቀሙ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ለማድረግ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች ድርብና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዲፅፉ ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታታሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ምንባብ አዳምጠው መረዳዳትን በተመለከተ ስሜታቸውን ይገልፃሉ፣
- ከሚደመጥ ፅሑፍ የሚወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፤
- ተገቢውን ፍጥነት ጠብቀው ምንባብ ያነባሉ፤
- ለቃላት አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመጠቀም አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፤
- ድርብና ውስብስብ አረፍተነገሮችን ጽፈው ያቀርባሉ፡፡

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ መናገር
- በስዕል ላይ የተገለጸ ሀሳብን መሰረት አድርጎ መናገር
- መረጃ አጠናቅሮ የቃል ዘገባ ማቅረብ

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

### 2.4. መፃፍ

- ቅጥያ ያላቸውን ቃላት መፃፍ
- ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ተጠቅሞ አረፍተነገር መፃፍ
- ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮችን መፃፍ

### 2.5. ቃላት

- ቃላት በአገባብና ከአገባብ ውጪ የሚኖራቸውን ፍች መስጠት
- ቃላት ላይ የተለያዩ ቅጥያዎችን እየጨመሩ ማርባት
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም

### 2.6. ሰዋስው

- በቃላት ላይ ቅጥያዎችን መጨመር
- ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮችን መለየት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች አዳምጠው ስሜታቸውን እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድን መከተል

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- መረዳዳትን በተመለከተ አዳምጠው ስሜታቸውን መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- ቅጥያዎችን መለየትና መጠቀም መቻላቸውን መፈተሽ
- ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮችን በትክክል ለይተው መጠቀም መቻላቸውን መፈተሽ

- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

**እባክዎ መምህር** ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

## ምዕራፍ ሦስት (መረዳዳት)

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች አዳምጠው የተሰማቸውን መግለጽ ይችላሉ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር እባክዎ የቀረቡት ቃላት ምን ትርጉም እንደያዙ ተማሪዎች እንዲገምቱ ይጠይቋቸው፤ የቀረቡትንም የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች (ከ1-4) እንዲመልሱ ያበረታቷቸው።

**እባክዎ መምህር** አሁን የተዘጋጀውን ምንባብ ለደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው።

## የአካል ጉዳተኝነት

የአካል ጉዳተኝነት የሰዎችን ከውልደት ጀምሮም ሆነ በህመም ወይም በአደጋ ምክንያት የተወሰነ የአካል ክፍላቸውን ማጣት ወይም የተወሰነ ተፈጥሯዊ ስርዓታቸው መዛባትን ይመለከታል፡፡

የአካል ጉዳተኝነት የሰው ልጆች የአኗኗር ገጽታ አንዱ አካል ነው፡፡ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ጊዜያዊ ወይም ዘለቄታዊ ጉዳት ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ አካል ጉዳተኝነት ስለአልፈለግነው የሚቀር ሳይሆን ባጋጣሚ የሚመጣ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ ለአካል ጉዳተኞች በተለያዩ ሁኔታዎች ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል የመማር መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶች የትምህርት ሂደቱን ለነዚህ አካላት ማመቻቸት አለባቸው። ከክፍል ውጭ በህንጻዎች መግቢያ እና መውጫ ደረጃ የአካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ መሆን

አለበት። በክፍል ውስጥ የመቀመጫ ወንበሮች ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ መሆን አለባቸው። የትምህርት አሰጣጡም ልዩነት መፍጠር የለበትም። ለአካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው እገዛ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ምንባቡ እየተደመጠ በተማሪ መጽሀፍ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ያድርጉ፡፡

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

በዚህ ክፍለጊዜ አስቀድሞ ባለፈው ስለተነበበው ምንባብ ታሪክ ተማሪዎች አስታውሰው የተወሰነ ነገር እንዲናገሩ ይደረጉ። እባክዎ መምህር የተማሪዎቹ ታሪኩን የማስታወስ አቅም መሰረት አድርገው ምንባቡን አንድጊዜ ፈጠን ባለመልኩ ያንብቡላቸው። በመቀጠልም አረፍተነገሮቹን ፅፈው የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎቹን እንዲሰሯቸው ያድርጉ። እውነት ወይም ሀሰት ያሉበትንም ምክንያት በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ይሁን በመጨረሻም ጥያቄዎቹ በጋራ ይሰሩ።

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

ለ. በዚህ መለማመጃ ስር የቀረቡትን ቃላት ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ በማስፈር ባዳመጡት ምንባብ መሰረት ፍቺያቸውን በማዛመድ እንዲመልሱ ያድርጉ።

ሐ. ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን በመመስረት እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፣ ጊዜ ከፈቀደም የሰሩትን ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## መልመጃ ሁለት

በዚህ ጥያቄ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች መጀመሪያ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ባዳመጡት ምንባብ መሰረት እየተነጋገሩ እዲመልሱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። በመቀጠል በጥንድ የሰሩትን ይዘው ወደ ቡድናቸው እንዲቀላቀሉና ተጨማሪ ውይይት እንዲያደርጉ ይጋብዟቸው። በመጨረሻም በቡድን ተወካዮቻቸው አማካኝነት የቃል ዘገባ ለክፍሉ ያቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ ሌላ ተጨማሪ ውይይት የማድረግ እድል ተመቻችቶላቸዋል። ስለሆነም ስለአካል ጉዳተኝነትና አካል ጉዳተኞችን መርዳት ስለሚቻልበት ሁኔታ በቡድን በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ሁኔታዎችን አመቻቹላቸው (ለምሳሌ አቀማመጥ፣ የመነሻ ሀሳብ በማቅረብ)፤ በውይይታቸውም ወቅት መደማመጥ እንዲኖር ያሳስቧቸው። በመጨረሻም ውይይት ሲያደርጉ ያነሷቸውን ሀሳቦች ለክፍሉ ተራ በተራ እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፤ አንዱ ሲያቀርብ ሌላው ያዳምጥ። ላደረጉት ተሳትፎም ይመስገኑ!

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ይህንን የመናገር ትምህርት ይዘት ተማሪዎችዎ ከተከታተሉ በኋላ ስዕሎችን እየተመለከቱ የመናገር አቅምን ያጎለብታሉ፤ አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ ስሜታቸውን መግለጽ ይችላሉ።

## ተግባር አንድ

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ በመማሪያ መፅሐፋቸው ላይ የሰፈሩትን ስዕል በጥንቃቄ እንዲያጠኑ ያድርጉ። በመቀጠልም በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት እንዲተገብሩት ያበረታቷቸው። ለዚህም ያመች ዘንድ በአነስተኛ ቡድን ያደራጇቸው። በውይይት ወቅትም ተሳትፏቸውን ይመዝኑ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ተግባር ሁለት

ይህ ተግባር አስቀድሞ በቤት ስራ መልክ የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎች መረጃ ሰብስበው፣ አብላልተውና አደራጅተው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህር በትዕዛዙ መሰረት ያሰሯቸው አፈፃፀሙንም በቅርበት ሆነው ይመዝኑ፤ ምጋቡ ምላሽ ይስጡ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

የዚህን ንዑስ ትምህርት ይዘት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ምንባብ አቀላጥፈው ማንበብ ይችላሉ፤ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችንም ይሰራሉ።

## ምንባብ አንድ

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ አቀላጥፎ ማንበብን በተግባር መለማመድ ይችሉ ዘንድ እርስዎ አንድ ጊዜ ሞዴል/አርዓያ/ ሆነው በማንበብ ተማሪዎቹ አንቀፆቹን በጥንድ በጥንድ ተከፋፍለው እንዲያነቡ ያድርጉ። በሚነበብበት ወቅትም ትክክለኛነት፣ ፍጥነትና አገላለፅን በተመለከተ ተማሪዎችዎ የሚያሳዩትን አፈፃፀም አንድ በአንድ ይገምግሙ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ወዲያው ምጋቤ ምላሽ ይስጡ። ታዲያ ተማሪዎችን ለይበልጥ ንባብ በሚያነሳሳ መልኩ!

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ምንባብ ሁለት

**መረዳዳት**

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

እባክዎ መምህር የዛሬውን የማንበብ ተግባር ተማሪዎቹን ወደ ሚነበበው ጽሁፍ የሚያሸጋግሩትን የቅድመምንባብ ጥያቄዎችን በመጠየቅና ለቀረቡት ቃላት ትንበያዊ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ ያስጀምሩ። በመቀጠልም ምንባቡን በአንቀፅ ተከፋፍለው በቡድን ተራ በተራ እንዲያነቡት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። እየተዘዋወሩም ድጋፍና ቃላዊ ማበረታቻ ይስጡ። ወይም የተሻለ ሆኖ ካገኙት በተናጠል ተራ በተራ ለክፍሉ ያንብቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ'ሀ' እና በ'ለ' ስር ያሉትን መልመጃዎች ደብተሮቻቸው ላይ በመፃፍ በየግላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ። በመቀጠል ጥንድ ጥንድ እየሆኑ የሰሩትን

እንዲናበቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። አማራጭነትም ጥያቄዎቹ ላይ በጋራ መነጋገር ይቻላል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## መልመጃ አራት

ሀ. በዚህ መልመጃ ስር ያሉት ጥያቄዎች ደብተር ላይ ተፅፈው እዲመለሱ የሚመከር ነው፤ ስለዚህ ጥያቄዎቹ ከተሰሩ በኋላ መምህር ደብተሮቻቸውን ሰብስበው እርማት ይስጡባቸው። በመጨረሻም የጋራ ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ለ. በዚህ ክፍል እንዲሰሩ የቀረቡት ሦስት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱ ሲሆን ለአፈጻጸሙ ይረዳ ዘንድ መጀመሪያ ተማሪዎችዎ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በመነጋገር ይስሯቸው፤ በመቀጠል የመለሱትን መልስ ይዘው ቡድን ይመስርቱ የተነጋገሩበትንም ሀሳብ ይለዋወጡ። በመጨረሻም በተወካይ አማካኝነት (ለምሳሌ ከየቡድኑ ሁለት ሁለት አቅራቢ) የቃል ዘገባ ለክፍሉ ተራ በተራ ያቅርቡ። የየቡድኑ አቀራረብም ይመዘን።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ተማሪዎች ይህንን የትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ በቃላት ውስጥ ያሉ ቅጥያዎችን ይለያሉ፤ ድርብና ድብልቅ የሆኑ አረፍተነገሮችን ይፅፋሉ

እባክዎ መጻፍ በሚለው ንዑስ ትምህርት የመጀመሪያ ክፍለጊዜ ቅጥያዎችን(የፊት፣ የኋላ) በተመለከተ ዝግጅት አድርገው ገለጻ ያድርጉላቸው። የተለያዩ በቂ ምሳሌዎችን በማቅረብም ቅጥያዎቹ ከተቀጠሉበት አቅጣጫ አኳር የፊት ወይም የኋላ መሆናቸውን አስለዩአቸው። በተሰጡት ምሳሌዎች መሰረትም የሚያውቋቸውና ቃላት እንዲናገሩ ይጋብዟቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ አምስት

ሀ.እባክዎ መምህር ባለፈው ክፍለጊዜ የቀረበውን ገለጻ ከለስ አድረገው አስቀድመው ያቅርቡላቸው (ዋና ዋና ነጥቦችን ብቻ)። በመቀጠል የቀረቡትን ቃላት ደብተራቸው ላይ ፅፈው ዋና ቃሉንና ቅጥያዎቹ የትኞቹ እንደሆኑ፣ በየትኛው በኩል እንደተቀጠሉም

ይለዩ። በመቀጠል የሰሩትን ጥንድ ጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ ትክክለኛነቱን ያረጋግጡ በመጨረሻ እንደክፍል ተወያዩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

ለ. በግል፣ ቀጥሎ በቡድን፣ ከዚያም በቡድን ይሰራ። በአማራጭነትም መምህር ደብተር ሰብስበው እርማት መስጠት ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስድስት

በትዕዛዙ መሰረት በግል ተፅፎ ይሰራ፤ በጥንድ ሆነው ንፅፅር ያድርጉ፤ በመጨረሻም እንደክፍል በጋራ ፅብረቃ ይቅረብበት።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ አረፍተነገሮቹን እንዲያነቧቸው ያድርጉ። በመቀጠል በሳጥኑ ውስጥ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ገለፃ ያቅርቡላቸው። ምሳሌዎችንም ሰሌዳ ላይ ፅፈው ያሳዩአቸው። እየተዘዋወሩም ማስታወሻ ስለመወሰዱ ምልከታ ያድርጉ፤ ግልፅ ያልሆነ ነገር ካለም እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ ስምንት

መምህር በዚህ መልመጃ ስር የቀረቡ አረፍተነገሮችን ድርብ ወይም ድብልቅ ስለመሆናቸው እንዲለዩ ያግዟቸው። ተማሪዎቹ መጀመሪያ በየግላቸው በመፃፍ ሰርተው ከጓደኞቻቸው ጋር ሀሳብ እንዲለዋወጡባቸው ያድርጉ፤ በአማራጭነትም የተማሪዎችን ደብተር ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ሊሰጧቸው ይችላሉ።

### ተግባር አራት

መምህር በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎችዎ አምስት ድርብ ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ እድል ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም የመሰረቷቸውን ዓረፍተ ነገሮች ለክፍል ተማሪዎች እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለጊዜ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

**ፍቺ ግመታ፡መዛባት** - መጣረስ/እንደበፊቱ አለመሆን፤

**ዘለቄታዊ** - የረጅም ጊዜ/የማይቋረጥ/ቋሚ፤

**ማመቻቸት** - ማደላደል/ እንዲደላ ማድረግ

**ሀ.** 1. አለ ወይም የለም ብለው ሊመልሱ ይችላሉ

2. ማንኛውም ከጥያቄው ጋር የተገናዘበ መልስ ተቀባይነት አለው

3. አዎ/አይ

4. ማናቸውም ከአካል ጉዳተኞች ጋር የተያያዙ ከተደመጠው ምንባብ ተቀባይነት አለው

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ዘለቄታዊ

2. በውልደት/በህመም ወይም በአደጋ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. ሀሰት 5. ሀሰት

**ለ.** 1. ለ 2. ሀ 3. ሠ 4. መ 5. ሐ 6. ሰ 7. ረ

**ሐ.** በአዛምድ ስር ያሉትን ተጠቅመው የተመሰረቱ፡ ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮች ምላሽ ይሆናሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**መልመጃ ሁለት**

1. ሰዎችን ከውልደት ጀምሮ ወይም በህመም/በአደጋ ምክንያት የተወሰነ የአካል ክፍላቸውን ማጣት/ ተፈጥሯዊ ስርዓት መዛባት

2. የአንደኛው ወይም ጥቂት የአካል ክፍሎች በትክክል አለመስራት

3. ለአካል ጉዳተኞች ተብሎ የተዘጋጀ በመሆኑ/ የአካል ጉዳት ያለባቸው በመሆኑ

4. ከሌሎች/ከአብዛኛው ተማሪ/ የተለየ ፍላጎት ያላቸው መሆን

5. ህመም ይዞን ህመሙ አካል ጉዳት ሲያስከትል ወይም በተለያዩ ድንገተኛ አደጋዎች ጉዳት ሲደርስብን

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

አካል ጉዳተኞችን የመርዳት ተግባርን የተመለከተ ማንኛውም ሀሳብ በምላሽነት ይቀርባል

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ስዕሎችን የተመለከቱ ማናቸውም ሀሳቦች (አካል ጉዳተኝነት እንዴት እንደሚፈጠር፣ አካል ጉዳተኞችን ስለመርዳት፣ ጉዳተኝነትን ስለመቀነስ የተነሱ)

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር ሁለት**

ተማሪዎች አካል ጉዳተኞችን አሰመልክቶ የሰበሰቡት መረጃ መሰረት ያደረገ የቃል ዘገባ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

ምንባብ አንድ፤ድምፅ ከፍ ተደርጎ ይነበብ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ቅድመማንበብ ጥያቄዎች**

የተማሪዎችን ልምድ ከግምት ያስገባ ማንኛውም የተማሪዎቹ ምላሽ፤

**ቃላት ግመታ፡** **አሳሰበው-** አስጨነቀው፣ **ትብብር-** ትግግዝ፣ **መቀጣጠር-** ቀጠሮ መያዝ/ለመገናኘት ማቀድ/፣ **ዊልቸር-** አካል ጉዳተኞች ከቦታ ቦታ የሚሄዱበት ጎማ ያለው ተንቀሳቃሽ ወንበር

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ይመስለናል ወይም አይመስለንም ብለው ሊመልሱ ይችላሉ፤ ምክንያት ያቅርቡ
2. ተቀጣጠረች
3. መገርቱ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. እውነት

**ለ.** 1. ረ 2. ሰ 3. ሀ 4. ለ 5. ሐ 6. መ 7. ሠ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**መልመጃ አራት**

**ሀ.** 1. ለ 2. ለ 3. መ 4. ሀ 5. ሀ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ.**1. ተማሪዎቹ የመለሱት ከጥያቄው ጋር የተዛመደ ማንኛውም ምላሽ

2. አካል ጉዳተኞችን ተባብረን እንርዳ

3. ተማሪዎቹ የሚሰጡት ማናቸውም አካል ጉዳተኞችን መርዳትን የተመለከተ ምላሽ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

ገለፃና ምሳሌዎች ይቅረቡ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ አምስት**

**ሰማያዊ** - ሰማይ-አዊ፣ **አስመለሰ** አስ- መለሰ፣ **አልመጣም** አል-መጣ- ም፣ **ፈረሰኛ** ፈረስ - ኛኛ፣ **ጠራው** ጠራ-ው፣ **ሄዶች** ሄደ- ች፣ **ተወረወረ** ተ- ወረወረ፣ **አስመጣ** አስ-መጣ፣ **ቅጥያዎች** ቅጥያ-ዎች

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ለ.** ማናቸውም ተማሪዎቹ የሚመልሷቸውና የተሰጡትን ቅጥያዎች ተጠቅመው የተመሰረቱ ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮች መልስ ይሆናሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**መልመጃ ስድስት**

1. ትዕግስት **ስለመጣች** ደስ **አለኝ**። (ስለ-፣ -ኝ)
2. ሮባ ብዙ **ደብተሮች ይገዛል**። (-ኦች፣ ይ-ል)
3. **ተራራማ አካባቢዎችን አየሁ**።(-ኣማ፣ -ዎች-ን፣ -ሁ)
4. **እነማሞ ወደቤት እየሄዱ** ነው። (እነ-፣ ወደ-፣ እየ- -ኡ)
5. ሁለት **ብርጭቆዎች ተሰበሩ**። (-ዎች፣ ተ- -ኡ)
6. **የሰለሞን** ወንድም **በሬዎቹን አሰማራ**።(የ-፣ -ን፣ -ዎች፣ -ኡ-፣ -ን፣ አስ-ተሰማራ/አሰማራ/)
7. እርሳስ፣ **መቅረጫ** እና **ደብተሮች ገዛሁ**።(መቅረፅ-ኢ.ያ፣-ኦች፣ -ሁ)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**መልመጃ ሰባት**

ተማሪዎቹ አረፍተነገሮቹን ማንበብ፤ ገለፃ ስለድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮች

1. ድብልቅ 2. ድርብ 3. ድርብ 4. ድብልቅ 5. ድብልቅ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መልመጃ ስምንት**

1. ድብልቅ 2. ድርብ 3. ድብልቅ 4. ድርብ

**ተግባር አራት**

ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮች

# ምዕራፍ አራት

# ሥርዓተጸታ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች ከቀረበላቸው ምንባብ የተወሰኑ መረጃዎችን እንዕፉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች የአንቀፅን ፅንሰሀሳብ እንዲገልፁ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ቃላት እንዲለዩ ምሳሌዎችና ፍንጮችን በመጠቆም ተሳታፊ ያደርጋሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች የተውሶ ቃላትን ለይተው ማመልከት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ግሶችን ተጠቅመው የተለያዩ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያስተባብራሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ምንባብ አዳምጠው ስርዓተጾታን በተመለከተ ስሜታቸውን ይገልፃሉ፣
- ከቀረበው ምንባብ መረጃ አጠናቅረው ይፅፋሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣
- ተገቢውን ፍጥነት ጠብቀው ምንባብ ያነባሉ፣
- የአንቀፅ ምንነትን ይገልፃሉ፣
- የተውሶ ቃላትን ለይተው ያመለክታሉ
- ለቃላት አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ መስጠት ይችላሉ፣
- ግሶችን ተጠቅመው አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ስርዓተፆታ ጋር በተገናኘ የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና የቃል ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- ስርዓተፆታን በተመለከተ መናገር
- ክርክር በማድረግ ወቅት መናገር
- ምስልን ተመልክቶ መናገር

## 2.3. ማንበብ

- ክርክር አደራረግን ለመረዳት ማንበብ
- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

## 2.4. መፃፍ

- አንቀፅን በተመለከተ መፃፍ

- የተውሶ ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር መጻፍ
- ግሶችን በመጠቀም አረፍተነገር መመስረት

### 2.5. ቃላት

- የተውሶ ቃላትን መለየትና መጠቀም
- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ግሶችን ለይቶ መጠቀም

### 2.6. ሰዋስው

- ግሶችን በመጠቀም አረፍተነገሮችን መመስረት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች አዳምጠው ስሜታቸውን እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድን መከተል

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- ስርዓተጸታንን በተመለከተ አዳምጠው ስሜታቸውን መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- የተውሶ ቃላትን መለየትና መጠቀም መቻላቸውን መፈተሽ
- ግሶችን በመጠቀም አረፍተነገሮች መመስረትመቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

**እባክዎ መምህር** ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

## ምዕራፍ አራት (ሥርዓተጾታ)

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ስለስርዓተጾታ አዳምጠው የተሰማቸውን መግለጽ ይችላሉ፤ አዳምጠው በክርክር ይሳተፋሉ።

**ክፍለ ጊዜ፡አንድ**

## ትምህርትአንድ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ የትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ አዳምጠው ስላዳመጡት ነገር የተገነዘቡትን ይገልፃሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ እንዲሁም አዳምጠው በክርክር ወቅት ንቁ ተሳታፊ መሆን ይችላሉ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ለማዳመጥ ተግባሩ ዝግጁ እንዲሆኑ ይረዳቸው ዘንድ የቅድመማዳመጥ ሦስቱን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፤ ጥያቄዎቹ ከያዟቸው ሀሳቦች ጋር የተዛመዱ ማናቸውም ምላሾች ተቀባይነት አላቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

መምህር ተገቢውን ፍጥነት ተከትለው (የተማሪዎችዎን አቅም ባገናዘበ ሁኔታ) ምንባቡን ማንበብ ይጀምሩ። በዚህን ወቅትም ተማሪዎችዎ እያዳመጡ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን እየሰሩ መሆናቸውን በአይን ይቃኟቸው።

## ጋዲሴ እና ወንድሟ

ስሜ ጋዲሴ ይባላል፤ እድሜዬም ስምንት ዓመት ሞልቷል፡፡ የምኖረው ከአባቴ፣ ከእናቴ፣ ከታናሽ እህቴ እና ከታላቅ ወንድሜ ጋር ነው፡፡ የወንድሜ ስም ጉዲሳ ሲሆን አስር ዓመቱ ነው፡፡

እኔ እና ወንድሜ በወላጆቻችን እንድናከናውን የተመደቡልን ስራዎች አሉ፡፡ ለእኔ የተመደቡልኝ ስራዎች እናቴ ምግብ ስታበስል እቃ በማቀራረብ ማገዝ፣ የምግብ እቃዎችን ማጠብ፣ ቤት መጥረግ እና መወልወል፣ እጅ ማስታጠብ፣ ታናሽ እህቴን መንከባከብ፣ ቡና ማፍላት፣ ከትምህርት ቤት የተሰጠ የቤት ስራ መስራት እና እቤት በፕሮግራም ማጥናት ናቸው፡፡

ለወንድሜ እንዲሰራ የተመደቡለት ስራዎች ደግሞ ልብስ ማጠብ፣ አልጋ ማንጠፍ፣ እቃዎችን ከሱቅ መግዛት፣ ከጓደኞቹ ጋር መጫወት፣ ጓደኞቹ ሰፈር ድረስ ሄዶ ማንበብ፣ ከትምህርት ቤት የተሰጠ የቤት ስራ መስራት እና እቤት በፕሮግራም ማጥናት ናቸው፡፡

እኔን ቅር የሚያሰኘን ነገር ቢኖር ስራ መስራቴ ሳይሆን እንደወንድሜ በእረፍት ጊዜዬ ከጓደኞቼ ጋር እንዳልጫወት መከልከሌ ነው፡፡ እንዲሁም ከእናቴ ጋር የምሰራቸውን የማድቤት ስራዎች እና ህጻን እህቴን ስንከባከብ ወንድሜ ስለማያግዘኝ ለምን እንዲህ እንደሆነ ሁልጊዜ ያሳስበኛል፡፡ ሌላው ቅር የሚያሰኘኝ ነገር ደግሞ ወንድሜ የቤት ስራውን ከጓደኞቹ ጋር ሰፈራቸው ድረስ ሄዶ መስራቱ እና እኔ ይህን እንዳላደርግ በኔ ላይ ወላጆቼ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረጋቸው ነው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

1. ተማሪዎች ሰንጠረዡን ደብተራቸው ላይ አስፍረው እንዲያሟሉት ይዘዟቸው። አፈፃፀማቸውን እየተዘዋወሩ በማየት ምንባቡ በድጋሚ እንዲነበብ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ካለ እባክዎ ያንብቡላቸው። ተማሪዎችዎ በግል ያሟሉትን ሰንጠረዥ በቡድን ሆነው እያስተያዩ መረጃዎቹ ላይ እንዲነጋገሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

2. ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ጋዲሴ ቅር ያሰኛትን ነገር ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲነጋገሩ ያስተባብሯቸው

3. የስራ ክፍፍሉ ፍትሃዊ መሆን አለመሆኑንና ለምን እንደሆነና እንዳልሆነ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ በመጨረሻም እርስዎ ማንኛውም ስራ በሁለቱም

ጸታዎች ሊሰራ እንደሚችልና ስራን እየተጋሩ መስራት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ያስረዷቸው።

4. የየራሳቸውን ምክንያት በምንባቡ መሰረት ይሰጣሉ

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ይህንን ንኡስ ትምህርት ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ በክርክር መሳተፍ ይችላሉ።

## ተግባር አንድ

መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ መደበኛ ክርክር ለማድረግ እድል የሚያገኙበት ወቅት ነው! በዚህም ሀሳብን በምክንያት አስደግፈው መናገርና ሳይጯጯሁ፣ አካላዊ ግጭት ውስጥ ሳይገባ መከራከር ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዷቸው። በዚህም ሁለቱንም ጥያቄዎች የያዙትን ሀሳብ ተራ በተራ እያነሱ እንዲከራከሩ ያበረታቷቸው። ጥያቄዎቹን የተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍለዋቸው በመከራከር እንዲያቀርቡም ማድረግ ይቻላል።

መምህር በቀጣይ ክፍለጊዜ ለሚሰሩት የወንዶችን የሴቶች የስራ ክፍፍል በተመለከተ መረጃ ሰብስበው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

መምህር ባለፈው ክፍለ ጊዜ መረጃ ሰብስበው እንዲመጡ የቤት ስራ መስጠትዎ ይታወሳል፤ ይህንን ስራ ተማሪዎችዎ በግል ተራ በተራ ሀሳብ እንዲያደራጁ እና የቃል ንግግር እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፤ ያበረታቷቸው፤ በመጨረሻም አጠቃላይ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ማስታወሻ (ክርክር)

መምህር እባክዎ የክርክር አካሄድን በተመለከተ የተዘጋጀውን ማስታዎሻ ማብራሪያ እየሰጡ ያስጽፏቸው። በመጨረሻም መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ቃላዊ ጥያቄዎችን ማስታወሻውን መሰረት አድርገው እየጠየቋቸው ዋና ዋና ሀሳቦችን እንዲከልሱ ያድረጉ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ተማሪዎች ከንባብ ተግባሩ አስቀድመው የቀረበውን ምስል እያዩ ሀሳብ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው። በመቀጠል የቅድመምንባብ ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ይጠይቋቸው። ሲጨርሱ ምንባቡን በጥሞና(በዝምታ) እንዲያነቡ ይጋብዟቸው!

## የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻ

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎቹም በማንበብ ሂደት ወቅት ይመለሱ።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

ሀ. በዚህ ትዕዛዝ ስር ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በማንበብ እውነት ወይም ሀሰት በማለት ምንባቡን መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉና መጀመሪያ በግል ቀጥሎም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. መምህር በዚህ ክፍለጊዜም ተማሪዎች ምንባቡን እንደገና አንብበው ሰንጠረዡን ፅፈው እንዲያሟሉና ያሟሉትንም ከሌሎች ጋር እንዲያነጻጽሩ ያበረታቱ።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

ሐ. የምንባቡን አንቀፆች መሰረት አድርገው በ **ለ** ስር ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር ተማሪዎቹ መጀመሪያ በግል ቀጥሎ ደግሞ በቡድን ሆነው እያነፃፀሩ በመወያየት እንዲመልሱ ሁኔታዎችን ያመቻቹ። ተሳትፏቸውን እያዩም ምዘና ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ይህንን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የተውሶ ቃላትን ለይተው ያመለክታሉ፤ ግስ የሆኑ የቃል ክፍሎችን መጠቀም ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ የውሰት ቃላትን የተመለከተውን ማስታወሻ፣ እያስጻፏቸው ገለጻ ያቅርቡላቸው። ምሳሌዎችን እየፈለጉ እንዲሰጡ ያትጓቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

### መልመጃ ሶስት

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ በቡድን ሆነው እየተጋገዙ ከተሰጡት ቃላት መካከል የተውሶ የሆኑትን እንዲለዩ ያበረታቷቸው። ሌሎች የአማርኛ የሚመስሉ ግን የተውሶ የሆኑ ቃላትንም እያሰሱ (ለምሳሌ ሱቅ፣ ኮት፣ ሸሚዝ፣ መኪና፣ በረንዳ፣ ብርጭቆ…) እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። በማስከተልም ከፈጠራና ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ በብዛት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ቃላትን እንዲጠቅሱና በቡድን እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው (ለምሳሌ አቀማመጣቸውን፣ ሴት ወንድ ተማሪዎችን አመጣጥኖ በቡድን ውስጥ ማሳተፍን)።

በየቤት ስራ መልክም ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ሌሎች የተውሶ ቃላትን ፅፈው እንዲመጡና ቃላቱ አቻ የአማርኛ ቃላት ያላቸው እንደሆነ እንዲያጣሩ ያድርጉ (ለምሳሌ ቴሌቪዥን - ትዕንግርተ ሳጥን፣ ሱሪ - ቦላሌ፣ ሞባይል ስልክ - ተንቀሳቃሽ ስልክ ወዘተ)

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

### መልመጃ አራት

እባክዎ መምህር ባለፈው ክፍለዘዜ (ክፍለጊዜ 11) የሰጧቸውን የቤት ስራ በተመለከተ ያከናወኑትን በቡድን በቡድን በመሆን መልሶቻቸውን እያነፃጸሩ እንዲወያዩ የተወሰነ ጊዜ ይስጧቸው። ሲጨርሱም የተውሶ ያሏቸውን እና የአማርኛ አቻ ቃል ይኖራቸው እንደሁ በማረጋገጥ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው።
በመቀጠል በዚህ መልመጃ ስር የተሰጠውን ተግባር በትዕዛዙ መሰረት ሰርተው እንዲያቀርቡ በማድረግ እርማት ይስጡበት።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

ለ. የተውሶ የሚሏቸውና ትምህርቱን መከታተል ከጀመሩ በኋላ ያገኟቸውን ሌሎች ቃላት ፅፈው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው (ለምሳሌ ስፖርት፣ ጌም…)

ሐ. በዚህ ተግባር ስር አማርኛ ከአገር በቀል ቋንቋዎች በመዋስ የሚጠቀማቸውን ቃላት እንዲለዩ የሚያስችል ክንውን ቀርቧል በቡድን እየተነጋገሩ እንዲያሚሉ ያድርጉ፣ በተመሳሳይ መልኩ ከቴክኖሎጂ ጋር የገቡና እየገቡ ያሉ ቀደም ሲል ባሉ ተግባራት ያልተነሱ ቃላትን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው፣ ይህም በቡድን ይሰራ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

ይህንን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ግስ የሆኑ የቃል ክፍሎችን መለየትና መጠቀም ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

እባክዎ መምህር በተማሪዎቹ መፅሐፍ ላይ ያለውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግና ተማሪዎች ግስ ስለሚባለው የቃል ክፍል ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ገለጻ ያቅርቡላቸው።

## መልመጃ አምስት

ሀ. በመቀጠልም ይህንን መልመጃ አምስት በትዕዛዙ መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

ለ. መምህር በተማሪዎቹ መፅሐፍ ላይ በቀረቡት አረፍተነገሮች ላይ ሌሎች ክፍል ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ ሁነቶችን የሚገልጹ አምስት አረፍተነገሮችን ጨምረው ለተማሪዎቹ ያቅርቡላቸውና በአረፍተነገሮቹ ውስጥ የተካተቱት ግሶች የትኞቹ እንደሆኑ ተማሪዎችዎ እንዲለዩ ያበረታቱ። የሰሩትንም መጀመሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያስተያዩና በመቀጠል ለክፍሉ እንዲያንጸባርቁ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ሐ. መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን ሆነው የልየታውን ስራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። አፈጻጸማቸውን እየተዘዋወሩ ይቃኙ። እርማትም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ. በምሳሌው መሰረት ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድና በቡድን እዲሰሩ ያበረታቷቸው። ተጨማሪ ግሶችንም ይስጧቸው። ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙና ግብረመልስ ይስጧቸው።

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለ ጊዜ፡አንድ**

**ትምህርትአንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

ማናቸውም ከጥያቄዎቹ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው መልሶች ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ጋዲሳ
2. ከእናቷ፣ ከአባቷ፣ ከታናሽ እህቷና ከታላቅ ወንድሟ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት የጋዲሴና የጉዲሳ ስራዎችን መዘርዘር

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

የተደመጠውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ማናቸውም ምላሾች

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ተማሪዎቹ አሳማኝ መከራከሪያ አስካቀረቡ ድረስ የትኛውም ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤ እርስዎ ግን ሁለቱንም ያታ ያማከለ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ላይ ተመስርተው ማጠቃለያ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

በተሰጣቸው የቤት ስራ መሰረት የሰበሰቡትን መረጃ አደራጅተው ንግግር ማድረግ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

ማስታወሻና ገለፃ የሚቀርብበት ክፍለጊዜ፤ ቃላዊ ጥያቄዎች ተረድኦትን ለመፈተሽ ሊቀርቡ ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

የቅድመማንበብ ሦስቱ ጥያቄዎችን በተመከተ የቀረበውን ምስልና የተማሪዎችን ዳራ መሰረት በማድረግ ይመለሳል። ማኛውም ከጥያቄዎቹ ይዘት ያላፈነገጠ መልስ ተቀባይት አለው።

የማንብብ ጊዜ ጥያቄዎቹም ምንባቡ እየተነበበ እዲመለሱ ያበረታቷቸው። ምላሾቹም ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ብቻ ሲሆኑ ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. ሀሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሀሰት
6. ሀሰት 7. እውነት 8. እውነት 9. እውነት

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ለ.**

| ተ.ቁ | ተለምዷዊ የወላጆች ኃላፊነቶች | የአሁን ጌዜ የወላጆች ኃላፊነቶች |
|---|---|---|
| 1 | ለወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመወሰን መብት ይሰጣል፤ | ሴቶች እና ወንዶች የቤተሰቡን ገቢ በማምጣት ይሳተፋሉ፤ |
| 2 | እናቶች የቤተሰቡ ተንከባካቢዎች ናቸው | አባቶችም ህጽናትን የመንከባከብ ኃላፊነትን መወጣት ይችላሉ |
| 3 | እናቶች የቤተሰቡን አባላት ህብረት እንዲጠናከር የማድረግ ግዴታ አለባቸው | የስራ ድረሻ ክፍፍል እንዲኖር ይጠይቃል |
| 4 | ልጆች ስለእጣፈንታቸው የመወሰን ሀላፊነት የላቸውም | ልጆች ስለእጣፈንታቸው የመወሰን ሀላፊነት አላቸው |

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ሐ.** 1. ለ 2. ሀ 3. ሠ 4. ሐ 5. መ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

ስለውሰት ቃላት ገለፃ ይቀርባል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. ሜዳሊያ፣ ቴሌቪዥን፣ አትሌት**

**ለ.ቴሌቪዥን፣ ሞባይል፣ ሪሞት፣ መኪና፣ ሜሴጅ፣ ሚስ ኮል፣ ቴክስት፣ ኮምፒውተር፣ ኢሜይል፣ ጌም፣ ቻናል፣ ላፕቶፕ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ ቸኮሌት፣ ኢንዱስትሪ፣ ፋብሪካ፣ ኢንስቶል፣ ላይቭ፣ አፕሊኬሽን...**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**መልመጃ አራት**

| ተቁ | ቃል | የተውሶቃል | የተውሶ ቃልን ያልሆነ |
|---|---|---|---|
| 1 | ገበታ | | ✓ |
| 2 | ሞባይል | ✓ | |
| 3 | ሬድዮ | ✓ | |
| 4 | ገበቴ | | ✓ |
| 5 | መንገድ | | ✓ |
| 6 | ሶላር | ✓ | |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ለ. ተማሪዎቹ የሚያቀርቧቸው ማናቸውም የተውሶ ቃላት**

**ሐ. ከአፋን ኦሮሞ ወደ አማርኛ ቋንቋ የገቡ የውሰት ቃላት**

- አኮሌ
- ሰንጋ
- ጮማ
- አሸቦ
- ቀበቶ

**በቴክኖሎጂ ምክንያት ከሌሎች የውጭ ሀገር ቋንቋዎች ወደ አማርኛ ቋንቋ የገቡ የውሰት ቃላት**

- ቴፕ
- ኮምፒውተር
- ቴሌቪዥን
- ክላሽንኮቭ
- ሞባይል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. ግሶች፡** ሮጠ፣ ጻፈ፣ አጨደ፣ ገመደ፣ አጠረ፣ አረሰ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ለ.** 1. የገዛሆን ሎተሪ እጣ **ወጣ**።
2. ቶሌራ መረብ ኳስ **ተጫወተ**።
3. ጓደኛዬ አጥሩን **ዘለለ**።
4. ቤታቸው በመንገድ ልማት ሰበብ **ፈረሰ**።
5. ቶልቱ ፈረስ **ጋለበች**።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ. ግስ የሆኑ፡** በቀለ፣ ፀለየ፣ ፈጠነ፣ አሠረ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መ.** 1. ቀለጠ - ቀለጠች
2. አመነ - አመነች
3. ዘመረ - ዘመረች
4. ደወለ - ደወለች

# ምዕራፍ አምስት

# ጉብኝት

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ስለቱሪዝም መስህቦችበቃላቸው እንዲገልጹ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብን አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የአንቀፅ ባህሪያትን ለይተው እንዲናገሩ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን መመስረት መቻላቸውን ይከታተላሉ
- ተማሪዎች ቅፅሎችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮችን መመስረት እዲችሉ ምሳሌዎችን በመስጠት ያተጋሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ስለቱሪዝም መስህብ ምንባብ አዳምጠው ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ፣
- ምንባብ አንብበውከፅሑፉ የሚወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣
- የአንቀጽ ባህሪያትን ለይተው ያመለክታሉ
- ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፣
- በአረፍተነገር ምስረታ ወቅት ቅፅሎችን ይጠቀማሉ

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ቱሪዝምን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የአንቀጽ ባህሪያትን በተመለከተ የሚቀርብ ገለጻን ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- ምስሎችን መሰረት አድርጎ መናገር
- የቱሪስት መስህብ ቦታዎችን በተመለከተ መናገር
- ስለአንቀፅ ባህሪያት ማብራሪያ መስጠት
- መረጃ አጠናቅሮ የቃል ዘገባ ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- ቱሪዝምን በተመለከተ የቀረበ ምንባብን ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ
- 

### 2.4. መፃፍ

- ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅሞ መፃፍ

- ቅፅሎችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን መመስረት

## 2.5. ቃላት

- ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማመልከት
- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ቅፅል የሆኑ ቃላትን ለይቶ ማወቅና መጠቀም

## 2.6. ሰዋስው

- በተዘውታሪ ቃላት ሰዋስውን የጠበቀ አረፍተነገር መመስርት
- ቅፅሎችን በመጠቀም አረፍተነገሮች መመስረት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች አዳምጠው የቱሪዝምን ጠቀሜታ እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ምሳሌ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- መረዳዳትን በተመለከተ አዳምጠው ቱሪዝምን መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ተዘውታሪ ቃላትን መጠቀም መቻላቸውን መመዘን
- የአንቀፅ ባህሪያትን ማስረዳት መቻላቸውን መፈተሽ
- ቅጽሎችን ለይተው በአረፍተነገር ምስረታ ወቅት መጠቀም መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

**እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን <u>አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው</u>**

## ምዕራፍ አምስት (ጉብኝት)

### ክፍለጊዜ፡ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የቱሪስት መስህብን በተመለከተ የቀረበ ምንባብን አዳምጠው ቃላዊ ዘገባ ማቅረብ ይችላሉ፤ የማዳመጥ ጊዜና ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

እባክዎ መምህር በመጀመሪያው ክፍለጊዜ የቀረበውን ስዕል ተማሪዎች ተመልክተው ሀሳብ እንዲሰጡ፣ የቅድመማንበብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

በዚህ ክፍለጊዜ ምንባቡ እንዲቀርብ ስላልታቀደ ስለቱሪዝምና ቱሪዝም ስለሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎችና ጉዳቶች (ካሉ)፣ በአገራችን ስላሉ ታዋቂ ቱሪስት መስህቦች፣ የተማሪዎቹ መኖሪያ አካባቢ ስላሉ የቱሪስት መስህቦች ወዘተ እንዲወያዩ ያድርጉ፣ እርስዎም ጥቆማ ይስጧቸው።

### ክፍለ ጊዜ፡ ሁለት

መምህር አሁን ለማዳመጥ ተግባር የተዘጋጀላቸውን ምንባብ የተማሪዎቹን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ሦስት ጊዜ ያንብቡላቸው። ታዲያ ተማሪዎችዎ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነው።

### ጉዞ ከቢሸፍቱ ወደ ባሌ

እኔ እና ቤተሰቦቼ መነሻችንን ከቢሾፍቱ ከተማ አድርገን ወደ ባሌው ሶፍዑመር ዋሻ ጉዟችንን ጀመርን። ሶፍዑመር ዋሻ በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ሶፍዑመር በምትባል አነስተኛ ከተማ አከባቢ ይገኛል። ከመሀል ሀገር አዲስ አበባም ያለው ርቀት ከ500 ኪ.ሜ. በላይ ነው።

ወደ ሶፍዑመር ዋሻ የተጀመረው ጉዞ ባቱ ከተማ ላይ ቁርስ ለመመገብ ገታ እንዲል ተደረገ። ባቱ በአትክልት፣ በፍራፍሬ እና በአሳ ምርቷ የምትታወቅ ናት። ከተማዋን አቋርጠው የሚያልፉ መንገደኞችን እጇን ዘርግታ በረከቶቿን ተቋደሱልኝ ትላለች። ተጓዦችም አያሳፍሯትም፤ ተሽከርካሪዎቻቸውን ጥግ ጥግ እያቆሙ ግብዣዎቿን

ያጣጥሙላታል። ደግመው መጥተው ሊጎበኟት ቃል እየገቡ ይሄዳሉ። እኛም በዕለቱ ቁርሳችንን የተለያዩ ምግቦችን አጣጣምን። አቤት የአሳው ጣዕም!

ከዚያም ለአፍታ የተገታው ጉዟችን እንደገና ተጀመረ። ለሰዓታት ከተጓዝን በኋላም ባሌ ብሄራዊ ፓርክ ደረስን። በዚህ ፓርክ ብዙ ብርቅዬ አራዊቶች ይገኛሉ። ለምሳሌ ከእንስሳት ቀይ ቀበሮ፣ ኒያላ፣ ከርከሮ፣ የመሳሰሉት ይገኛሉ። በዚሁ ፓርክ የተለያዩ ዝርያዎች ያላቸው አዕዋፍትም ይገኛሉ። እነዚህን የተፈጥሮ ፀጋ የሆኑ የዱር እንስሳትንና እፅዋትን ለመጎብኘት በርካታ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ሀገር ጎብኚዎች ወይም ቱሪስቶች በየአመቱ ይመጣሉ።

ባሌ ብሔራዊ ፓርክን ጥቂት አለፍ እንዳልን ዲንሾ ከተማ ገባን። መቼም እዚህች ከተማ ደርሶ የገብስ ቆሎ ሳይቆረጥም የሚያልፍ የለም። እኛም የድረሻችንን ዘግነንና በአካባቢው ያለ ውብ ተፈጥሯዊ ሀብት እያየን ሮቤ ከተማ ደረስን።

ከሮቤ ከተማ ተነስቶ የሶፍዑመር ዋሻ ለመድረስ 110 ኪ.ሜ ያህል ይፈጃል። የጎሮ እና የመልካ አካባቢዎችን እያማተርንና አጃኢብ የሚያሰኙ መልክዓምድር አቀማመጥን እያየን መድረሻችን ሶፍዑመር ከተማ ገባን። ዋሻው ዝቅተኛ ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ቁልቁለቱን ወርደን ዋሻው ደረሰን። ይህ ድንቅ ተፈጥሯዊ ዋሻ ዋናው መግቢያ በር አዮ መከ ይባላል። የወይብ ወንዝም በውስጡ ይገኛል። ዋሻው ከ15 ኪሎሜትር በላይ የሚረዝም ሲሆን መውጫው በር ደግሞ ሁሉቃ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። እድለኛ ሆነን የጎበኘነው ይህ ዋሻ የያዘው ተፈጥሯዊ በረከት አንዴ ከገቡ ውጡ ውጡ የሚያሰኝ አይደለም። ጉብኝቱ በአጠቃላይ ወደ ሁለት ሰዓት ፈጅቶብናል፣ በእርግጠኝነት ተመልሰን እንጎበኘዋለን።

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

በመጀመሪያው የማንበብ ሂደት በጽሞና እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣ በሁለተኛው ዙር ምንባብ የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፣ በሦስተኛው ደግሞ ያልተሟሉ ምላሾችን እንዲያሟሉ እድል ይስጧቸው፡፡

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

የማንበብ ሂደት ሲጠናቀቅ ተማሪዎችዎን እያሳተፉ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን በጋራ አሰሯቸው።

## መልመጃ አንድ

ሀ. በቃል ይሰራ

ለ. ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ ፅፈው ይመልሷቸው

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

ሐ. በዚህ ክፍል ያሉትን የምርጫ ጥያቄዎች ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፤ አስቀድመው ግን በምንባቡ ተነስተው ስለነበሩ ዋና ዋና ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው

መ. እነዚህ ጥያቄዎች በተደመጠው የጉዞ ታሪክ መሰረት በቃል ይመለሳሉ

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ንኡስ ክፍል ተማሪዎች የቱሪስት መስህብ ቦታዎችን በተመከተ ልምዳቸውን መሰረት አድርገው ወይም መረጃ ጠይቀው የቃል ዘገባ ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ. እባክዎ መምህር በተማሪዎች መኖሪያ ያለ የቱሪስት መስህብን ተማሪዎች ራሳቸው ጎብኝተው ወይም የጎበኙ የቤተሰብ አባላትን ስለቦታው ወይም ሁኔታው የቃል ዘገባ እዲያቀርቡ ያትጓቸው፤ ተግባሩንም አስቀድመው በመስጠት ዝግጅት እንዲያደርጉ ይርዷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

ለ. መምህር ተማሪዎችዎ የቤተሰብ አባላት ወይም የአካባቢ ሰዎች ከዚህ ቀደም የጎበኙትን ቦታ በተመለከተ ጥያቄ አቅርበው ወይም በመገናኛ ብዙሃን ሲቀርብ ስለተመለከቱት ወይም ስላዳመጡት የቱሪስት መስህብ ቦታ መረጃ አጠናቅረው በመምጣት ተራ በተራ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፤ ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ: ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ማንበብ የተሰኘውን የትምህርት ንኡስ ክፍል ይዘት ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ የቀረበ ምንባብ አንብበው ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ፤ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

# ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ለማንበብ ተነሳስኦት እንዲኖራቸው አስቀድመው የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያድርጓቸው።

በመቀጠል በለሆሳስ ምንባቡን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፤ ምንባቡ ትንሽ ረዘም ያለ ቢሆንም በተሰጠው ጊዜ እንዲጨርሱ ያበረታቷቸው፤ በንባብ ወቅትም የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ይንገሯቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

ሀ. መምህር እባክዎ እነዚህን ጥያቄዎች መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን ሆነው ተማሪዎችዎ እንዲሰሯቸው ያበረታቷቸው። በመጨረሻም በቡድን ተወካይ ወይም ተወካዮች አማካኝነት የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያትጓቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

ለ. በዚህ ክንውን ስር በምንባቡ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትን ከፍቺያቸው ጋር የማዛመድ ጥያቄ ቀርቧል። መጀመሪያ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ እዲጽፉ ያድርጉ፤ በመቀጠል ወደ ምንባቡ ተመልሰው ቃላቱ የት የት ቦታ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ይመልከቱ፤ ባሉበት አውድም ምን አይነት ፍቺ እንደያዙ ይፈትሹ በመጨረሻም ከቀረቡት አማራጮች እየፈለጉ ፍቺያቸውን ያዛምዱ። ሲጨርሱም ከቅርብ ጓደኞች ጋር ያነጻጽሩ። በጋራም ክፍል ውስጥ ተነጋገሩበት።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ተግባር ሁለት

መምህርም አሁንም ምንባቡን እየተጠቀምን የቋንቋ የተማሪዎችን ክሂሎችን ማጎልበት እንቀጥላለን። በዚህ ተግባር ተማሪዎች በንባብ ያገኙትን ግብኣት (ሀሳብ)ን በራሳቸው አባባል አሳጥረው እንዲገለጹ የሚደረግበት ነው። በመሆኑም ወደኋላ ተመልሰው በምልልሱ ተሳታፊ የነበሩትን ግለሰቦች ምልልስ መሰረት በማድረግ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት

ሰንጠረዡን እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው፤ ለዚህምመ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፤ ይህንን ሲጨረወሱም ወደ ቡድናቸው ተመልሰው በጋራ ምላሻቸውን ያነፃፅሩ በመጨረሻም ለክፍሉ ዘገባ ያቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ከዚህ ንኡስ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የአንቀፅን ባህሪያት ለይተው በማወቅ የቀረቡ አንቀጾች የተጠቀሱት ባህሪያት ይንፀባረቁባቸው እንደሆን ይመረምራሉ፡፡

### ተግባር ሶስት

ሀ. 'ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች' የሚለው ምንባብ የተለያዩ ሀሳቦች ተስተናግደውበታል። እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ወደ ምንባቡ ተመልሰው ዋና ዋና የሚሏቸውን ሀሳቦች ነቅሰው እንዲያወጡ ያበረታቷቸው። ነጥቦቹንም ደብተሮቻቸው ላይ ይፃፉ፤ በመቀጠል ወደ ቡድን ውይይት ይግቡና የያዟቸውን ነጥቦች እነማንነት ለጓደኞቻቸው ያጋሩ። በመጨረሻም የቃል ዘገባ ለክፍሉ ያቅርቡ። መሰላቸት እንዳይኖር በውይይታቸው መካከል እንቆቅልሽ ቢጠይቋቸው ወይም ቀልድ ቢነግሯቸው ይመረጣል፤ ተማሪዎቹ ራሳቸውንም ማስቀረብ ይቻላል።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

ለ. በዚህ ተግባር ስር አንድ አንቀፅ ያለው ምንባብ ቀርቧል፤ በትዕዛዙ መሰረትም ተማሪዎች አንበብውት ዋናውን ሀሳብ እንዲያወጡ ይጋብዛል። ይሁን እንጂ አንቀፁን ከዚህ ተግባር በተጨማሪም አቀላጥፎ ማንበብን ለማለማመጃነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በመሆኑም አስቀድመው ተማሪዎችዎ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡትና ልምምድ እንዲያደርጉበት ይገብዟቸው፤ ምዘና ያካሂዱበት፤ ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው። በመጨረሻ ስለዋና ሀሳቡ ይጠይቋቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

### ተግባር አራት

መምህር ስለአንቀጽ ባህርያት የቀረበውን ጽሁፍ ማስታወሻ እየያዙ እንዲያነቡ ከዚያም ማስታወሻቸውን በአንቀጽ ባህርያት መሰረት አደራጅተው እንዲጽፉና የጻፉትን ለክፍል ተማሪዎች እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ የስራ ሂደቱንም በአንክሮ ይከታተሉ፡፡ የቀረበውን

የአንቀጽ ባህሪያት በተመለከተ ግን እርስዎ ማሳያ የሚሆን አንድ አንቀፅ መርጠው እንዴት በአንቀፁ ውስጥ ያሉ አረፍተነገሮች ግጥምጥምነትን (የሀሳብ ፍሰት ወይም ተያዥነትን እንደፈጠሩ) እና ስለተመሳሳይ ነገር የተናገሩ ስለመሆናቸው ያስረዷቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ተግባር አምስት

እባክዎ መምህር ተማሪዎች እርስዎ ቀደም ባለው ክፍለጊዜ የሰጧቸውን ገለፃና ያቀረቡላቸውን ምሳሌ መነሻ በማድረግ ስለነቦንቱ ጉብኝት የሚያወሳው አንቀፅ የአንቀፅ ባህሪያትን ስለማሟላቱ እንዲገመግሙና የደረሱበትንም ለቡድን አባላቶቻቸው እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው።ሌሎች ተጨማሪ አንቀፆችን ቢሰጧቸውም ልምምዱን ውጤታማ ያደርገዋል (ለምሳሌ ከሌላ ትምህርት፣ እንደአከባቢ ሳይንስ ካሉ መፅሐፍት አንቀፆችን በመጠቀም)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ይህንን ንኡስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎችን መስጠት ይችላሉ።

### መልመጃ ሶስት

ሀ. በዚህ መልመጃ የመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎቹ ለቃላቱ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጧቸው ካበረታቷቸው በኋላ የሰጧቸውን ፍቺዎች ከግምት ባስገባ መልኩ በቃላቱ አረፍተነገሮች እንሲመሰርቱ ይጠይቋቸው፣ ሲጨርሱም የሰሩትን ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲያነፃፅሩ ያትጓቸው፣ በመጨረሻም እርስዎ ደብተሮቻቸውን ሰብስበው እርማት ሊሰጡበት ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

ለ. መምህር በመልመጃ ሦስት ‹‹ሀ›› ስር ተማሪዎችዎ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ከሰጡ በኋላ በቃላቱ አረፍተነገሮችን ሰርተው አቅርበዋል፣ በዚህኛው ክፍል ደግሞ በተቃራኒው ለቀረቡላቸው ለቃላት ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ቃላትን አስቀድመው በመስጠት ቀጥለው አረፍተነገሮችን ይመሰርቱባቸዋል። ይህንኑ ከግምት አስገብተው በግል፣ በጥንድና በቡድን ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ሰዋስው የሚለውን ንኡስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ቅጽል የሆኑ የቃል ክፍሎችን ለይተው መጠቀም ይችላሉ።

መምህር አስቀድመው ቅጽል የቃል ክፍሎች ስለሚባሉት አጠር ያለ ገለፃ ያቅርቡላቸው በገለፃው ወቅትም የሚከተሉትን ነጥቦች ሊያነሱ ይችላሉ፡-

- ቅፅሎች የስም ገላጭ ስለመሆናቸው
- ስምን ከመጠን፣ ከአይነት፣ ከቀለም፣ ከባህሪ አንፃር ሊገልጹ ስለመቻላቸው
- **በጣም** ….. ስም/በጣም + ቅጽል+ ስም/ መዋቅር መካከል ገብተው መነገር ስለመቻላቸው
- ነባር ወይም ውልድ (ከሌሎች ቃላት ስለመገኘታቸው)

## መልመጃ አራት

ሀ. መጽሀፋቸው ላይ ባለው ምሳሌ መሰረት እንዲሰሩ ያትጓቸው፤ የሰሩትን አይተው ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ስድስት

ለ. እባክዎ መምህር ቅፅልን አስመልክተው ባለፈው ክፍለጊዜ ያቀረቡላቸውን ገለፃ መልሰው ይከልሱላቻው። በመቀጠልም የቀረበውን መልመጃ ደብተራቸው ላይ ጽፈው ሀረጋቱን ካዋቀሩት ቃላት መካከል ቅፅሎቹ የትኞቹ እንደሆኑ ለይተው እንዲያመለክቱ ይጠይቋቸው። የሰሩትንም በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲያመሳክሩ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ሐ.መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ ቅፅሎችን እየተጠቀሙ ሀረጋትን እንዲመሰርቱ የሚያደርጉበት ትምህርት ቀርቧል። መጀመሪያ በትዕዙ መሰረት ደብተራቸው ላይ ፅፈው ባዶ ቦታውን ቅጽሎቹን እየመረጡ ያሟሉ፤ በመቀጠል ያሟሉትን ለጓደኞቻቸው ያንብቡላቸው፤ በመጨረሻም ያሟሏቸውን የሚመስሉ ሌሎች አጫጭር ሀረጋትን ቅጽሎችን እየተጠቀሙ እዲመሰርቱ ያትጓቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ. በዚህ መልመጃ ክፍል የቀረቡት ቃላት ቅፅል ስለመሆን አለመሆናቸው ተማሪዎች መጀመሪያ በግል ቀጥሎ ደግሞ በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲለዩ ያድርጓቸው፤ ምላሻቸውንም ክፍሉ በጋራ ይመልከተው፤ ቅፅል የሆኑትን ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ።

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹ የተማሪዎቹን ልምዶች መሰረት አድርገው የሚመለሱ ናቸው። ማናቸውም ከጥያቄዎቹ ይዘት ጋር የተናበቡ ምላሾች ተቀባይነት አላቸው።

## ክፍለ ጊዜ፡ ሁለት

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ቢሾፍቱ ከተማ 2. ሶፍ ዑመር ዋሻ 3. ኦሮሚያ
4. ባቱ 5. ባሌ ብሄራዊ ፓርክ 6. ወይብ ወንዝ

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. ሀሰት 5. ሀሰት 6. እውነት 7. ሀሰት 8. ሀሰት 9. ሀሰት 10. ሀሰት

**ለ.** 1. ሠ 2. ሀ 3. መ 4. ለ 5. ሐ

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

**ሐ.** 1. መ 2. መ 3. ሀ 4. ለ 5. መ 6. ሐ 7. ሐ 8. ለ

## ክፍለጊዜ፡ አራት

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ሀ. ማንኛውም የተማሪዎችን የጉብኝት ልምድ የያዘ ዘገባ ምላሽ ይሆናል።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

ለ. የቤተሰብ ወይም የአከባቢ ሰው የቱሪዝም መስህብ አካባቢ ጉብኝት ዘገባ በምላሽነት ይወሰዳል።

**ክፍለጊዜ: ስድስት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**ቅድመማንበብ ጥያቄዎች**

1. ፎቶውን አይተው ያውቁ እንደሆነ ይናገራሉ

2. በአካባቢያቸው ያሉ ነባር ቤቶችን (በጣም የቆዩ) ካሉ ይጠቁማሉ

3. ማንኛውም ስለምንባቡ የገመቱት በምላሽነት ይወሰዳል

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ዮርዳኖስ ሶፊያን ትጠይቃታለች ብለው የሚገምቱት ከቱሪዝም ጋር የተያያዘ ማንኛውም ምላሽ ተቀባይነት አለው

2. በአገራችን የሚገኙ ጥንታዊ ቦታዎችን ይገምታሉ

3. የንጉስ አባጅፋር ቤተመንግስት የት እንደሚገኝ ይገምታሉ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሁለት**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. ሀሰት 5 እውነት 6. ሀሰት

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ለ.** 1. ለ 2. ረ 3. መ 4. ሠ 5. ሀ 6. ሐ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ተግባር ሁለት**

ሰንጠረዡን የሚያሟሉት የሶፊያና የዮርዳኖስን ጥያቄና መልስ በራሳቸው አገላለጽ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ (የሶፊያንና የዮርዳኖስን ምልልስ መሰርተ ያደረጉ ጥያቄዎች ከተሰጡ ተቀባይነት ይኖረዋል።)

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**ተግባር ሶስት**

**ሀ.** ከምንባቡ የወጡ ዋና ዋና ሀሳቦች ተቀባይነት ያላቸው ምላሾች ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ለ.** ምንባቡን አቀላጥፈው ያነባሉ፤ ዋናውን ሀሳብ ይለያሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ተግባር አራት**

ማስታወሻውን አንብበው የተረዱትን ይገልጻሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ተግባር አምስት**

አንቀፁን ከአንቀጽ ባህሪያት አንጻር ይመዝኑታል፤ ለምላሻቸውም ምክንያት ይሰጣሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

1. ጉብኝት - ቅኝት/ምልከታ
2. ፓርክ - የእንስሳት መጠለያ
3. መልክዓ ምድር- የመሬት አቀማመጥ
4. የቱሪስት መስህቦች - የሚጎበኙ ስፍራዎች
5. ግጥምጥምነት - ተያያዥነት
6. አንድነት - ተመሳሳይነት
7. ምሉዕነት - ወጥነት/ያልተጓደለ
8. አንቀፅ - ሙሉ ሀሳብ የያዘ የጽሁፍ ክፍል .

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

1. ሙቀት - ቅዝቃዜ
2. ከተማ - ገጠር
3. ቁልቁለት- አቀበት/ዳገት
4. የዱር እንስሳት - የቤት እንስሳት
5. ሀዘንተኛ - ደስተኛ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

**መልመጃ አራት**

ሀ. ቅፅል ስምን የሚገልጽበትን ምሳሌዎች ይሰጣሉ፤

| | | |
|---|---|---|
| ትልቅ ስልክ | ብሩህ ሰማይ | ቆንጆ ቱሪስት |
| ፈጣን ጎዞ | ቀይ ቀሚስ | አስደሳች ጉብኝት |

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ስድስት**

1. ፈጣን
2. ሯጭ
3. ረጅም
4. ሠካራም
5. ደማቅ
6. ብልህ
7. ጠመዝማዛ
8. ተወርዋሪ
9. ገደላማ
10. ቡናማ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ.**

1. ሩቅ ሀገር
2. ጎበዝ ተማሪ
3. ደመናማ ቀን
4. ድፍርስ ውሃ
5. ነጭ መኪና

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

| **ቃላት** | **መልስ** |
|---|---|
| ሰነፍ | ቅጽል |
| ገለጸ | አይደለም |
| ትልቅ | ቅጽል |
| የዋህ | ቅጽል |
| ጨከነ | አይደለም |
| ደግ | ቅጽል |
| ረጅም | ቅጽል |

# ምዕራፍ ስድስት

# ስፖርት

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ተመሳሳይ መረጃዎችን በቃላቸው እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች እያንዳንዱን አንቀፅ አንብበው የምንባን ሀሳብ እንዲገልጹ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ ያተጋሉ
- ተማሪዎች ባለቤትና ግስን በማስማማት አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ያነቃቃሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- የቀረበ ምንባብ አዳምጠው ተመሳሳይ መረጃዎችን በቃላቸው ይናገራሉ፣
- እያንዳንዱን አንቀጽ አንብበው የምንባን ሀሳብ ይገልፃሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣
- የቃላት እውቀታቸውን ያዳብራሉ
- ባለቤትና ግስን በማስማማት አረፍተነገር ይመሰርታሉ

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ስለአገራችን ታዋቂ አትሌቶች የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- ተመሳሳይ ሀሳብን ለመናገር ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- የታዋቂ አትሌቶችንአስተዋፅኦ በተመለከተ መናገር
- ታዋቂ እግር ኳስ ተጫዋቾችንአስመልክቶ ንግግር ማድረግ
- አንቀጾችን አንብቦ የተረዱትን መናገር

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

## 2.4. መፃፍ

- ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅሞ መፃፍ
- ቅፅሎችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን መመስረት
- አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መፃፍ

### 2.5. ቃላት

- አውድን ተጠቅሞ የቃላትን ፍቺ ማወቅ
- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት

### 2.6. ሰዋስው

- ባለቤትና ግስን አስማምቶ አረፍተ ነገር መመስረት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበባቸውን እንዲያሻሽሉ በተግባር ማለማመድ
- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች የስፖርትን ጠቀሜታ እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ምሳሌ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት

## 4. የክፍል አደረጃጀት

1. ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
2. ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- ስለታዋቂ አትሌቶች ሚና አዳምጠው ሲናገሩ መከታተል
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽን እያስማሙ አረፍተነገሮች መመስረት መቻላቸውን ማጤን
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል፤

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

## ምዕራፍ ስድስት (ስፖርት)

### ክፍለጊዜ፡ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህንን ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ አዳምጠው ተመሳሳይ መረጃን በቃላቸው ይናገራሉ፤ አዳምጠው ከማዳመጥ በኋላ ተግባራትን ይሰራሉ፡፡

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር ዛሬ አዲስ ምዕራፍ የሚጀምርበት መርሀትምህርት ይከናወናል! በመሆኑም ተማሪዎችዎ ነቃ ብለውና ለትምህርቱም ተነሳሳኦት እያሳዩ ተሳታፊ ማድረግ ይገባል። ለዚህም የቀረቡትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲመልሱና (አትሌቶችን የተመለከተ) በፎቶ ግራፉ የተመለከቱትን ታዋቂ አትሌቶች ማንነት እንዲገምቱ ያድርጉ።

ቅድመማዳመጥ ተግባሩ ሲጠናቀቅ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን አንብበው እንዲረዱና እያዳመጡ እንዲመልሱ አስቀድመው መመሪያ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ዝግጁ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ምንባቡን በማንበብ ያቅርቡላቸው። ታዲያ የክፍል ተማሪዎችዎ ያሉበትን ደረጃ ከግምት ያስገቡ።

## የኢትዮጵያ አትሌቶች

ኢትዮጵያ በተዋቂ አትሌቶቿ አማካይነት በአትሌቲክስ ስፖርት ስሟ ተደጋግሞ ይነሳል። ኢትዮጵያ የታወቀችበት የአትሌቲክስ ውድድር ሩጫ ነው። በዚህ የሩጫ ዘርፍም አይረሴ ጀግኖችን በተለያዩ ጊዜያት አፍርታለች። ከቀድሞዎቹ እነአበበ ቢቂላ ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩፅ ይፍጠርና በበላይነህ ዲንሳሞ ሲነሱ፣ በኋላ ላይ ደግሞ እንደነፋጡማ ሮባ፣ ብርሃኔ አደሬ፣ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ቀነኒሳ በቀለ መሠረት ደፋርና የዲባባ ልጆች ወዘተ ተከስተዋል። ከነዚህ መካከል ለዛሬ ስለኃይሌ ገብረስላሴንና ደራርቱ ቱሉን በጥቂቱ እንመልከታቸው።

ኃይሌ ገብረስላሴ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ድንቅዬ አትሌቶች አንዱ ነው። ኃይሌ ገብረስላሴ በሩጫ ዘመኑ በ10 ሺ.ሀ፣ በ5 ሺ.ሀ፣ በግማሽ ማራቶንና በማራቶን፣ እንዲሁም በሌሎች የሩጫ አይነቶች ከአስራ አንድ በላይ የአለም ክብረወሰኖችን ሰብሯል። ኃይሌ ከተፈጥሯዊ ጥንካሬው ባሻገር ልምምዶችን ሳይሰለች መስራቱ ውጤታማ አድርጎታል። ኃይሌ ሁለት ጊዜ የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆኗል፤ በሲድኒና በአትላንታ ኦሎምፒክ።

ሌላዋ የአትሌቲክስ ውድድር ቁንጮ ደራርቱ ቱሉ ናት። ደራርቱ በአስደናቂ ብልሃት፣ ጽናት እና በጠንካራ ልምምድ ከታጀበው ውብ አሯሯጧ ጋር ተወዳዳሪዎቿን የማሸነፍ ብቃት ያላት ጀግና አትሌት ናት። ዓለማቀፋዊ ድሏን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስመዘገበችው በመም ውድድር ነው። ይህንንም በቡልጋሪያዋ ኘሎቭዴቭ ከተማ በተካሄደው የተዳጊ ወጣቶች የዓለም አትሌቲክስ ሸምፒዮና በ10ሺ.ሀ አሸናፊ ሆና አሳክታዋለች። እንዲሁም በቶክዮ ጃፓን በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በግማሽ ፍጻሜ 10ሺ.ሀ ሜትር ውድድር አንደኛ ወጥታለች። በርቀቱም የኢትዮጵያ ክብረወሰንን በመስበር የዓለም አቀፍ የሴቶች ረጅም ርቀት ሩጫ ትኩረት ወደ እሷ እንዲዞር አድርጋለች። ደራርቱ ባጠቃላይ በሶስት የ10ሺ.ሀ ሜትር ውድድሮች አሸንፋለች። ከባርሴሎናው ኦሎምፒክ መጀመር ጥቂት ቀደም ብሎ በተካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፑዮና ላይም ርቀቱን ክብረወሰን በመስበር ጭምር አሸንፋ የወርቅ ማዳሊያ አጥልቃለች።

## ክፍለ ጊዜ፡ሁለት

## መልመጃ አንድ

ሀ. መምህር በዚህ የመልመጃ አንድ ክፍል እውነት/ሐሰት ጥያቄዎች ቀርበዋል በተደመጠው ምንባብ መሰረት ተማሪዎች ፅፈው እንዲመልሷቸው ያድርጉ። መልሳቸውንም ከሌላ ተማሪ ጋር ያነጻጽሩ።

ለ. እባክዎ መምህር ይህንንም የማዛመድ ክንውን ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ ጽፈው በተነበበው ምንባብ መሰረት እንዲመልሱ ያድርጉ፤ ሲጨርሱም እርማት አድርገው ምጋቤ ምላሽ ይስጡበት።

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

ሐ.ይህ የመልመጃ ክፍልም ልክ ከላይ እንደቀረቡት ሁለቱ ደብተር ላይ በመጻፍ የሚመለስ ነው። እባክዎ መምህር ያንን እንዲያደርጉ ለተማሪዎችዎ ያሳውቋቸው። በተጨማሪም ተማሪዎችዎ ይህንን መልመጃ እንዲሰሩ የማዳመጥ ፅሁፉን አንድ ጊዜ ያንበብቡላቸው፤

ተማሪዎቹም ማስታወሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ይምከሯቸው፡፡ ከዚያም የምርጫ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያግዟቸው፤ ሲጨርሱም መልሶቻቸውን ለቡድን አጋሮቻቸው አቅርበው ያስተያዩ።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

ሠ. መምህር ተማሪዎችዎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ከሰጡ በኋላ በቃላቱ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያትጓቸው። አፈጻጸማቸውንም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረምና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ይመዝኑ።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ይህንን ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በጥሞና ከተከታተሉ በኋላ ከክፍል ውጪ መረጃ አሰባስበውና አጠናቅረው የቃል ዘገባ ማቅረብ ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል

### ተግባር አንድ

መምህር ይህ ተግባር ለተማሪዎቹ አስቀድሞ የሚሰጣቸው ሲሆን ስለሁለት ታዋቂ የሀገራችን አትሌቶች (በምንባቡ ከተካተቱ ውጪ) ቤተሰባቸውን ወይም የአካባቢ ሰው ጠይቀው በመምጣት የቃል ዘገባ የሚያቀርቡበት ነው። በአቅርቦት ወቅትም ለንግግር ችሎታቸው ትኩረት ሰጥተው (የሀሳብ ፍሰት እና ተጨባጭነት) እያንዳንዳቸውን ይመዝኗቸው። ድጋፍ ለሚያሻቸውም ይቅረብላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

### ተግባር ሁለት

ይህ ከተግባር አንድ ጋር ተመሳሳይ አካሄድን የሚከተል ነው፤ በዚሁ መሰረት ይሰራ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ይህንን ንኡስ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ አቀላጥፈው ማንበብ ይችላሉ፤ ከምንባብ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችንም ይሰራሉ።

## ምንባብ አንድ (ሴት አያቴ)

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንቀጾች ተከፋፍለው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማንበብ አቀላጥፎ ማንበብን እንዲለማመዱ ያድርጉ። አፈጻጸማቸውንም በተናጠል ይመዝኑ፤ ድግፍ (ለሚዘገዩ)ና ማበልጸጊያ(ለሚፈጥኑ) ለሚያሻቸውም እንደሁኔታው ያቅርቡላቸው።

### ክፍለ ጊዜ፡ ስምንት

## ምንባብ ሁለት (ስፖርት)

### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

ሦስቱን ቅድመማንበብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፤ የቀረቡትን ቃላት ፍቺ በመጠየቅ ያስገምቷቸው። ዝግጁ ሲሆኑም **አካላዊ እንቅስቃሴ** በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በዝምታ እንዲያነቡት ይዘዟቸው፤ አፈጻጸሙንም እየተዘዋወሩ ይቃኙ።

### ክፍለ ጊዜ፡ ዘጠኝ

### መልመጃ ሁለት

ሀ. እውነት/ ሀሰት ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት በቃል እንዲመልሱ ያትጓቸው፤ ለመልሶቹ እርግጠኛ ስለመሆናቸው ወደ ምንባቡ እየተመለሱ እንዲያዩም ጥቆማ ይስጧቸው።

ለ. በዚህ ክፍል የቀረቡትን ጥያቄዎች መጻፍን በዚያው ይለማመዱ ዘንድ ደብተራቸው ላይ ጽፈው ይስሯው። እንደአፈጻጸማቸው ቅደም ተከተልም እርማትና ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

### ክፍለ ጊዜ፡ አስር

ሐ. እባክዎ መምህር ይህንን የማዛመድ ተግባር ተማሪዎችዎ ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ሀረጋቱንም ከፍቺዎቻቸው ጋር ያዛምዱ። መልሶቻቸውን በቡድን ወይም በጥንድ አስተያይተው ከጨረሱ በኋላ ሀረጋቱን በመጠቀም የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱባቸው ያበረታቷቸው፤ አፈጻጸማቸውንም ይመዝኑ።

### ክፍለ ጊዜ፡ አስራ አንድ

መ. መምህር ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በውይይት ከሰሩ በኋላ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

### ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ ንኡስ ትምህርት ክፍል መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ይችላሉ፤ ቃላትን በአግባቡ ተጠቅመው አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

### መልመጃ ሶስት

በዚህ ምልመጃ 'ሀ' ስር ያሉት ጥያቄዎች በተማሪዎቹ ደብተር ላይ ተፅፈው የሚሰሩ ናቸው (በዚያው መጻፍ እንዲለማመዱ)። የሰሩትን ጥንድ ጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲያነጻጽሩ ያትጓቸው፤ ሲጨርሱም በጋራ ስሯቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

ለ· በዚህ ክፍል ቃላት ቀርበዋል። ተማሪዎቹ የቃላቱን ፍቺ አስቀድመው በመስጠት ከቡድን አጋሮቻቸው አነጻጽረው በፍቺዎቹ ላይ ከተስማሙ በኋላ አረፍተነገሮች ይመሰርቱባቸዋል። የመሰረቷቸውን አረፍተነገሮችም መልሰው ከቡድን አጋሮቻቸው ጋር ያስተያያሉ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ይህንን የመጻፍ ትምህርት ንኡስ ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ቃላት/ሀረጋት በመጠቀም አረፍተነገር መመስረት ይችላሉ፣ ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸውን አረፍተነገሮች አስተካክለው ያዋቅራሉ።

### መልመጃ አራት

ሀ. ተማሪዎች በመጀመሪያ ቃላቱን አጥንተው የትኞቹን በትክክል እንዲሚያውቋቸው ይለዩ። በመቀጠል የማያውቋቸውን በተመለከተ ከጎናቸው ካሉ ተማሪዎች ጋር

ይነጋገሩ፣ ከዚያም ሁሉንም ቃላት በመጠቀም አረፍተነገሮች መስርተው ተለዋውጠው ይተራረሙ። በመጨረሻም ቃላቱን እንደክፍል አንስታችሁ ተወያዩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

ለ· በዚህ ክፍል ያሉ አረፍተነገሮችን ደብተራቸው ላይ ይጻፉ፣ ለመልሱም አንዳንድ መስመር ትተው ይለፉ። ጽፈው ሲጨርሱ እያስተካከሉ በተተወው ቦታ ላይ ያስፍሩ። ሲጨርሱም እርስዎ እርማት አድርገው ምጋቤ ምላሽ ይስጠዋቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

መምህር የዛሬው ክፍለጊዜ የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት መሆኑን በማስተዋወቅ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ፅፈው እንዲሰሯቸው ይዘዟቸው። ሲጨርሱም በቡድን ሆነው መልሶቻቸውን ተራ በተራ ያነጻጽሩ፣ ስንቶቹ መልሶች እንደተመሳሰሉም ጠይቋቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ይህ ክፍለጊዜ ስህተት ያለባቸው አረፍተነገሮች እየተስተካከሉ እዲጻፉ የሚያስችል ተግባር የተካተተበት ነው። እባክዎ መምህር ምሳሌውን ሰሌዳ ላይ ጽፈው እያሳተፉ ይስሩት። በመቀጠልም የቀረቡትን አረፍተነገሮች ጽፈው እንዲመልሷቸው ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

በትእዛዙ መሰረት ይሰራ፣ መልሶቻቸውንም ያነፃፅሩ። ጊዜው ከፈቀደ እርስዎም ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው፣ የእርስዎ እርማት መስጠት የመማር ተነሳስአታቸው እንዲጨምርና ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል።

## የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለ ጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ- ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት አድርገው ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት መልስ ከይዘቱ እስካወጣ ድረስ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ሁለት**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1. እውነት 2. ሐሰት 3. ሐሰት 4. ሀሰት 5. እውነት

**ለ.** 1. ሠ 2. መ 3. ሐ 4. ሀ 5. ለ

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ሐ.** 1. መ 2. ሀ 3. ለ 4. ሀ 5. ሐ 6. መ 7. ለ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ሠ.** ተጠቃሽ - ስማቸው የሚነሳ፣

ትኩረት - አጽንዖት፣

ገናና- ዝነኛ፣

ውድድር - ፉክክር፣

ማጀብ - ማገዝ/፣

ውብ - ቆንጆ/ያማረ፣

ቀድሞ - ድሮ፣

ብቃት - ችሎታ፣

ድንቅ - ገራሚ (ተማሪዎቹ የሚሰጡት ፍቺ አማራጭም ተቀባይነት አለው)

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ትምህርት ሁለት፡መናገር**

**ተግባር አንድ**

ስለአትሌቶቹ ጠይቀው በመምጣት የዘገቡት ማንኛውም መልስ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሁለት**

ስለእግር ኳስ ተጫዋቾቹ ተማሪዎቹ የሚዘግቡት ማንኛውም ተጨባጭ ምላሽ

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**ምንባብ አንድ**

አቀላጥፎ ማንበብን በተግባር መለማመድ

**ክፍለ ጊዜ፡ ስምንት**

**የቅድመማበብ ጥያቄዎች**

ተማሪዎቹ ለሶስቱ ጥያቄዎች የሚሰጧቸው ከጥያቄዎቹ ይዘቶች ጋር የተዛመዱ ማናቸውም ቃላዊ ምላሾች እና ለቃላቱ የሚሰጡት ግምታዊ ምላሽ። (**አካል ብቃት** - የሰውነት ጥንካሬ፣ **ምርታማ** - ውጤታማ፣ **እንዲወገዱ** - እንዲጠፉ፣ **የሰለጠኑ** - የተማሩ/የበቁ)

**ክፍለ ጊዜ፡ ዘጠኝ**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. እውነት

**ለ.** 1. ሀ 2. ሐ 3. ሀ 4. ለ 5. መ

**ክፍለ ጊዜ፡ አስር**

**ሐ.** 1. ሠ 2. ሐ 3. ሀ 4. ለ 5. መ

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ አንድ**

**መ.** ከ1-4 ማናቸውም ምንባቡን መሰረት ያደረጉና በውይይቱ ወቅት የተነሱ ሀሳቦች

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ.** 1. ለ 2. መ 3. ለ 4. ሀ 5. ሐ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ለ. ድል - ማሸነፍ፣ አሸናፊ - ድል አድራጊ፣ ነጥብ - ውጤት፣ በረኛ - ግብ ጠባቂ፣ ደጋፊ - ቲፎዞ፣ ተሸናፊ - ድል ተደራጊ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ትምህርት አምስት፡ መጻፍ**

**መልመጃ አራት**

**ሀ.** ማናቸውም ሰዋስዋዊ ህግን የጠበቁና የተሰጡትን ቃላት የተጠቀሙ ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮች ምላሽ ይሆናሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ለ.** 1. እኔና አንቺ ጥናታችንን እናጥና።

2. ደራርቱ በፍጥነት ወደ ቤቷ ሄደች።

3. አጎቴ መጣ።

4. ሰውዬው ብርጭቆውን ሰበረ።

5. እኔ አገሬን እወዳለሁ።

6. ልጆቹ ኳስ እየተጫወቱ ነው።

7. ሁለት አትሌቶች ዛሬ ይመጣሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

1. እያደረጉ/እየሰሩ 2. እበላለሁ/በልቻለሁ 3. ናቸው 4. መጠየቅ

5. ትወጣለች/ትላቀቃለች 6. ዘመርን/እንዘምራለን

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

1. እህቴ ደብዳቤ ፃፈ ለኔ። *እህቴ ለኔ ደብዳቤ ፃፈችልኝ።*
   *(የባለቤትና የግስ አለመስማማት)*
2. አበበ ስልክ ተደወለልኝ። *አበበ ስልክ ደወለልኝ።*
   *(የባለቤትና የግስ አለመስማማት)*
3. የተሰጡት ክፍለጊዜዎች አለቀ። *የተሰጡት ክፍለጊዜዎች አለቁ።*
   *(የባለቤትና የግስ አለመስማማት)*
4. ለሊሴና አሰለፈች እህትማማቾች ነው። *ለሊሴና አሰለፈች እህትማማቾች ናቸው።*
   *(የባለቤትና የግስ አለመስማማት)*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

1. ለ 2. ሠ 3. ሰ 4. ሀ 5. መ 6. ሐ

# ምዕራፍ ሰባት

# ውሃ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች በኢመደበኛ ሁኔታ ውስጥ በሚደረገው ሚና ጨዋታ አዳምጠው እንዲሳተፉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች አዳምጠው በዝርዝር አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ቅድመዝግጅት አድርገው እንዲከራከሩ ይቀሰቅሳሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የውሃ ጥቅምን የተመለከተ መዝሙር አዳምጠው ስለውሃ ጥቅም እንዲፅፉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ግሶች ተጠቅመው አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ያነቃቃሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ ተማሪዎች፡-**

- በኢመደበኛ ሁኔታ ውስጥ በሚደረገው ሚና ጨወታ አዳምጠው ይሳተፋሉ፤
- አዳምጠው በዝርዝር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤
- የየራሳችሁን የተሟሉ አረፍተነገሮች ይፅፋሉ፤
- ተውሳከ ግስን ተጠቅመው አረፍተነገሮችንይመሰርታሉ፤
- ስለ ውሃ ጥቅም የቀረበውን መዝሙር አዳምጠው ስለ ውሃ ጥቅም ይፅፋሉ፤
- በተሰጠው ርዕስ ላይ ክርክር ያደርጋሉ፤
- የተሰጧቸውን ግሶች ተጠቅመው የተሟሉ አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- በሚና ጨዋታ ለመሳተፍ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በዝርዝር ለመመለስ ማዳመጥ
- በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- ሚና ጨዋታ መጫወት
- ቅድመዝግጅት አድርጎ በክርክር መሳተፍ
- በቡድን ውይይት መሳተፍ
- መዝሙር መዘመር

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን በዝርዝር ለመመለስ ማንበብ

## 2.4. መፃፍ

- ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅሞ መፃፍ
- ተውሳከ ግሶችን በአረፍተነገር ምስረታ ወቅት መጠቀም

- ግሶችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን መመስረት
- የተሟሉ አረፍተነገሮችን መፃፍ

### 2.5. ቃላት

- ተውሳከ ግሶችን መለየትና መጠቀም
- አውድን ተጠቅሞ የቃላትን ፍቺ ማወቅ
- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት

### 2.6. ሰዋስው

- ተውሳከግስን በአረፍተነገር ውስጥ በተገቢው ቦታ መጠቀም
- ግስን በአረፍተነገር ምስረታ መጠቀም

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- የሚና ጨዋታ
- ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበባቸውን እንዲያሻሽሉ በተግባር ማለማመድ
- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን እያነበቡ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች የውሃን ጠቀሜታ በመግለጽ በውይይት እንዲሳተፉ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ምሳሌ ማቅረብ፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት
- ክርክርን እንደመነጋገሪያ ብልሃት መጠቀም
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድን መከተል

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በሚና ጨዋታ እየተሳተፉ ሲሰሩ ምልከታ ማድረግ
- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- ስለውሃ ጥቅም አዳምጠው ሲናገሩ መከታተል
- በክርክር ተሳትፏቸው ወቅት የሀሳብ አቀራረባቸውንና ማስረጃ አጠቃቀሳቸውን መመርመር

- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- ተውሳከ ግሶችንና ግሶችን በአግባቡ መመስረታቸውን ማረጋገጥ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

## ምዕራፍ ሰባት (ውሃ)

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህንን ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ አዳምጠው በሚና ጫዋታ ይሳተፋሉ፤ በክርክር ወቅት አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር ወደማንበቡ ከመሄድዎ በፊት ሁለቱን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ልምዳቸውን ወደ ማዳመጥ ተግባሩ እንዲሳቡ ይጠይቋቸው፤ የተወሰኑ ተማሪዎችንም ለመልሱ ያሳትፉ ወይም በአማራጭነት ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ይንገሯቸው። በመቀጠል ወደፊት በምንባቡ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውንና ትርጉማቸውን እንዲገምቱ የቀረቡ ቃላትን ፍቺ ይስጡ። ትክክለኛ ባይሆንም የሰጡት ፍቺ ለጊዜው ይያዝላቸዋል። በምንባቡ መጨረሻ ላይ ግን ይረጋገጣል።

እባክዎ መምህር አሁን ምንባቡን ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ማንበብ ይጀምሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ሦስቱን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች አስቀድመው እንዲያነቧቸውና በማዳመጥ ጊዜ እንዲመልሷቸው ያበረታቷቸው። ንባብዎን ቆም እያደረጉም ምላሻቸውን ይቀበሏቸው።

ምንባቡ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ይነበብላቸው።

**የውሃ ጥቅም**

የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሰው ልጅ የውሃ ፍላጎትም እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በምድራችን ያለው ውሃ በቤት ውስጥ እና በቤት ውጪ በሚሰጠው አገልግሎት መሠረት ይወሰናል፡፡ በከተማና በገጠር አከባቢዎች ውሃ ምግብ ለማዘጋጀት፣ ለመጠጥ፣ ለአከባቢ እና ለመፀዳጃ ቤት ንፅህና አገልግሎት ይውላል፡፡

የውሃ ሌላው አገልግሎቱ ለመሥኖ ስራ መዋሉ ነው፡፡ ውሃን ገድቦ በመስኖ መጠቀም በአመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ለማምረት ያስችላል፡፡ በዚህም ለምግብ ፍጆታና ለገበያ የሚውሉ ምርቶች በሰፊው ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ በአጭር ጊዜ ምርት የሚሰጡ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የጥራጥሬ ወዘተ ምርቶችን አምርቶ መጠቀም ይቻላል፡፡

ውሃ በቱሪዝም ሀብትነትም የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡ አሁን አሁን የሰው ልጆች ከውሃ ጋር የተያያዙ መዝናኛዎችን ማዘውተር ጀምረዋል፡፡ በዚህም ረጅም ርቀቶችን በመጓዝ የባህርና ውቅያኖስ ዳርቻዎችን ያስሳሉ፤ ሀይቆችንና ወንዞችን ይጎበኛሉ። ከውሃ ጋር የተያያዙ ውድድሮችም የጎብኚዎች ቁጥር በየጊዜው እንዲጨምር አድርገዋል። የጀልባ ቀዘፋዎች፣ የውሃ ላይ ጨዋታዎች፣ የዋና ውድድሮች ወዘተ ለዚህ የሚጠቀሱ ናቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

**የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

መምህር ከተማሪዎችዎ ጋር ሆነው በማዳመጥ ተግባር ወቅት የቀረበውን ምንባብ ታሪክ በቃል ከልሱት፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው (ለምሳሌ ታሪኩን እረስተውት ከሆነ)። በመቀጠል የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎቹን ባዳመጡት ታሪክ መሰረት በቃል ይመልሱ፤ አንዳቸው ሲመልሱ ሌሎቹ እንዲያረጋግጡ ያድርጉ።

ከእውነት/ሐሰቱ ቃላዊ ምላሽ በኋላ በ ‘ለ’ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ደብተራቸው ላይ በማስፈር በፅሑፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው። ምላሻቸውንም በቡድን በቡድን እየሆኑ ያነጻጽሩ።

### ክፍለጊዜ፡ ሦስት

ሐ. በዚህ ንኡስ የመልመጃ ክፍል ተማሪዎች ቃላቱን ደብተራቸው ላይ ፅፈው ከተሰጡት አማራጭ ፍቺዎች እንዲያዛምዱ ያበረታቷቸው፤ ከዚህ ቀጥለውም የሰጡትን ምላሽ በተመለከተ ከጓደኞቻቸው ጋር በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ይወያዩበት። ያልተስማሙበት ካለ ለክፍሉ ያቅርቡ፤ በመጨረሻ በነዚሁ ቃላት አረፍተነገሮች ጽፋ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያትጓቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ይህንን የመናገር ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች መረጃ አሰባስበውና አደራጅተው የቃል ዘገባ ማቅረብ ይችላሉ፣ በክርክር ይሳተፋሉ።

### ተግባር አንድ

ውሃና አጠቃቀሙን እንዲሁም ንፅሕናው ተጠብቆ በዘላቂነት ጥቅም እንዲሰጥ ምን መደረግ እንዳለበት አስመልክቶ ከአካባቢያቸው መረጃ አጠናቅረው እንዲመጡ በማሳሰብና ውይይት በማድረግ የቃል ዘገባ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፤ ተግባሩም አስቀድሞ ይሰጣቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አምስት

ሀ. ተማሪዎች ለክፍለጊዜው ተዘጋጅተው የቀረቡ ስዕሎችን አጥንተውና በስዕሎቹ ላይ ያስተዋሏቸውን ተግባራት በተመለከተ አረፍተነገሮች ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያነባሉ። ስለሆነም መምህር በዚሁ መሰረት ተማሪዎችዎ እንዲሰሩ ይንገሯቸው። በቡድን ሆነውም ይነጋገሩ፤ እርስዎም እየተዘዋወሩ ድጋፍ ያድርጉላቸው፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ይመዝኑ።

### ክፍለጊዜ፡ ስድስት

ለ. እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ክርክር ማድረግን በተግባር እንዲለማመዱ ለማድረግ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ለዚህም በሁለት የተከፈለ የተከራካሪዎች ቡድን ይዋቀር፤ ሰዓት ያዢና ክርክሩን የሚዳኙ ዳኞችም ይመረጡ፣ ፀሐፊም ይኑር፤ በመቀጠል

ለክርክር የቀረበውን ሀሳብ ደጋፊና ተቃዋሚ በመሆን የመከራከሪያ ነጥቦችን በየቡድናቸው ሆነው ተከራካሪዎቹ ያሰናዱ፤ በማስታወሻቸውም ላይ ያስፍሩ። በመቀጠል የክርክርን መርሆች ተከትለው ክፍል ውስጥ ይተግብሩ፤ በክርክር ወቅት ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው *(የሌላን ሀሳብ ማክበር፣ ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም፣ ንግግርን በምሳሌና ማስረጃ እያጠናከሩ ማክበር፣ ተራ እየጠበቁ መናገር፣ ድምፅና የፊት ገፅታን እንደየሁኔታው እየቀያየሩ መጠቀም፣ ዳኞችና ተሳታፊዎችን ማክበር፣ ለውሳኔ መገዛት...)፤* እርስዎ ምልከታ በማድረግ አካሄዱን ይመዝኑ፤ ወደፊት መሻሻል ስላለባቸው ጉዳዮች መጨረሻ ላይ ያንሱ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

ሐ.መዝሙሩን ከተማሪዎችዎ ጋር በተደጋጋሚ በመለማመድ ክፍል ውስጥ ዘምሩት። ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው መዘመራቸውን ሲያረጋግጡም እርስዎ ተሳትፎዎን ቀንሱ። ተማሪዎችዎ ደጋግመው ይዘምሩት ይደሰቱበት!

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ማንበብ የሚለውን ንኡስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎቹ ከተከታተሉ በኋላ የሚቀርቡላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተረድተው መስራት ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

መምህር እባክዎ ቅድመማንበብ ጥያቄዎችን አሳታፊ በሆነ መንገድ ተማሪዎችዎ በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፤ ተሞክሯቸውንም ከሚነበበው ምንባብ ጋርእንዲያዛምዱ ያድርጉ።

ሲጨርሱም ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ይጋብዟቸው። እያነበቡም የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## መልመጃ ሶስት

መምህር ያለፈውን ክፍለጊዜ ምንባብ ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን በቃል ከልሱት። ይህንንም ተከትሎ የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያትጓቸው፤ አብዛኛው ተማሪ በመመለስ ወይም የተመለሱትን በማረጋገጥ እንዲሳተፍ ያበረታቱ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

ለ. የእውነት/ሐሰቱ ጥያቄዎች ሲጠናቀቁ በ ለ ስር ያለውን የማዛመድ ክንውን ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉና እንዲያዛምዱ ያበረታቱ። ሲጨርሱም መልሶቻቸውን በጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ በመነጋገር እንዲያመሳክሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

ሐ. በዚህ ንኡስ የመልመጃ ክፍል ተማሪዎች ለጥያቄዎቹ ከቀረቡት አማራጮች መካከል እየመረጡ እንዲመልሱ ይጠበቃል። ስለሆነም ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ በመጻፍ ይስሯቸው (መጻፍን በዚያው እንዲለማመዱ) ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

ከዚህ ንኡስ ትምህርት ይዘት ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የተዛቡ አረፍተነገሮችን አስተካክለው መጻፍ ይችላሉ፤ የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት ይችላሉ፤ በተሰጧቸው ቃላት አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

## መልመጃ አራት

ሀ. በዚህ መልመጃ የመጀመሪያ ክፍል ተማሪዎች ተዘበራርቀው የተሰጧቸውን አረፍተነገሮች አስተካክለው ይፅፋሉ። እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ አረፍተነገሮቹን ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲሰሯው ይንገሯቸው። ሲጨርሱም ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት ይስጧቸው። ሲጨርሱም አረፍተነገሮቹ እንዴት እንደተስተካከሉ እያሳተፉ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳዩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ለ.መምህር እባክዎን ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን በደብተራቸው ላይ ጽፈው ተገቢ ናቸው ያሏቸውን ሀረጎች እየመረጡ እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

ሐ. ለአረፍተነገር መመስረቻነት የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም ተማሪዎቹ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ቃላትን አውዱን በመረዳት መጠቀም ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

### መልመጃ አምስት

በመልመጃ አምስት ተማሪዎች በየአረፍተነገሩ ውስጥ ያሉ አውዶችን በመቃኘት የተሰጧቸውን ቃላት ያሟላሉ። ስለሆነም መምህር ለዚሁ ተግባር ይሆን ዘንድ አስቀድመው ጥያቄዎቹን ደብተራቸው እንዲፅፉና እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም በጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ እንዲያነጻጽሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። በመጨረሻም እንደክፍል ተነጋገሩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ንኡስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አረፍተነገሮችን ያሟላሉ፣ ግሶችንም ለይተው መጠቀም ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

### መልመጃ ስድስት

ሀ. እባክዎ መምህር ተማሪዎች አረፍተነገሮችን በተገቢው ቃል እያሟሉ እዲፅፉ የሚያስችለውን ይህን መልመጃ ምሳሌዎችን አቅርበው በመስራት አስጀምሯቸው። በመቀጠል ተማሪዎቹ ደብተሮቻቸው ላይ ፅፈው እንዲመልሷቸው ያትጓቸው።

ሲያጠናቅቁም በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡባቸውና ምላሾቻቸውን እንዲያረጋግጡ ይሁን። ልዩነት የታየበት ጥያቄ ካለም ቡድኑ ለክፍሉ አቅርቦ በጋራ አቋም እንዲያዝበት ይሁን።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

ለ.ይህ ክፍለጊዜ ለተማሪዎች ሌላ አረፍተነገሮችን ጽፎ የመለማመጃ እድል የሚፈጥር ነው። ስለሆነም እባክዎ ተማሪዎቹ ወቅታዊና የቅርባቸው የሆኑ ነገሮችን እየገለፁ በተሰጧቸው ቃላት አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው። እየተዘዋወሩም አፈጻጸማቸውን በመመልከት እርማትና ተገቢ የሆነ እገዛና ማበረታቻ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ሐ.መምህር ተማሪዎች እአደጋገሙ እንዲፅፉ መደረጉ የመፃፍ ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ከመርዳቱም በላይ ሀሳባቸውን ስርዓት አስይዘው በወጉ እንዲገልጹም ያስችላቸዋል። ስለሆንም እንዳይሰለቹብን በማበረታታትና ማነቃቂያዎችን በማቅረብ (ለምሳሌ እንቆቅልሽ፣ ተረት፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ወዘተን በመጠቀም) የማስተማር ሂደቱን ሳቢና አስደሳች ማድረግ ይጠበቅብናል። ማነቃቃትን ከከወኑ በኋላ ተማሪዎች ከቀረቡት ግሶች እየመረጡ አረፍተነገሮቹን እንዲያሚሉ ይጠይቋቸው። መጀመሪያም በግል፣ ቀጥሎ በጥንድና ከዚያም በቡድን መልሶቻቸውን ያነጻጽሩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ.የግስ ገላጮች ተውሳከ ግስ በመባል ይታወቃሉ። ተውሳከግሶች በግሱ የተገለጸውን ሁነት ወይም ድርጊት መቼ፣ እንዴት፣ የት፣ ስንት ጊዜ ወዘተ እንደተፈጸመ የሚጠቁሙን ናቸው። እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ከቀረቡላቸው አረፍተነገሮች ውስጥ የግስ ገላጭ (ተውሳከ ግሶች) የሆኑትን ለይተው እንዲያሰምሩባቸው ይጠይቋቸው። ሲጨርሱም በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው የግስ ገላጮቹ ለምን ተግባር በአረፍተነገሮቹ ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋሉ እንዲነጋገሩ ያድርጉ። ጊዜው ከፈቀደልዎትም (ክፍለጊዜው ካላለቀ) ተውሳከ ግሶችን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው።

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከወንዝ፣ ከምንጭ፣ ከጉድጓድ፣ ከቧንቧ ወይም ከዝናብ እያሉ ሊመልሱ ይችላሉ
2. ምግብ ለማብሰያነት፣ ልብስ ለማጠብ፣ ንጽህናን ለመጠበቅ፣ ለእርሻ ስራ ወዘተ
3. ተማሪዎቹ የገመቱትን ይገምቱ፤ መልሳቸው ልክ/ስህተት አይባልም፡፡ ነገር ግን ቀጥሎ የቀረቡትን ሊገምቱ ይችላሉ፡፡

**አገልግሎት** - ጠቀሜታ፣

**ፍጆታ** - ጥቅም ላይ የሚውለው መጠን

**ቱሪዝም** - የጉብኝት አገልግሎት ማቅረብ፣

**ማዘውተር** - መደጋገም፣

**ጎብኚ** - ቱሪስት

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ንፅህና አገልግሎት 2. መስኖ 3. አትክልት፣ ፍራፍሬና ጥራጥሬዎች

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. ሀሰት 5. እውነት

**ለ.** ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው መልሶች ከይዘተነገሩ እስካልወጡና ምክንያታዊ እስከሆኑ ድረስ ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**ሐ.** 1. ሐ 2. ሀ 3. ለ 4. መ 5. ሠ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተግባር አንድ**

በትዕዛዙ መሰረት የተጠናቀረውን መረጃ በተመለከተ የተሰናዳ ማንኛውም ምላሽ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

ስዕሎችን መሰረት አድርገው የተነሱ ማናቸውም ሀሳቦች ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ለ.** በክርክሩ ወቅት እንዲሟሉ የሚገባቸውን ሁሉ አሟልተው ከተገኙ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ሐ.** ግጥሙን አጥንቶ፣ ተለማምዶ መዘመር

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ቅድመንባብ ጥያቄዎች

የተለያዩ መልሶች፣ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ውሃን ለምን ለምን ጥቅሞች እንደሚያውሉ ከግምት በማስገባት የሚቀርብ ማንኛውም ምላሽ (ከ1-3 ላሉ ጥያቄዎች)

**ለምሳሌ** 1.ለመጠጥ፣ ምግብ ለማብሰል፣ ለእርሻ፣ ለንፅህና ወዘተ

2. ከከርሰ ምድር፣ ከወንዝ፣ ከምንጭ፣ ከዝናብ ወዘተ

3. መኖር የምንችል አይመስልም

### የማንበብ ጊዜ ጥያቅዎች

- ሰዎች ውሃን ለመጠጥ፣ የግል ንፅህናን ለመጠበቅ፣ ምግብ ለማብሰል እና ልብስና ቁሳቁስን ለማጠቢያነት ይገለገሉበታል

- ምግብና ማዕድናት በደም ውስጥ ያዘዋውራል፣ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ከሰውነታችን ያስወግዳል፣ የሰውነት ፈሳሽ ሚዛን ይጠብቃል እንዲሁም የሰውነት ሙቀትን ይቆጣጠራል

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ.** 1. እውነት 2. ሀሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሀሰት

**ለ.** 1. ሠ 2. ሀ 3. ሐ 4. ለ 5. መ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ሐ.** 1. ለ 2. ሐ 3.መ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አራት፡ መፃፍ**

**መልመጃ አራት**

**ሀ.** 1. የተበከለ ውሃ ለጤና ጠንቅ ነው።

2. የወንዝን ውሃ አፍልተንና አቀዝቅዘን መጠጣት አለብን።

3. የምንጭ ውሃን አጣርተን መጠጣት አለብን።

4. ጉደር ወንዝ የአባይ ገባር ወንዝ ነው።

5. የባሮ ወንዝ ለመጓጓዣ አገልግሎት ይውላል።

6. የአዋሽ ወንዝ መነሻ ደንዲ ወረዳ ነው።

7. ወንጪ ሐይቅ በበርካታ ቱሪስቶች የሚጎበኝ ውብ ስፍራ ነው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ.** 1. እንዲጨምር ይረዳል 2. ማመንጨት ይቻላል 3. በክረምት ወቅት ነው

4. ህይወት ነው 5. በክረምት ወቅት ይሞላሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ሐ.** የተሰጡትን ቃላት ተጠቅመው ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮች ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ አራት**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ አምስት**

1. ላሚቷን 2. ዳቦ 3. መንገድ 4. ቆሎ 5. መሬቱን 6. ከብት 7. አጠበ 8. ገጠመ

**ክፍለጊዜ አስራ አምስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ.** 1. ሄደ 2. ተጫወቱ 3. በልተዋል 4. ይፈተናል 5. ነኝ

**ለ.** የተሰጡትን ቃላት (*ቆየ፣ ፈቀደ፣ ለቀመ፣ ተከለ፣ አፀዳ*) ተጠቅመው ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው ማናቸውም ተገቢነት ያላቸው አረፍተነገሮች ተቀባይነት አላቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ.** 1. ቆረጠ 2. ቀጠፈ 3. ወረደ 4. ወጣ 5. አፀዳ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መ.** 1. ልጁ **ክፉኛ** ወደቀ።

2. አንበሳው **በፍጥነት** ሮጠ።

3. ተማሪዎች **ገና** አልመጡም።

4. ጋሻው ምግቡን **ቶሎ ቶሎ** ባላ።

5. **እያዘገመ** መጣ።

# ምዕራፍ ስምንት

# ድርድር

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ዋና ዋና ሀሳቦችን በቃላቸው እንዲገልጹ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ተራቸውን በመጠበቅ እንዲያዳምጡና እንዲናገሩ አቅጣጫ ይሰጣሉ
- ተማሪዎች ምንባብን አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ቃላት ያላቸውን አውዳዊና ከአውድ ውጪ ፍቺ ለይተው መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የምንባብን ዝርዝር ይዘት እንዲያነቡ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች ቅጥያዎችን ከግሶች መነጠልእንዲችሉ ምሳሌዎችን በመስጠት አቅም ይፈጥራሉ
- ተማሪዎች ስለትምህርት ቤታቸው ደንብና መመሪያ እንዲፅፉ ያተጋሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ተራቸውን በመጠበቅ ያዳምጣሉ፤ ይናገራሉ፣
- ምንባብ አንብበው ከፅሑፉ የሚወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የክፍል ደረጃውን የጠበቀ ንግግር ያደርጋሉ፣
- ራሳቸውን ችለው የምንባቡን ዝርዝር ይዘት ያነባሉ፣
- ስለትምህርት ቤታቸው ደንብና መመሪያ ይፅፋሉ፣
- ቅጥያዎችን ከግሶች ይነጥላሉ።

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ተራን ጠብቆ ማዳመጥና መናገር
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በድርድር እየተሳተፉ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- ተራን ጠብቆ መናገር
- በክርክር አውድ ተሳታፊ ሆኖ መናገር
- ገዢ ወይም ሻጭ ሆኖ ሚና መጫወት
- ስለትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ መናገር
- መረጃ አጠናቅሮ የቃል ዘገባ ማቅረብ

## 2.3. ማንበብ

- የባልና ሚስት ድርድር በሚል የቀረበ ምንባብን ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

## 2.4. መፃፍ

- ስለትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ መፃፍ

- ቅጥያዎችን ከግሶች ነጥሎ መፃፍ

### 2.5. ቃላት

- ምህጻረ ቃላትን መጠቀም
- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- ግሶችን ላይ ያሉ ቅጥያዎችን መለየት

### 2.6. ሰዋስው

- ግሶች ላይ ያሉ ቅጥያዎችን በተመለከተ

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- ተማሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲያዳምጡና እንዲናገሩ ሞዴል መሆን
- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን አንብው ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲገልፁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ተማሪዎች የድርድር ተሳታፊ እንዲሆኑ ማትጋት፣
- ተማሪዎችቅጥያዎችን ከግስ ለይተው እንዲፅፉ ምሳሌ በማቅረብ ማስተማር፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድን መከተል

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- መረዳዳትን በተመለከተ አዳምጠው መልሰው መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ተማሪዎች ከግሶች ላይያሉ ቅጥያዎችን መነጠል መቻላቸውን መፈተሽ
- ስለትምርት ቤት ደንብና መመሪያ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- አህጽሮተ ጽሑፎችን መለየት መቻላቸውን ማጤን
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

## ምዕራፍ ስምንት (ድርድር)

### ክፍለጊዜ፡ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህንን ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ተራቸውን ጠብቀው የማዳመጥና የመናገር አቅም ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎች ድርድር ማድረግን የተመለከተ ምንባብ ያዳምጣሉ። ለዚህም ይሆን ዘንድ ወደ ማዳመጥ ተግባሩ ከመሄዳቸው በፊት ቅድመዝግጅት እንዲያደርጉ የቀረበ ምስል እንዲመለከተቱና ድርድር ማድረግን በተመለከተ ያላቸውን ዳራዊ ግንዛቤ ለመቀስቀስ የቀረቡ ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ይደረጋል። በዚሁ አግባብም ይከወን።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ተማሪዎቹ ምንባቡን እያዳመጡ ባሉበት ጊዜ እነዚህን ጥያቄዎች በመጠየቅ የማዳመጥ ክንውኔ ተሳታፊነታቸው ያጠናክሩ።

**ክረምት፡-** አንተ ደረቅ ልምላሜ የሚባል ነገር የማይወድህ ሁሉም ፍጡር የኔን መምጣት ሲጠባበቅ አንተ እላያቸው ላይ ተጎልተህ ትዝናናላቸዋለህ

**በጋ፡-** አፍ አለኝ ብለህ ትናገራለህ ጭፍንፍን ጨለማ ከማልቀስ በስተቀር ምን ሙያ አለህ

**ክረምት፡-** የኔ ዝነኛ ቡቃያውን እኔ እበቀልኩት በላ የሙቀቱን ኃይል እኔ ቀነስኩት በሉ

**በጋ፡-** ምነው ዘበረቅህ እህል ቢወቃ ምርት ቢሰበሰብ ሕዝብ ቢደሰት በእኔ እንጂ ባንተ ነው

**ክረምት፡-** ማን? በበቀለው እህል ማን? ባረሰው መሬት እንደዚህ በሙሉ ልብ የምታወራው

**በጋ፡-** አንተ የምታውቀው ጥላ በማስያዝ እና ቦቲ ጫማ በማስደረግ እንጂ አንድ ቀን ሕዝብ ደስ ብሎት አያውቅም ጭፍን ጨለማ ደግሞ ታወራለህ እንዴ?

**ክረምት፡-** አንተ የከሲታ ከብቶች ባለቤት አንተ የሣር ስስታም ገለባም ቢሆን በቁጥብ የምታሰጥ ውሃ ጥማም ወሬህ ሁሉ ፍሬ ቢስ መሆኑን መገንዘብ አለብህ

**በጋ፡-** ግን እኮ ስመለከተው አንተ ያፈራኸውን በኔ ባይሰበሰብ ሁሉም ውድቅ ነው የሚሆነው አይተኸዋል ተገንዝበኸዋል

**ክረምት፡-** ታዲያ ምንድነው የምታወራው?

**በጋ፡-** አንተ ያበቀልከውን በኔ ወቅት ካልተሰበሰበ አንተ ይዘኸው ከቆየ በስብሶ ይወድማል እኔ ቶሎ ብዬ ባልረዳዳ እና ባይሰበሰብ ከንቱ ነው፡፡

**ክረምት፡-** ሁለታችንም አስፈላጊ ነን ማለት ነው

**በጋ፡-** አዎ ግን ተቃራኒ ያደርጉናል ተደጋጋፊ ቢሉን እንዴት ጥሩ ነበር

**ክረምት፡-** ተሳስቻለሁ ሁለተኛ አልቃረንም ተደጋጋፊ ነን ህዝቡንም እንጠይቅ የትኛችን እንዳምንሻል

**በጋ፡-** አትድከም ሁለታችንንም በየወቅታችን ይወዱናል

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

እባክዎ መምህር በማዳመጥ የሚገኝ መረጃን ይዘው ማቆየት መቻላቸውን ለመፈተሽ በሚል አላማ የተዘጋጁትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስቀድመውም ባለፈው ክፍለጊዜ ስለተደመጠው ምንባብ ይዘተነገር አሳታፊ ክለሳ ያድርጉ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም (ታሪኩን ማስታወስ ላይ ክፍተት ካለ) ምንባቡን አንዴ ያንብቡላቸው።

ሀ. በመቀጠል የቡድን ውይይት ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በተደመጠው ምንባብ ውስጥ ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን መልሰው እንዲያነሱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፤ ሁሉም አባል ተራውን ጠብቆ የማዳመጥና የመናገር እድል ያግኝ። በመጨረሻ በመልመጃ አንድ የቀረበውን የእውነት/ሀሰት ጥያቄ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ (በፅሑፍ እንዲመልሱት ማድረግም ይችላሉ)። የጥያቄዎቹን መልሶችም በጋራ ስሯቸው፤ በዚህን ጊዜ አንዳቸው ሲመልሱ ሌሎቹ ምላሹ ልክ ስለመሆን ያለመሆኑ ማረጋገጫ ይስጡ።

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

ለ. በዚህ ክፍል አዳምጠው የቃላትን ፍቺ መስጠት መቻልን እንዲለማመዱ የሚያስችል ተግባር ቀርቧል። በመሆኑም መምህር አስቀድመው ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ የማዛመድ ጥያቄዎቹን (ቃላቱን) ጽፈው በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፤ በመቀጠል መልሶቻቸውን ይዘው በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ይተራረሙ። ሲጨርሱም ምላሾቹ ላይ በጋራ ተነጋገሩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

ሐ. እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ በማዳመጥ ትምህርቱ የቀረበውን ታሪክ አጠር አጠር አድርገው ለቡድን አባላት ተራ በተራ እንዲናገሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ከዚህ ተግባር ቀጥሎም በማዳመጥ ምንባቡ የተነሱ ዝርዝር ሀሳቦችን መልሰው እንዲያነሱ ለማስቻል በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ (መልመጃ አንድ ሐ) ጽብረቃ እንዲያካሂዱ ያበረታቷቸው። ሂደቱንም እየተዘዋወሩ ይቃኙ፤ ተሳትፏቸውን እያዩም ምዘና ያካሂዱ፤ ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

መ. በመልመጃ አንድ 'መ' ስር የተለያዩ ከማዳመጥ ምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበዋል። መጀመሪያ በቡድን ሆነው በመተጋገዝ ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ ይደረግ፤ በመቀጠል በየግላቸው በነዚሁ ቃላት አጫጭር አረፍነገሮችን ይመስርቱ (ይህ የቃላቱን ፍቺ በትክክል ስለመረዳታቸው ለማወቅ ያስችላል)። በመጨረሻም አረፍተነገሮቻቸውን ለጓደኞቻቸው ተራቸውን እየጠበቁ ያንብቡላቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ ክፍል ሁለት የመናገር ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በንግግር ሂደት ወቅት ተራ ጠብቆ መናገርን ይተገብራሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ ለዚህም በሚና ጨዋታ እየተሳተፉ ይተገብራሉ

## ተግባር አንድ

ሀ. መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ የገገርና ሻጭ ሚናዎችን እንዲጫወቱ ያበረታቷቸው። ይህንንም የየራሳቸው አውድ እየፈጠሩ አጭር ልምምድ በማድረግ

እንዲተገብሩት ያድርጓቸው፤ ልምምዱ ሲጠናቀቅ ለክፍሉ ይቀርባል። በሚና ጨዋታው ያላቸውን ተሳትፎ መሰረት በማድረግም ምዘናዎትን ያካሂዱ።

ለ. በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ሁለት ሁለት እየሆኑ ድርድር ማድረግን እንዲለማመዱ ይደረጋል። ለዚህ ሂደት ማከናወኛ የሆነውም ትምህርት የሚወድ ተማሪና ትምህርት የማይወድ ተማሪ መካከል የተካሄደ የሀሳብ ልውውጥ ነው። እባክዎ መምህር በተባለው መሰረት ተማሪዎችዎ ጥንድ ጥንድ እንዲሆኑ ያድርጓቸው፤ አቻ ያላገኘ ተማሪ ካጋጠመዎት ሦስት ሆነው እንዲሰሩ ያድርጉ። በመቀጠል ትምህርት ወዳጁ ተማሪ ትምህርት የማይወደውን ተማሪ ወደ ትምህርት መውደድ እንዲመጣ ለማሳመን ድርድር ይጀምር፤ ምልልሱም በዚሁ መንገድ ይቀጥል። እርስዎም በመዘዋወር እየቃኙ ምዘና ማድረግ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ተማሪዎች ይህንን ንኡስ የትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ምንባብ አንብበው የምንባቡን ዝርዝር ይዘቶች ይገልጻሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ አንቦ የመረዳት ጥያቄዎችንም ይሰራሉ

### ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

መምህር፣ ተማሪዎችዎ ወደ የማንበብ ተግባሩ ከመሸጋገራቸው በፊት የቅድመማንበብ ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሷቸው ይጠይቋቸው።

በመቀጠል ወደ ምንባቡ ይምሯቸው፤ እያነበቡም የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎቹን እንዲመልሷቸው ያሳስቧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

### መልመጃ ሁለት

መምህር ተማሪዎችዎ ባነበቡት ምንባብ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ በ ‹ሀ› እና በ‹ለ› ስር የቀረቡትን መልመጃዎች በትኩረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። በመጀመሪያ ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ጽፈው በግል ይስሩ፤ ለመልሳቸው ትክክለኛነት ወደ ምንባቡ እየተመለሱ ያረጋግጡ። ሲጨርሱ በመልሶቹ ላይ በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ይነጋገሩባቸው። በአማራጭነትም እርስዎ ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት ሊሰጡበት ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

## ተግባር ሁለት

መምህር፣ ይህን ተግባር ለመከወን ተማሪዎችዎ ጥንድ ጥንድ በመሆን የቀረበውን ምንባብ በድጋሚ እንዲያጠኑ ካደረጉ በኋላ የባልና የሚስቱን ሚና ተክተው ለመጫወት እንዲችሉ ልምምዳቸውን ይከታተሉ፤ ያበረታቷቸው፤ ስራቸውንም ዋጋ ይስጡት፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ተግባር ሶስት

ይህን ተግባር ለመስራት ተማሪዎችዎ ለመነሻነት ከምንባቡ የወጣውን ምሳሌያዊ አአነጋገር ፍች፣ በቡድናቸው እንዲወያዩበት ካደረጉ በኋላ ሌሎች መሰል ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ያውቁ እንደሆነ ጠይቀው ግብረመልስ ይቀበሏቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮችም በምን ጊዜ እና በምን ሁኔታ ሰዎች እንደሚጠቀሙባቸው እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

## ተግባር አራት

ሀ. በዚህ ክፍለጊዜ በወንድምና እህት መካከል የጥናት መርሃ ግብር አፈጻጸምን በተመለከተ የሚካሄድ ድርድርን በተመለከተ የመጻፍ ተግባር ቀርቧል፤ እባክዎ መምህር ተማሪዎች በትዕዛዙ መሰረት እንዲሰሩ ያትጓቸው። ወንደም እና እህት የሚያደርጉትን ድርድር በተመለከተ የሚፈጠር ምልልስን በፅሑፍ ያቅርቡ። እርስዎም ተጨባጭነቱን አይተው ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው (ሰብስበው እርማት ይስጧቸው)።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

ለ. የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎችን ርዕሰ መምህርን፣ ምክትል ርዕሰ መምህርን ወይም መምህራንና ሌሎችን በመጠየቅ በጉዳዩ ላይ ያገኙትን መረጃ በጽሁፍ አሰናድተው እንዲያቀርቡ አስቀድመው በየቤት ስራ መልክ ይስጧቸው። በክፍል ውስጥም በጥንድ ወይም በቡድን ሁነው በጻፉት ስራ ላይ እንዲነጋገሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹ፤ ሲጨርሱም የቃል ዘገባ፣ ደንብና መመሪያዎቹን በተመለከተ፣ እንዲያቀርቡ ይጋብዟቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ይህንን ንዑስ ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች በሀረጋት ውስጥ ያሉ ቃላትን መጠን በመለየት ይመድባሉ፡፡

### መልመጃ ሶስት

ሀ. በትዕዛዙ መሰረት በግል ሰርተው የሰሩትን በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ይተራረሙ። እርስዎም ምልከታ በማድረግ ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

ለ. ምህጻረ ቃል መጠቀምን እንዲለማመዱ የቀረበውን መልመጃ እንዲተገብሩት ይሁን፤ መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን ሆነው በሰሩት ላይ ሀሳብ ይለዋወጡ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

ሐ. በትዕዛዙ መሰረት ይሰራ

መ. በትዕዛዙ መሰረት ይሰራ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ይህንን ንኡስ የትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች በግሶች ላይ የተቀጠሉ ቅጥያዎችን ለይተው በማመልከት ለምን ተግባር እንደተቀጠሉ መናገር ይችላሉ

### መልመጃ አራት

ሀ. መምህር መጽሐፉ ላይ ከቀረቡት ምሰሌዎች በተጨማሪ ሌሎችን ሰሌዳ ላይ ፅፈው ያሳዩአቸው። በመቀጠልም ከቀረቡት ቃላት ቅጥያዎች መለየትን በግል ያሰሯቸው። የሰሩትንም በጥንድ ወይም በቡድን እንዲያነጻጽሩ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

ለ. መጽሐፉ ላይና እርስዎ የሚሰጧቸውን ምሳሌ መሰረት አድርገው ክፍለጊዜ አስራ ሰባት በቀረበው አካሄድ መሰረት ይሰራ። ወይም በአማራጭነት እርስዎ ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት ይስጡበት።

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

(ከተራ ቁጥር 1-3) ከጥያቄዎቹ ይዘቶች ጋር የተያያዙ ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው መልሶች

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ክረምት እና በጋ 2. በጋ 3. በጋ 4. ተደጋጋፊ መሆናቸው (በጋ)

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. ሀሰት 6. ሀሰት 7. እውነት

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ለ**.1. መ 2. ሠ 3. ሐ 4. ለ 5. ሀ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

ሐ. ምንባቡንና የተማሪዎችን አስተያየቶች የያዙ ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው መልሶች

1. የክረምት ወቅት ጨለም ስለሚል
2. በበጋ ወቅት ብዙ ውሃ ስለማይገኝ
3. ክረምት
4. በጋ፤ ጥላ ስለማያስይዝ፤ ቦቲ ስለማያስለብስ፤
5. ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

መ. ከንቱ - የማይረባ፣ ስስታም - ቆጥቋጣ፣ ጨለማ - ብርሃን የሌለበት፣
ተቃራኒ - የማይመሳሰል፣ ልምላሜ - ማበብ፣ ቡቃያ - ችግኝ፣ ጭፍን - ምክንያተ ቢስ፣
ጉራ - እኔ ብቻ ባይ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

*ሀ. ገገርና ሻጭ ሆነው ሚና ይጫወታሉ*

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

*ለ. ድርድር በተማሪዎች መካከል*

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**ቅድመማንበብ ጥያቄዎች**

*ለሁለቱም ጥያቄዎች ማናቸውም ከጥያቄዎቹ ይዘት ጋር የሚሄዱ ምላሾች ተቀባይነት አላቸው*

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

*ባል እና ሚስቱ ወደ ድርድር የሚያመሩ ይመስላችኋል?*

- *አዎ ወይም አይ ብለው ምክንያት ይስጡ*

*ባልዬው ሚስቱ እንደምታስበው ሀሳቡን የሚቀየር ይመስላችኋል?*

- *ግምታቸውን ያስቀምጣሉ*

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. *እውነት* 2. *ሀሰት* 3. *እውነት*

**ለ.** 1. *አቶ ጎሣ፤ ምክንየቱም በመነጋገር መግባብት ስላልለመደ*

2. *ወይዘሮ አለሚቱ*

3. *እንነጋገር፣ እንወያይ፣ እንረዳዳ... /. አልሰማም፣ እኔ አያገባኝም...*

4. *በስምምነት*

**ሐ.** *ወሳኝ - ዋነኛ፣ ባልትና - ሙያ፣ አዛዥ - አስፈፃሚ፣ በጀት - ወጪ፣ ፈቃድ - ይሁንታ፣* (*ማናቸውም አረፍተነገሮች ቃላቱን የተጠቀሙና ተቀባይነት ያላቸው*)

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ተግባር ሁለት**

*በምንባቡ መሰረት የሚና ጨዋታ ይጫወቱ*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ተግባር ሦስት**

የሚያውቋቸውን ምሳሌያዊ ንግግሮች በማንሳት ፍች ለመስጠት ይሞክሩ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**ተግባር አራት**

**ሀ.** በእህትና ወንድም መካከል የተደረገ ድርድር

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ለ.** የትምህርት ቤት ደንብን የተመለከተ ጽሑፍ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

***መልመጃ ሦስት***

**ሀ.** በትዕዛዙና በምሳሌው መሰረት ይሰራሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ለ.** ተቀባይነት ባለው መልኩ አህጽሮተ ጽሁፎቹ ይጽፋሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ሐ.**ተቀባይነት ባለው መልኩ ሙሉ ቃሉ ይጽፋል

**መ.** ተቀባይነት ባለው መልኩ ይሰራል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

***መልመጃ አራት***

**ሀ.** 1.ተ-ሠራ 2. አስ- ሮጥ - ኦ 3. ቆል - ኣቸው 4. ተ- ቀሰመ 5. ሄድ - ኣችሁ

6. ሰጥ - ን 7. ተ- ከፈተ 8. ተ- ለወጠ 9. ቆረጠ - ው 10. ቆፈረ - ው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ለ.**

| ተ.ቁ | ቅጥያ ያለበት ቃል | ቅጥያ የሌለው ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1. | አለፋቸው | አለፈ | ኣቸው |
| 2. | አስመታው | መታ | አስ- ው |
| 3. | አልሄደም | ሄደ | አል-ም |
| 4. | ተፈለጠ | ፈለጠ | ተ |
| 5. | አዘዘው | አዘዘ | ው |
| 6. | ሠራተኛ | ሠራ | -ተኛ |
| 7. | አስፈለጠው | ፈለጠ | አስ - ው |
| 8. | ጠጣው | ጠጣ | ው |
| 9. | አስደገነጠ | ደገነጠ | አስ- |
| 10. | ተፈለገ | ፈለገ | ተ- |

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የመገናኛ ብዙሃን

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎች የተቀረጹ ድምጾችን አዳምጠው የንግግርን ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ አቅጣጫ ይሰጣሉ
- ተማሪዎች ምንባብን አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የምንባብን ዝርዝር ይዘት እንዲያነቡ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች መስተዋድዶችን እንዲለዩ ምሳሌዎችን በመስጠት አቅም ይፈጥራሉ
- ተማሪዎች ተራ አረፍተ ነገሮችን ተጸቅመው አንቀጽ እንዲፅፉ ያተጋሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- የተቀረጹ ድምጾችን በማዳመጥ የንግግርን ፍሬ ሀሳብ ይናገራሉ፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤

- ተራ አረፍተነገሮችን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፤
- መስተዋድዶችን ተጠቅመውአረፍተነገር ይመሰርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የተቀረጹ ድምጾችን አዳምጦ መናገር
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- አዳምጦ መናገር
- ስለመገናኛ ብዙሃን ጠቀሜታ መናገር
- መረጃ አጠናቅሮ የቃል ዘገባ ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- የመገነኛ ብዙሃንን የተመለከተ ምንባብ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

### 2.4. መፃፍ

- ዋናና ዝርዝሀሳቦችን መፃፍ
- ስለኢንተርኔት ጠቀሜታ መፃፍ
- ተራ አረፍተነገሮችን ተጠቅሞ አንቀጽ መጻፍ
- መስተዋድዶችን ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት

### 2.5. ቃላት

- ቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ መፍታት
- መስተዋድዶችን መለየት

### 2.6. ሰዋስው

- መስተዋድዶችን መጠቀም

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- ተማሪዎች የተቀረፀ ድምጽን እንዲያዳምጡ ማስቻል (ማዘጋጀት)
- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ዕሑፍን አንብበው ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲገልፁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ተማሪዎች መስተዋድዶችን ለይተው እንዲፅፉ ምሳሌ በማቅረብ ማስተማር፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- የተቀረጸ ንግግርን አዳምጠው መልሰው መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ተማሪዎች መስተዋድዶች መለየት መቻላቸውን መፈተሽ
- ተራ አረፍተነገሮች ተጠቅመው አንቀጽ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

### ምዕራፍ ዘጠኝ (የመገናኛ ብዙሃን)

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህንን ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ የመናገር ልምምድ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር፣ ወደ ማዳመጥ ተግባሩ ተማሪዎችዎ ከመግባታቸው በፊት እባክዎ የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹን ያሰሯቸው። (ተራ ቁጥር 1 እና 2)

መምህር፣ በተማሪዎቹ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እንዲያነቡና እያዳመጡ የሚመልሷቸው መሆኑን ያስገንዝቧቸው፡፡ ተማሪዎችዎ ዝግጁ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ የሚከተለውን ጽሁፍ ያቅርቡላቸው።

## የመገናኛ ብዙሀን ጥቅምና ጉዳት

መገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በርቀት ያሉ ሰዎችን እንዲተዋወቁና እንዲግባቡ ማመቻቸት፣ ሰዎች ትምህርታቸውን በርቀት እንዲከታተሉ ማድረግ ፣ አገራትን እንዲቀራረቡና የባህል ልውውጥ በመካከላቸው እንዲኖር ማድረግ ፣ የተለያዩ ድርጅቶች አገልግሎቶቻቸውን እና ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ ፣ መረጃን በስፋት ማሰራጨት፣ማዝናናት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይህም በኤሌትሮኒክስ መሳሪያዎች (ስልኮች ፣ ኮምፒዉተሮች ፣ ታብሌቶች እና ሌሎችም) አማካኝነት ይፈፀማል።

መገናኛ ብዙሀን ጠቀሜታ እንዳላቸው ሁሉ ብዙ ጉዳትም አላቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የሰው ልጅ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ጥገኛ እንዲሆን ማድረግ ፣ አልፎ አልፎ የሚተላለፈው መረጃ ከእውነት የራቀ መሆንና በሰዎች መካከል ግራ መጋባት መፍጠር፣ የጥላቻ ንግግሮችን በማስተጋባት በግለሰቦችና በህብረተሰብ መካከል ግጭት እንዲፈጠር ማድረግ ፣ ማጭበርበር ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መገናኛ ብዙሀን ጠቀሜታም ጉዳትም እንዳላቸው በመገንዘብ በጥንቃቄ ልንጠቀምባቸው ይገባል፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን እያዳመጡ እንዲሰሩ በወቅቱ ያሳስቧቸው፤ የሚደመጠውን ነገርም ለአፍታ ገታ ያድርጉላቸው

## ክፍለ ጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ በተደመጠው ምንባብ መሰረት ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ማነቃቂያ ይስጧቸው። የእውነት ሀሰት ጥያቄዎቹን የተደመጠውን ታሪክ ከከለሳችሁት በኋላ

ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሩና ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። ሲጨርሱም ምላሻቸውን ለክፍሉ ያቅርቡ።

## ክፍለ ጊዜ:ሶስት

ለ. ይህንን ተግባር ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገውና ልምዳቸውን በመንተራስ በቡድን ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ እያነሱ ይወያዩባቸው። ሲጨርሱም በተወካይ አማካኝነት የቃል ዘገባ ያቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት ፡መናገር

ይህንን ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ የመገናኛ ብዙሃንን ምንነትና ጠቀሜታ በተመለከተ ንግግር ማድረግ ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል

## ተግባር አንድ

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ዝግጅት አድርገው በመገናኛ ብዙሃን ጠቀሜታ ላይ በቡድን እንዲወያዩና በቡድን ተወካይ አማካኝነት የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። አፈጻጸሙንም ይመዝኑ።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ተግባር ሁለት

እባክዎ መምህር ከተለያዩ ምንጮች ስለመገናኛ ብዙሃን ጥቅምና ጉዳት በተለያዩ አውዶች የተደረገ ውይይትን በመጭመቅ ለተማሪዎችዎ ያቅርቡላቸው። በመቀጠልም ስለተደመጠው ነገር በቡድን ሆነው ውይይቱ (ምን ምን ነገሮች እንደቀረቡበት) እንዲያደርጉና በቡድን ተወካይ አማካኝነት ወይም ተራ በተራ ሁሉም ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፤ ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ይህንን የትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ያለችግር ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## የመገናኛ ብዙኀን

መምህር ተማሪዎቹ የቀረቡትን ምስሎች እንዲቃኟቸው ይጠይቋቸው።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

ምንባቡ ከመነበቡ በፊት የቅድመማንበብ ጥያቄዎቹ በጋራ በቃል ይስሩ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎቹ ምንባቡ እየተነበበ ይሰሩ፣ የማንበቢያ ጊዜ (ደቂቃ ተወስኖ ይሰጣቸው)

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

እባክዎ መምህር ምንባቡን በድጋሚ አንዴ እንዲያነቡት ይጠቁሟቸው!

ሀ. በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት ብለው ይመልሱ ይህንንም መጀመሪያ በግላቸው ከዚያም በቡድን ሆነው ያረጋግጡ። በአማራጭነት እርስዎ ደብተራቸውን ሰብስበው ማረም ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

ለ. ጥያቄዎቹ በግል ደብተር ላይ ይጻፉና ይሰሩ፣ ምንባቡን ደግመው በማንበብ ምላሾቹ ላይ እርግጠኛ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል።

ሐ.መምህር ተማሪዎቹ ወደ ምንባቡ ተመልሰው የተሰጡት ቃላት የት የት እንደሚገኙ እንዲጠቁሙ (አንቀጽና መስመሩን) በማድረግ አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጧቸው ያድርጉ። ሲጨርሱም የሰጧቸውን ፍቺዎች እንዲያነፃፅሩና ቃላቱን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ፣ እርማትም ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ተግባራትና መልመጃዎችን በመስራ መጻፍ ይለማመዳሉ::

## ተግባር ሦስት

ሀ. መምህር፣ ተማሪዎችዎ ቀደም ሲል ያነበቡትን ጽሁፍ በጥልቀት እንዲያነቡት እድል ከሰጧቸው በኋላ የየአንቀጾቹን ሀሳብ በአንድ አንድ አረፍተነገር ጨምቀው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፤ ያግዟቸውም፡፡የጻፏቸውንም በየቡድናቸው እንዲወያዩባቸውና የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ይደረግ፤ ከአነበቡት ምንባብ ውስጥ ዋና ዋና ሀሳቦችን አውጥተው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስር

ለ. መምህር በዚህ ተግባር የተዘረዘሩ የመገናኛ ብዙሃንን አገልግሎትና ባህርይ ተማሪዎችዎ አጭር ዓረፍተነገር እንዲጽፉ መመሪያ ከሰጧቸው በኋላ ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ ለስራዎቻቸውም ማበረታቻና ዋጋ መስጠትዎን አይዘንጉ፡፡

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ተግበር አራት

የኢንተርኔት (በይነ መረብ) አገልግሎት ምንነትንና የሚሰጣቸውን ጠቀሜታዎች  እንዲሁም ሊያስከትል የሚችላቸውን ጉዳቶች በተመለከተ ሃሳባቸውን በፅሁፍ እንዲያሰፍሩ ይነገራቸው። ሲጨርሱም በቡድን በቡድን እየሆኑ ውይይት ያድርጉ፤ በማጠቃለያውም ከቡድኑ አባላት የተሻለ ነው ያሉትን ምላሽ በንባብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ይደረግ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ተግባር አምስት

በዚህ ተግባር ተማሪዎች አስቀድመው ዝግጅት እንዲያደርጉ በሌላ ክፍለጊዜ ይነገራቸዋል። በትዕዛዙ መሰረትም ስለአንድ ወቅታዊ ጉዳይ ወይም የስፖርት ክንውን ጋዜጠኞች እንደሚያደርጉት ዜና ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ እንዲያነቡ ይበረታቱ፤ ፅፈው የመጡትንም ከንባባቸው በኋላ ሰብስቦ ማረም ይገባል።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

የዚህን ንኡስ ትምህርት ክፍል ይዘት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ለቃላት አውድን መሰረት ያደረገ ፍቺ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ.** የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ በጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ ውይይት እንዲያደርጉባቸው ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተነገር ይመስርቱ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

**ለ.** እባክዎ መምህር የተሰጧቸውን ቃላት በመጠቀም አረፍተነገሮቹን እንዲመሰርቱ ይንገሯቸው። ሲጨርሱም ደብተሮቻቸውን ሰብስበው ምጋቤ ምላሽ ይስጡባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

## መልመጃ አራት

**ሀ.** ከተሰጧቸው አረፍተነገሮች ውስጥ ቅጥያዎችን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጓቸው። ሲጨርሱም ምላሾቻቸውን በቡድን በቡድን ሆነው እንዲነጋገሩባቸው ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ሲጨርሱም እርስዎ ስለመስተዋድዶች አጭር ገለፃ ያቅርቡላቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**ለ.** ያለፈው ክፍለጊዜ ትምህርት ይከለስ፣ ቅጥያዎችን በተመለከተ ማብራርያ ይሰጧቸው፤ በመቀጠል የቀረቡትን ቅጥያዎች በመጠቀም አረፍተነሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ። በመጨረሻ ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**ሐ.** በትዕዛዙ መሰረት ይሰራ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

**መ.** በትዕዛዙ መሰረት መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ በቡድን ቡድን በመሆን ተሰርቶ ምጋቤ ምላሽ በጋራ ይሰጥበት።

# የመልመጃዎችና የተግባራት መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መፅሔት፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት…
2. መረጃ ለህዝብ ማዳረስ፣ ሀሳቦችን ማንሸራሸር፣ ማዝናናት፣ ለንግድ(ለማስተዋወቅ)

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. መረጃ ማሰራጨትና ማዝናናት… 2. ብዙ ጉዳት 3. ግራ መጋባት

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ.** 1.እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሀሰት 5. እውነት

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

ለ. 1. በርቀት ያሉ ሰዎችን እንዲተዋወቁ ማድረግ፣ ሰዎች ትምህርታቸውን በርቀት እንዲከታተሉ ማመቻቸት፣ አገራትን ማቀራረብና ባህል ማለዋወጥ፣ ማዝናናት፣መረጃን ማሰራጨት፣ ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ

2. የሰው ልጅ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ጥገኛ እንዲሆን ማድረግ ፣ የሚተላለፈው መረጃ ከእውነት የራቀ መሆን፣ በሰዎች መካከል ግራ መጋባት መፍጠር፣ የጥላቻ ንግግሮችን በማስተጋባት ግጭት እንዲፈጠር ማድረግ
3. የርቀት ትምህርትንም ሆነ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት በማሳለጥ
4. ምርትንና አገልግሎትን በማስተዋወቅ 5.
5. በጥንቃቄና በአግባቡ (የሀሰት መረጃ ወይም የተዛባ መረጃም ሊተላለፍባቸው ስለሚችል)

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት ፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

የመገናኛ ብዙሃን በተለይም የማህበራዊ ሚዲያን በተመለከተ ያላቸውን ጠቀሜታና ጉዳት በዝርዝር አንስተው እንዲወያዩ ያደርጉ፤ መረጃን መርጦ ስለመውሰድ፣ ሁልጊዜ የሚባለው

ልክ ላይሆን እንደሚችልና ሁሉንም በጅምላ ከመቀበል ተቆጥበው መረጃን እንዲያጣሩና ባግባቡ እንዲጠቀሙበትም ምክር ይስፀጧቸው፤ እርስዎም አርዓያ ይሁኗቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሁለት**

ስለመገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ የተደረጉ ውይይቶችን ሀሳብ መናገር

**ክፍል ጊዜ ስድስት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**የቅድመማበብ ጥያቄዎች**

1. ከስዕሉ የተረዱትን ማንኛውንም ነገር ይገልጻል
2. የመሰላቸውን ይናገራሉ፤ ልክ ቢሆንም ባይሆንም
3. ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን ወዘተ እያሉ

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ… ((**የብሮድ ካስት** ወይም የስርጭት፤ ቴሌቪዥን ፣ ሬድዮ) (**የህትምት**፡ ጋዜጣ ፣ መፅሔት)፤ (**የኢንተርኔት**፡ ማህበራዊ ሚዲያ))
2. ጋዜጣ፣ መፅሔት በራሪ ወረቀቶች

**ክፍል ጊዜ፡ ሰባት**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሀሰት

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ለ.** 1. ሀ 2. ለ 3. ለ 4. መ 5. ሐ

**ሐ.** 1. የተወሰነ 2. ደጋፊነት 3. የመጀመሪያ 4. ተንቀሳቃሽ 5. ብዙ

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**ተግባር ሦስት**

**ሀ.** የአንቀጾቹ ዋና ሀሳቦች

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ለ.** ተቀባይነት ያላቸው አጫጭር ዓረፍተነገሮች/ ዋና ዋና ሀሳቦችን አውጥቶ መጻፍ

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

**ተግበር አራት**

እንተርኔት ጠቀሜታው (ጊዜና ቦታ ሳይገድበው፣ በምስልና ድምፅ እንዲሁም በፅሑፍ መረጃን ማስተላለፉ፣ ዘመናዊ መሆኑ፤ ጉዳት፡ የሀሰት መረጃ ሊተላለፍበት መቻሉ፣ ህፃናት ላይ ጉዳት ሊያመጣ መቻሉ፣ ውድ መሆኑ) ሌሎች ተማሪዎቹ የሚያነሷቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ተግባር አምስት**

አዘጋጅተው ያመጡት ወቅታዊ ጉዳይ ወይም ስፖርታዊ ክንውንን የተመለከተ ጉዳይ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ ሶስት**

1. ገደብ - ልክ
2. ግለሰባዊ - አንድ ሰው
3. አገልግሎት - ማስተናገድ/መጥቀም
4. ህትመት - ፅሑፍ
5. መረጃ - ሁነት/ስለጉዳዩ ያለ እውነት
6. ፈጣን - ቀልጣፋ
7. ሙያ - ስራ
8. ቀዳሚ - የመጀመሪያ
9. ማሰራጨት - ማስተላለፍ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ለ.** 1.ታዳሚዎች 2. መረጃ 3. ኮምፒዉተር 4. ትኩረት 5. ምስል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው**

**መልመጃ አራት**

**ሀ.** 1.ስለ 2. በ- 4. ላይ 5. ስለ-፣

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ለ.** ላይ ፣ ስር፣ ጋር ፣ ውስጥ የተሰኙ ቅጥያዎችን ተጠቅመው የተመሰረቱ አረፍተነገሮች

**ክፍለጊዜ አስራ ሰባት**

**ሐ.** 1. ከ- 2. ላይ/አጠገብ/ስር 3. በ- 4. ከ- 5. ስለ-

**ክፍለ ጊዜ አስራ ስምንት**

**መ.** 1. ከ-፣ 2. በ-፣ በ- 3. ስለ- 4. የ- 5. -ን፣ በ-፣ የ-፣ ለ-

# ምዕራፍ አስር

# ንግድ

## (የክፍለጊዜ ብዛት፡ አስራ ስምንት)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎች ምንባብን አዳምጠው ዋናውን ሀሳብ እንዲለዩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ አቅጣጫ ይሰጣሉ
- ተማሪዎች ምንባብን አንብበው የእያንዳንዱን ምንባብ አንቀጽ ዋና ዋና ሀሳብ እንዲለዩ ምሪት ይሰጣሉ
- ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት እንዲችሉ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተመስርተው አጭር አንቀፅ እንዲፅፉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት እንዲለዩ ምሳሌዎችን በመስጠት አቅም ይፈጥራሉ
- ተማሪዎች ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ተጠቅመው አረፍተነገር እንዲፅፉ ያተጋሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍለጊዜ ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ይበጃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርትበኋላ፡-**

- ምንባቡን አዳምጠው ዋናውን ሀሳብ ይለያሉ፣
- የተሰጠውን ምንባብ አንብበው የእያንዳንዱን አንቀፅ ዋና ዋና ሀሳብ ይገልጻሉ፣
- በተሰጠው ርዕስ ላይ ተመስርተው አጭር አንቀጽ ይፅፋሉ፣
- ከአንድ ፍቺ በላይ ያሏቸውን ቃላት ለይተው ያመክታሉ፣
- ቅጥያ ባላቸው ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ዋናውን ሀሳብ ለመለየት ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በውይይት ተሳታፊ ለመሆንና ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- አዳምጦ መናገር
- መረጃ አጠናቅሮ የቃል ዘገባ ማቅረብ
- በቡድን ውይይት መሳተፍ

## 2.3. ማንበብ

- ንግድን የተመለከተ ምንባብ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- የማንበብ ጊዜና የድህረማንበብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ

## 2.4. መፃፍ

- ዋናና ዝርዝሀሳቦችን መፃፍ
- የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መሰረት አድርጎ አረፍተነገር መፃፍ
- ሀሳብ አደራጅቶ አንቀጽ መጻፍ
- መስተዋድዶችን ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት

### 2.5. ቃላት

- ሁለት ፍቺ ያላቸውን ቃላት ለይቶ መጠቀም
- የቃላትን ፍቺ ከአውድ መረዳት

### 2.6. ሰዋስው

- ቅጥያ ያላቸውን ቃላት መለየት

## 3. ማስተማሪያ ብልሃቶች

- ተማሪዎች የተቀረፀ ድምጽን እንዲያዳምጡ ማስቻል (ማዘጋጀት)
- የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ፅሑፍን አንብው ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲገልፁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ተማሪዎች መስተዋድዶችን ለይተው እንዲፅፉ ምሳሌ በማቅረብ ማስተማር፣
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊና የተግባቦቱ ባለቤት እንዲሆኑ ማመቻቸት
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድን መከተል

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- ተማሪዎች ምንባብን አዳምጠው ዋና ሀሳብን ሲገልጹ መከታተል
- ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ አንብበው የእያንዳንዱን አንቀጽ ዋና ሀሳብ ለይተው ማመልከት መቻላቸውን መመዘን
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- የተሰጠ ሀሳብን በመጠቀም አንቀጽ መፃፍ መቻልን ማረጋገጥ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## የምዕራፉ ዝርዝር አቀራረብ

እባክዎ መምህር ትምህቱን ለተማሪዎችዎ ሲያቀርቡ በየንዑስ ክፍሉ ቀጥሎ የተሰጡትን አቀራረቦች እንደመነሻ ይጠቀሟቸው

# ምዕራፍ አስር (ንግድ)

መምህር፣ በዚህ ምዕራፍ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በየትምህርት ክፍሉ የቋንቋ ትምህርት ይዘትን ለማገዝ ቀርበዋል፤ በመሆኑም በቀጣይ የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትኩረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ጥያቄዎቹ እንደየክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ በጥንድና መጨረሻም ከቡድን ውይይት በኋላ በተወካይ አማካኝነት ሊመለሱ ይችላሉ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር ምንባቡ ስለምን እንደሆነ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ የተማሪዎችን ምላሽ መቀበል፤ ስዕሉን እንዲመለከቱ መጋበዝ፣

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እነዚህ ጥያቄዎች ምንባቡ እየተነበበ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሲሆኑ በምንባቡ ውስጥ በያዙት ቅደም ተከተል መሰረት ይጠየቁ።

መምህር እባክዎትን ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ይህንን ምንባብ ተገቢውን ፍጥነትና አገላለፅ በመከተል ቢያንስ ሁለት ጊዜ ለተማሪዎችዎ ያንብቡላቸው።

# ሕጋዊ ነጋዴዎች

ወይዘሮ ጫልቱ ከአቶ ረጋሣ ጋር ትዳር መስርተው መኖር ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ወይዘሮ ጫልቱ እና አቶ ረጋሣ ሁለቱም በንግድ ሥራ ተሰማርተው ይሰራሉ፡፡ እነዚህ ባለትዳሮች አራት ልጆች አፍርተዋል፡፡

ባንድ ወቅት ግብር በወቅቱ ባለመክፈላቸው ምክንያት ሱቃቸው ስለታሸገ ሥራቸው ለተወሰነ ጊዜ የንግድ ስራቸው ቆሞ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ግራ በመጋባታቸው ስለሁኔታው ለመረዳት ወደ አካባቢው ገቢዎች ጽህፈት ቤት በመሄድ ስለጠቅላላ የንግድ ህጎች በመጠየቅ ህጉን ተረዱ። የተነገራቸውንም የንግድ ሕጎች በመረዳት ሌሎችንም ማስረዳት ጀመሩ። ወደ ንግድ ዓለም የሚቀላቀሉ አዳዲስ ነጋዴዎችንም ፍቃድ እንዲያወጡ ግብራቸውን በወቅቱ እንዲከፍሉ መምከር የዜግነት የውዴታ ግዴታቸው እንደሆነ ያስገነዝቧቸዋል፡፡ ግብር መክፈል ሀገሪቱ የጎደላትን መሰረተ ልማቶች ለማሟላት እንደሚያስችል ጠንቅቀው

አውቀዋል፡፡ ዜጎች የተሻለ ማህበራዊ አገልግሎት ለማግኘት ፍትሀዊ እና ትክክለኛ ግብርን በወቅቱ መክፈል አስፈላጊ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል፡፡

ወይዘሮ ጫልቱ እና አቶ መገርሳ ስለንግድ ሕጎች ካወቁ በኋላ ሁሉንም የንግድ ሥራቸውን በንግድ ሕጉ መሰረት ያከናውናሉ፡፡ አንድም ቀን ሳያሳልፉ በወቅቱ ግብራቸውን ይከፍላሉ:: በዚህም የተነሳ የአመቱ ሕጋዊ ግብር ከፋዮች በመሆናቸው ከወረዳው ገቢዎች ጽህፈትቤት ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

በሚኖሩበት ከተማ ግብርን በአግባቡ በመክፈል ለአካባቢው ማህበረሰብ አርአያ ናቸው፡፡ ገቢ እና ወጪያቸውንም በየጊዜው ይመዘግባሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ከእነሱ የሚጠበቅባቸውን ገንዘብ በየዓመቱ ለመክፈል ነው፡፡ የንግድ ፈቃዳቸውን በማስደስ እና ለፍቃዱ ማደሻ የሚጠየቁትን ገንዘብ በደስታ ይከፍላሉ፡፡

አቶ መገርሣ በአካባቢያቸው በስፋት የሚመረተውን የጥራጥሬ ምርት እየገዙ ወደ ተለያዩ ቦታዎች መላክ ጀምረዋል፡፡ ለሱቃቸው የሚሆን ሸቀጣሸቀጥ ከአዲስ አበባ በማስመጣት ስለሚሸጡ ትርፋማ ሆነዋል፡፡ ከአካባቢው ነዋሪዎችም በተሻለ ሁኔታ ኑሯቸውን መምራት ጀምረዋል፡፡ ሕጋዊ ነጋዴ በመሆናቸውም ደስተኞች ናቸው፡፡

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ስለተነበበው ምንባብ አንዳንድነጥቦች በክለሳ መልክ እያስታወሱ እንዲናገሩ በመጋበዝ ይጀምሩ። ቀጥሎም የእውነት/ሀሰት መልመጃውን እያነበቡ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### መልመጃ ሁለት

ለ. መምህር፣ ተማሪዎች 'የወይዘሮ ጫልቱንና የአቶ መገርሣ'ን ታሪክ በቃል እንዲያቀርቡ በመጠየቅ ማስጀመር ይቻላል። ከዚያም መጀመሪያ ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ በግል ማሰራት ቀጥሎ ወደ ቡድን ውይይት እዲገቡና በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ። በመጨረሻም በተወካይ አማካኝነት የቃል ዘገባ ማስቀረብ።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

ሐ· አውዳዊ ፍች መስጠት

- የቀረቡትን ቃላት ወይም የምንባቡን ታሪክ ተጨባጭ የሚያደርጉ መርጃዎችን አዘጋጅወቶ ወይም ተውሶ መምጣትና መጠቀም።
- የተሰጡትን ቃላት ሰሌዳ ላይ መፃፍ፤በታሪኩ ውስጥ ቃላቱ ያሉበትን አረፍተ ነገር እየመረጡ ማንበብና ፍቻቸውን ከአውዱ እንዲሰጡ ማበረታታት።
- ሲሰሩ እየተዘዋወሩ መቃኘት፤ የሰሩትን በመመልከት እርማትና ምጋቤ ምላሽ መስጠት።

## ክፍለ ጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎቹ ሀሳብ እንዲለዋወጡ የሚያስችሉ ተግባራት ተካትተው ቀርበዋል። እባክዎ መምህር ሁሉም ተማሪዎች በቀረቡት ተግባራት ላይ መሳተፋቸውንና የመናገር እድሉን ማግኘታቸውን ክትትል እያደረጉ ያረጋግጡ።

## ተግባር አንድ

- ተማሪዎችዎን አምስት ወይም ስድስት ስድስት እያደረጉ ማቧደን፤
- ከዚያም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሀሳብ እንዲያዋጡ ማበረታታት፤ ለደቂቃዎች ከተወያዩ በኋላም ሁለት ሁለት ተወካዮች ከየቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ የቃል ዘገባ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማበረታታት
- የቃል ዘገባው ሲቀርብ የሚነሱ ነጥቦችን ተጨባጭነትና የሀሳብ ፍሰትን መመዘን፤ እንዳስፈላጊነቱ ምጋቤ ምላሽ መስጠት

## ክፍለ ጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ይህንን ትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ በትክክል አንብበው ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

## ንግድ

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

የቀረበውን ምስል እያዩ ምንን የተመለከተ እንደሆነ እንዲናገሩ መጠየቅ፣ የሦስት ወይም አራት ተማሪዎችን መልስ መቀበል

ከተራ ቁጥር 1- 3 ያሉትን ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ እድል መስጠት (ማሳተፍ)

## የማንበብ ጊዜ

- ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ መጋበዝ፣ አፈፃፀሙንም እየተዘዋወሩ ምልከታ በማድረግ መከታተል
- የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎቹንም እያነበቡ እንዲመልሷቸው ማሳሰብ (ሁለት ጥያቄዎች)
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምንባቡን አንዴ በሞዴልነት ማንበብ

## ክፍለጊዜ ሰባት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

- በየቡድናቸው ሆነው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን እንዲሰሯቸው ማበራታት
- እንደስልትም ወደኋላ ተመልሰው ምንባቡን መልሰው እንዲያነቡት መንገር
- አፈጻፀሙን እየተዘዋወሩ መቃኘት፣
- ድጋፍ ለሚሹ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ
- የእውነት/ሀሰት እና የምርጫ ጥያቄዎቹን በጋራ ማመሳከር (መልስ መስጠት)

## ክፍለጊዜ ስምንት

ሐ. እባክዎ መምህር የቀረቡትን ጥያቄዎች (ከ1-5 ስር) መጀመሪያ ተማሪዎችዎ በግል፣ ቀጥሎ በቡድን እንዲመለከቷቸው ማስቻል፣ በመጨረሻም እንደክፍል እየተወያያችሁባቸው መልስ ስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ይህንን ንኡስ ትምህርት ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የየራሳቸውን አንቀፅ በደረጃቸው መፃፍ ይችላሉ

**መልመጃ ሦስት**

በዚህ መልመጃ ስር ከምንባብ የወጡ ቃላት ቀርበዋል። እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ወደ ምንባቡ በመመለስ ቃላቱ የት የት እንደሚገኙ እዲያመለክቱ ይጋብዟቸው፤ ይህንንም ከጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ እንዲሰሩ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በመጨረሻ ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አስር**

**ተግባር ሁለት**

እባክዎ መምህር አንቀጽ ምን እንደሆነ (አንድ ሙሉ ሀሳብን የያዘ የጽሁፍ መዋቅር ስለመሆኑ፤ በውስጡ ሀይለቃል የሚባልና ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ስለመኖራቸው፤ አንቀፅ ሲጻፍ አንድነት፣ ተለጣጣቂነትና ምልኡነት ያለው ስለመሆኑ) አጠር ያለ ገለጻ ይስጧቸው። በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የተሰጡትን ሀሳቦች አደራጅተው አንቀጽ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ደብተራቸውን ሰብስበው ምዘና ያካሂዱ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አራት

ሀ. በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ቃላት ሁለት የተለያየ ፍቺ ሊኖራቸው እንደሚችል ተገንዝበው በሚሰጣቸው ምሳሌ መሰረት ለቀረቡት ቃላት ሁለት ሁለት ፍቺ እንዲሰጡ ይደረጋል። እባክዎ መምህር አንድ ሁለት ምሳሌዎችን ሰሌዳ ላይ ጽፈው ተማሪዎችዎን ያሳዩአቸው፤ ያንኑ መሰረት አድርገው የተሰጧውን ቃላት ይስሩ። ሲጨርሱ ጥንድ ጥንድ ሆነው ያነጻጽሩ። እንደክፍልም ተነጋገሩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ለ. በክፍለ ጊዜ አስራ አንድ ሁለት ሁለት ፍቺ የሰጡባቸውን ቃላት በመጠቀም ዛሬ ተማሪዎችዎ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ። እባክዎ መምህር ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ወይም ሶስት ቃላትን በመውሰድና ለቃላቱ ሁለት ሁለት ፍቺ በመስጠት ካሳዩ በኋላ የተሰጠውን ፍቺ መሰረት አድርገው አረፍተነገር በስርተው ያሳዩአቸው። በምሳሌው

መሰረት እንዲሰሩም ያትጓቸው። ተማሪዎቹ ሲጨርሱ ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

ሐ. በዚህ ንኡስ መልመጃ ክፍል ባዶ ቦታ ላይ ሊሞሉ የሚችሉ ቃላት ተሰጥተዋል። መምህር ተማሪዎችዎ መጀመሪያ አረፍተነገሮቹን ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉና በመቀጠል ቃላቱን እየተጠቀሙ እንዲያሟሏቸው ያበረታቷቸው። ሰርተው ሲጨርሱም ከክፍል ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የሰሩትን እንዲያነጻጽሩ ይንገሯቸው። በመጨረሻም በጋራ እንደክፍል ይሰራ፤ ተመሳሳይ ስራም በየቤት ስራ መልክ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

መ. በትዕዛዙ መሰረት መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን በመሆን ሁለት ሁለት ፍች ያላቸውን ቃላት ተማሪዎቹ ይለዩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

መምህር፣ ተማሪዎችዎ በክፍለጊዜ አስራ አራት ‹መ› ስር የለዩትን ሁለት ሁለት ፍች የላቸውን ቃላት ተራ በተራ እየተነሱ የቃላቱን ፍች ከጻፉ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ አምስት

ሀ.መምህር እርስዎ በሚሰጧቸው ምሳሌ መሰረት ከቀረቡት ቃላት ተማሪዎችዎ ቅጥያዎችን እየለዩ እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው። መልመጃውንም በግላቸው ሰርተው ሲጨርሱ ስራዎቻቸውን እርስበርስ እንዲተራረሙ እድል ይፍጠሩላቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ለ. በክፍለጊዜ አስራ ሰባት በተሰራው መሰረት ይከወን።

## ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ስምንት

ሐ. እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ቅጥያ አላቸው ብለው የለዩአቸውን አረፍተነገሮች በመጠቀም አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ከምስሉ የተረዱትን ይናገራሉ
2. በአከባቢያቸው ያሉ ነጋዴዎች የሚነግዱትን ይናገራሉ
3. የሚጠበቀው መልስ አዎ፤ ምክንያቱም ግብር የዜግነት ግዴታ ነው፤ ግብር ሲከፈል የተለያየ ስራ ይሰራበታል (መንገድ፣ ውሃ፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና ተቋም…)
4. አዳዲስ ቃላትና ዋና ዋና ሀሳቦች የሚሏቸውን ይመዘግሉ፤

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. በንግድ 2. ግብር በወቅቱ
3. ገቢዎች ጽህፈት ቤት 4. መሠረተ ልማቶች

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**መልመጃ አንድ**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሀሰት 5. ሀሰት 6. እውነት

**ክፍለ ጊዜ፡ ሶስት**

ለ· 1. ንግድ /ጠቅላላ ንግድ/ 2. አራት 3. መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት፤ ለዕድገት
4. ህጋዊ ፈቃድ ሲኖረውና ግብር አሳውቆ በጊዜ ሲከፍል

**ክፍለ ጊዜ፡ አራት**

ሐ· 1. ግብር - ገቢ በመገኘቱ የሚከፈል ገንዘብ 2. ፈቃድ - ይሁንታ/ማረጋገጫ ወረቀት
1. ገቢዎች - ግብር ሰብሳቢ መስሪያቤት 5. ተሸላሚ - እውቅና የተሰጠው
2. ሸቀጣሸቀጥ - የተለያዩ ምርቶች 6. ሱቅ - መሸጫ ቦታ
3. ማደስ - እንደገና መውሰድ 7. ምርት - የተረተ ነገር
4. ውዴታ - በፈቃድ/በፍላጎት 8. ግዴታ - ያለፈቃድ/በህግ የተወሰነ

**ክፍለ ጊዜ፡ አምስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

**ሀ.** ሲያዳምጡ በመዘገቧቸው አዳዲስና ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ ይወያያሉ

**ለ.** በአካባቢያቸው ስላሉ የንግድ ክንውኖች መረጃ በንግግር ያቀርባሉ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ**

**የቅድመማንበብ ጥያቄዎች**

1. ከምስሉ የተረዱትን ለጓደኞቻቸው ይገልፃሉ
2. ከአካባቢያቸው ካለ ሱቅ ገዝተው የሚያውቁትን ነገር ይዘረዝራሉ
3. ግምታቸውን ይናገራሉ

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

ህጋዊ ነጋዴ የሚበላው እንዴት ያለ ነው? ፈቃድ ያለው፤ ግብር አሳውቆ በጊዜ የሚከፍል ግብር መክፈል ለምን ይጠቅማል?መሰረተ ልማት ለማሟላት፤ ለማህበራዊ አገልግሎት

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ.** 1. ሀሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

**ለ.** 1. ለ 2. ሀ 3. ለ 4. ሐ 5. መ

**ክፍለ ጊዜ፡ ስምንት**

**ሐ.**1. በህግ ተጠያቂ ይሆናል 2. መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት
3. በየወቅቱ ህጋዊነትን ለመላበስ 4. ፈቃድ ሳይኖረው የሚነግድ/ግብር የሚሰውር
5. ግብር መክፈል

**ክፍለ ጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

**መልመጃ ሶስት**

**መ.** 1. ንግድ ማለት ሕጋዊ የምርት ውጤቶች በመግዛት እና...

2. … ልውውጥ ማድረግና **አገልግሎት** መስጠት ነው።
3. … መንግስት አገሪቱን **ላቅ** ያለ ደረጃ ለማድረስ ይጥራል።
4. በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት የጤና ወዘተ **ተቋማትን** ለማስፋፋ…
5. … በመሸጥ **ልውውጥ** ማድረግና አገልግሎት መስጠት ነው።
6. የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው ሰው ሕጋዊ በመሆኑ **የህግ** ከለላ ይሰጠዋል።
7. …የንግድ ፈቃድ ይዞ የሚሰራ አካል ለሕግ **ተገዥ** በመሆኑ ነው።
8. እንዲሁም ከዚህ የሚገኝ **ትርፍ** ሀብት ማግኛ ዘዴ ነው።
9. እንዲሁም ከዚህ የሚገኝ ትርፍ **ሀብት** ማግኛ ዘዴ ነው።

**ክፍለ ጊዜ፡ አስር**

**ተግባር ሁለት**

**ሀ.** ትክክለኛው ቅደም ተከተል፡ 2፣ 5፣ 1፣ 6፣ 7፣ 4፣ 3

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ አራት**

**ሀ. ተኩላ-** ቀበሮ የሚመስል፣ አደገኛ/መጥፎ፤

**ጠራ -** ንጹህ ሆነ፣ ና አለ **ቆላ -** አበሰለ (ቆሎ)፣ በረሃማ አከባቢ

**አጠረ -** ቁመት ቀነሰ፣ አጥር ሰራ **ሰፈረ -** ለካ/ **ሰፈረ -** ስፍራ ያዘ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ.** ሁለቱን ፍቺዎች በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ይፃፉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ሐ.** 1. ጠመደ 2. ጠመደ 3. ቀጨች 4. ቀጨ 5. ቋጨች 6. ቋጩ

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ አራት**

**መ.** ምክንያት አቅርበው የመረጧቸው ማናቸውም ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ሠ.** በመረጧቸው ቃላት በምሳሌው መሰረት ተገቢ አረፍተነገሮች ይመስርቱ

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ.**

| ተ.ቁ | ቃል | መነሻ ቅጥያ | ነጻ ቃል | መድረሻ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሬውን | በ | በሬ | ውን |
| 2. | ሀቀኛ | - | ሐቅ | እኛ |
| 3. | ታዳሚዎች | - | ታዳሚ | ዎች |
| 4. | አስፈጠረ | አስ | ፈጠረ | - |
| 5. | ቤተሰባዊ | - | ቤተሰብ | አዊ |
| 6. | እንደራስህ | እንደ | ራስ | ሠ |
| 7. | አልመታም | አል | መታ | ም |
| 8. | በፍጥነት | በ | ፍጥነት | - |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ለ.** ሰካራም ፣ ሰማያዊ፣ በሬው፣ ሠራተኛ፣ አይናማ፣ ሀገራዊ፣ መምህራን

**ክፍለ ጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ሐ.** ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች

# አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ 4ኛ ክፍልመርሀትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው፡፡ይኸውም ለ21ኛው ክፍለዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደፊት የሚያራምድ ነው፡፡ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓተትምህርት ንቀርጿል፡፡ በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘትፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርአተትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስርዓተትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው፡፡

መርሃትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል፡፡

ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው፡፡ የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ፣ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው

መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል፡፡

### የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ግቦችና አላማዎች

#### የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች፡-

- ከቅድመአንደኛ ደረጃ እስከሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍመፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል፡፡

#### ግቦች

- የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፣

- ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል፡፡

<u>አላማዎች</u>

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-**

- መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤
- የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡

**ራዕይና እሴቶች**

**ራዕይ**

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ፡፡ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል፡፡ይህን እሳቤ ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትየጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

**እሴቶች**

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው፡፡እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት የተዘጋጀው መርሀትምህርት ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስበእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

## አንደኛው ወሰነትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡ የአካባቢ ጥበቃ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የተሰጠውን ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፤
- የክፍሉን ደረጃ የጠበቀ ምንባብ አንብበው ዝርዝር ጉዳዮችን ይለያሉ፤
- የቃላትን በአገባብና ከአገባብ ውጪ ትርጉም/ፍች ይሰጣሉ፤
- ጥገኛ መስተጻምርን በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡<br>• አዳምጠው መልዕክቱን መናገር<br>• ምንባብን አንብበው ዝርዝር ጉዳዮችን መለየት፤<br>• የቃላትን ፍቺ መስጠት፤<br>• ድርብ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፤<br>• አያያዥ መስተጻምሮችን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን መመስረት | **ማዳመጥና መናገር**<br>አዳምጦ በምንባቡ መሰረት መመለስ<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>የተሰጠውን ምንባብ በማንበብ አናጻራዊ ዝርዝር መረጃዎችን መስጠት<br>**ቃላት**<br>የቃላት ፍቺ<br>**መጻፍና ሰዋሰው**<br>አያያዥ መስተጻምሮች | ምንባብን አዘጋጅቶ ለተማሪዎች ማንበብ ፤ ከዚያ ዋናውን መልዕክት እንዲገልጹ መጠየቅ፡፡ (ምሳሌ ያዳመጣችሁትን ንገሩኝ፤ ከአዳመጣችሁት ምንባብ ምንድን ነው የተማራችሁት)<br>ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ዋና ሀሳቡን እንዲያወጡ ማድረግ ፤(ምሳሌ አንቀጹ ስለምን ያወራል? ያካባቢያችንን ንጽህና እንዴት እንጠብቃለን?)<br>ለተወሰኑ ቃለት ፍቺ መስጠትና በዚያው መንገድ እንዲሰሩ ማድረግ፤<br>ተማሪዎቹ በራሳቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ አያያዥ መስተጻምር እንዲጠቀሙ ማድረግ፤ (ምሳሌ እና፣ ግን፣ ስለዚህ፤ አንተና ጓደኛህ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናችሁ፡፡ | የማዳመጥ ችሎታቸውን ለመገምገም ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ ምሳሌ፡<br>ሀ. (ያዳመጣችሁት ምንባብ መልዕክት ምንድን ነው?<br>ለ. ከምንባቡ ያገኛችሁት ትምህርት ምንድን ነው?)<br>ደረጃቸውን የጠበቀ ምንባብ በመስጠት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አንብበው ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ፤ ምሳሌ አካባቢያችሁን እንዴት ትንከባከባላችሁ?<br>አካባቢን የመጠበቅ ሃላፊነት የማን ነው?<br>ከተሰጠው ምንባብ የወጡትን ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ፤ አያያዥ መስተጻምሮችን እንዲጠቀሙ ተማሪዎችን በጠየቅ፣ (ግን፣ እና፣ስለዚህ፣ እንዲሁም…) |

**ምዕራፍ ሁለት፡ የመንገድ ላይ ጥንቃቄ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ስለ መንገድ ላይ ጥንቃቄ የተዘጋጅን መዝሙር አዳምጠው ይዘምራሉ፤
- በሚጠበቀው ደረጃ የቀረበውን አንቀጽ ድምጻችወን ከፍ አድርገው ያነባሉ፤
- የቃላትን ከነባሪ ሁኔታዎች ጋር ያዛምዳሉ፤
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ድርብ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• ምንባቡን አዳምጠው በትክክል ደግሞ መናገር<br>• ምንባብን ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ<br>• ቃላትን ከናበራዊ ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ<br>• ድርብ አረፍተነገሮችን መመስረት | **ማዳመጥና መናገር**<br>ተራ በተራ እያዳመጡ መናገር<br>**ማንበብ**<br>አስተካክሎ ማንበብ<br>**ቃላት**<br>ቃላትን ከትራፊክ መብራት ጋር ማዛመድ<br>**መጻፍና ስዋሰው**<br>ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ስለመንገድ ጥንቃቄ መዝሙር ማዘጋጀት (መቅረጽ፡- ከሬድዮ ወይም በወረቀት ላይ የተጻፈ መዝሙር፡፡)<br>ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ማድረግ ፤ ከዚያም እንዲዘምሩ ማድረግ፡፡<br>የትራፍክ ህግጋትን በቅድሚያ ነግሮ ተማሪዎቹ ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ቃላቱን እንዲዛምዱ ማድረግ፡፡<br>ምሳሌ ሀ. አረንጓዴ መብራት ሂድ ለማለት ነው፡፡<br>ለ. ቢጫ መብራት ለመሄድ ተዘጋጅ ለማለት<br>ሐ. ቀይ መብራት ማቋረጥ ክልክል ነው ለማለት፡፡<br>ተማሪዎች ምንባቡን ድምጽ አሰምተው እንዲያነቡ ማስቻል፡፡<br>ተማሪዎች በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት የራሳቸውን ድርብ አረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ ጊዜ መስጠት፡፡<br>ምሳሌ፡ ጫላ ትምህርት ቤት ሂዶ ተመልሶ መጣ ፡፡ | ተማሪዎቹ በሙሉ እንዲሳተፉ ( ሁሉም መዝሙሩን እንዲዘምሩ ) ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ በትክክል ማንበባቸውን መከታተል፡<br>ተማሪዎቹ ቃላትን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያዛምዱ መጠየቅ፡፡ (ቀለሞችን በመለየታቸው ግብረ መልስ መስጠት)<br>ተማሪዎቹ ድርብ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ መጠየቅ |

**ምዕራፍ ሶስት ፡ መረዳዳት (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህንን የምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች

- የቀረበውን ምንባብ በማዳመጥ ስሜታቸውን ይገልጻሉ፤
- በሚጠበቀው የፍጥንት ደረጃ የቀረበውን ምንባብ ያነባሉ፤
- ቅጥያ ባላቸው ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፤
- ድርብና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ<br>ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ<br>• ምንባብን በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ አንብበው ዋና ሀሳብ መለየት<br>• በአረፍተ ነገር ምስረታ ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያዎች መጻፍ | **ማዳመጥና መናገር**<br>ምንባቡን አድምጠ ማስታወሻ መፃፍ<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br>በመካከለኛ ፍጥነት ማንበብ<br><br>**ስዋሰው**<br>ቅጥያ ባላቸው ቃላት መጠቀም | አጭር ገለጻ በመስጠት ወይም ስለመረዳዳት የተጻፈውን ምንባብ በማንበብ አካል ጉዳተኞችን በተግባር እንዴት መርዳት እንደሚቻል እንዲጽፉ ማድረግ (ይህ የማዳመጥን ክህሎት ለማዳበር ይረዳል፡፡)<br><br>የንባብ ክህሎትን ለማዳበር ተማሪዎችን ማደራጀት በንባብ ጊዜ ያሉትን/<br><br>የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች መስጠት፤<br><br>በተሰጠው ሰዓት ውስጥ አንብበው እንዲያበቁ ማድረግ)<br><br>የተወሰኑ ቅጥያዎችን በምሳሌነት በመስጠት የቀሩትን ተማሪዎቹ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ | በማዳመጥ ጊዜ የያዟቸውን ማስታወሻዎች ማየት፤<br><br>በተወሰነ ጊዜ የተሰጣቸውን ምንባብ አንብበው መጨረሳቸውን ማረጋገጥ፤<br><br>በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት የጻፏቸውን ቅጥያዎች መጠየቅ |

**ምዕራፍ አራት፡ ስርዓተ ጾታ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በተሰጠው ርዕስ ላይ የቀረበውን አዳምጠው ስሜታቸውን ይገልጻሉ፤
- ከቀረበው ምባብ የተወሰኑትን መረጃዎች አንብበው ይጽፋሉ፤
- የአንቀጹን ጽንሰ ሀሳብ ይገልጻሉ፤
- የተውሶ ቃላትን ይለያሉ፡፡
- ግሶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ<br>ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• አዳምጠው የራሳቸውን ስሜት መግለጽ<br>• ምንባብን አንብበው የተወሰኑ መረጃዎችን መጻፍ<br>• አንቀጽን መግለጽ<br>• የተውሶ ቃላትን መለየትና መጠቀም፡፡<br>• ግሶችን ለይቶ አረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም | **ማዳመጥ**<br>አዳምጠው ሀሳብን መግለጽ<br>**መናገር**<br>ክርክር<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>ለውስን መረጃ ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>አንቀጽን በጽሁፍ መግለጽ<br>**ቃላት**<br>የተውሶ ቃላት<br>**ሰዋሰው**<br>በአረፍተ ነገሮች ውስት ግሶችን መጠቀም | ስለ ስርዓተ ጾታ ለተማሪዎች መንገር ልምዳቸውንና ስሜታቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ<br><br>ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በወንዶችና በሴቶች የስራ ድርሻ (ሚና) ላይ ባለው ጽንሰ ሀሳብ እንዲከራከሩ ማድረግ (ዋና አላማው የመናገር ክህሎትን ለማዳበር ነው፡፡)<br><br>ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ እንዲመልሱ የሚፈለጉትን ጥያቄዎች ማዘጋጀት፡፡<br><br>ስለ አንቀጽ ለተማሪዎች መግለጽ፡፡ እንደ ምሳሌ የሚያገለግል አጭር አንቀጽ ጽፎ በሱ ላይ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡<br><br>በቴክኖሎጂ ምክንያት የገቡትን የተውሶ ቃላት (ስሞች) መዘርዘር፡፡ ምሳሌ ኮምፒተር፣ ዋይ ፋይ፣ ፌስ ቡክ፣ ቴሌግራም…)<br><br>ስሞችን ሊተኩ የሚችሉ ግሶችን እንዲለዩ የሚያስችል መልመጃ ለተማሪዎች መስጠት | የመረዳት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የማዳመጥ ክሂላቸውን መመዘን<br><br>ክርክራቸውን እየመሩ ወዲያውም ተሳትፏቸውን መመዘን<br><br>ለተሰጡት ጥያቄዎች ባነበቡት ምንባብ መሰረት የሰጧቸውን መልሶች መመዘን<br><br>ለተማሪዎቹ የተውሶ ስሞችን በመንገር የሚያውቋቸውን እንዲዘረዝሩ መንገር<br><br>ግሶችን በትክክል መለየታቸውን ወይም አለመለየታቸውን መገምገም፤ አብዛኛዎቹ መለየት ካልቻሉ ተጨማሪ ምሳሌዎችን መስጠትና ማበረታታት |

**ምዕራፍ አምስት፡ ጉብኝት (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ስለ ቱሪዝም መስህቦች አድምጠው በቃላቸው ይዘግባሉ፤
- ምንባቦችን አንብበው ይረዳሉ፤
- የአንቀጽን ባህሪያት ይለያሉ፤
- ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡
- በአረፍተ ነገር ምስረታ ጊዜ ቅጽሎችን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• አዳምጦ መዘገብ<br>• አንብቦ ዋናውን ጉዳይ መለየት<br>• ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃለት ማዛመድ<br>• ቅጽሎችን ለይቶ መጠቀም | **መናገርና ማዳመጥ**<br>ልምድ መለዋወጥ<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>ምንባብን አንብቦ ዋና ዋና ነጥቦችን በጽሁፍ መግለጽ<br>**ቃላት**<br>የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ መስጠት<br>**ሰዋሰው**<br>ቅጽሎችን መጠቀም | ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ መምራት በቅድሚያ የራስን ልምድ ማካፈል፡፡ ምሳሌ የጎበኟቸውን ቦታዎች እና የተደሰቱባቸውን (በምክንያት) መንገር በመቀጠል የራሳቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ፡፡<br>በንባብ ጊዜ የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች መስጠት (እነዚያ ጥያቄዎች በሚያነቡበት ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲያገኙ ይረዷቸዋል፡፡)<br>ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት እንዲያዛምዱ ማድረግ | የንግግራቸውን አደረጃጀት መገምገም<br>መልሳችወን አይቶ ግብረ መልስ መስጠት<br>መልሳቸውን አይቶ (ቃላትን ማዛመድ) እርማት መስጠት<br>ቅጽሎች ያሉባቸውን አረፍተ ነገሮች ሰጥቶ ቅጽሎችን ለይተው እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ ምሳሌ ቀጥሎ ያሉትን ከስር የተሰመረባቸውን<br>ሀ. ልጅቷ <u>ትልቅ</u> ጃኬት ለብሳለች፡፡<br>ለ. ልጁ <u>ጎበዝ</u> ተማሪ ነው፡፡<br>ሐ. እኔ <u>ጥቁር</u> ብዕር አለኝ፡፡ |

## ሁለተኛ ወሰነትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፡ ስፖርት (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- አድምጠው ተመሳሳይ መረጃዎችን በቃላቸው ያካፍላሉ፤
- እያንዳንዱን አንቀጽ አንብበው የምንባቡን ሀሳብ ይገልጻሉ፤
- በልምምድ የቃላት እውቀታቸውን ያዳብራሉ፤
- ባለቤትንና ግስን በማስማማት አረፍተ ነገር ይገነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• አዳምጠ ልምድን ማካፈል<br>• ምንባብን አንብበው የምንባቡን ሀሳብ መግለጽ<br>• ሙሉ ሀሳብ የሚያስተላልፍ አረፍተ ነገር መገንባት<br>• የቃላት እውቀትን ማሳደግ | **ማዳመጥና መናገር**<br>መረጃን ማካፈል<br>**ማንበብ**<br>አንብቦ ሀሳብን መግለጽ<br>**መጻፍ**<br>ባለቤትና ግስ አስማምቶ አረፍተ ነገር መገንባት<br>**ቃላት**<br>የቃላት እውቀትን ማሳደግ | ስለ ታዋቂ አትሌት ለተማሪዎቹ መንገር፤ ከዚያ ከ3 እስከ 4 ቡድኖችን በማደራጀት ስለሚያውቋቸው ታዋቂ አትሌቶችና ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ልምዳቸውን እንዲጋሩ ማድረግ፡፡ (ይሄን ማድረግ የንግግርና የማዳመጥ ልምዳቸውን ያዳብራል)<br>የተሰጧቸውን ቃላት ተጠቅመው የራሳቸውን አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ተማሪዎቹን ማበረታታት፡፡ ምሳሌ<br>ሀ. ስፖርት እወዳለሁ፡፤<br>ለ. የስፖርት ዜናን ተመለከትን፡፡<br>ተማሪዎች ባለቤትና ግስን አስማምተው አረፍተነገሮችን እንዲጽፉ ማድርግ፡፡ | በውይይቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት።የጻፏቸውን አረፍተ ነገሮች አይቶ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን መስጠትና የአረፍተ ነገሮቹ ስህተቶችን ለይተው ማረም፡፡ ምሳሌ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ባለቤትና ግስ በማስማማት ደግመው እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ሀ. እነሱ ተማሪ ነው፡፡<br>ለ. እሱ ተማሪ ናቸው፡፡<br>ሐ. እሷ አስተማሪ ነው፡፡ |

**ምዕራፍ ሰባት፡ ውሃ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በኢመደበኛ ሁኔታ ውስጥ በሚደረገው የሚና ጨዋታ አዳምጠው ይሳተፋሉ፤
- ምንባቡን አንብበው በዝርዝር ይገልጻሉ፤
- የየራሳቸውን የተሟሉ አረፍተ ነገሮች ይጽፋሉ፤
- ተውሳከ ግስን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ስለ ውሃ ጥቅም የቀረበውን መዝሙር አዳምጠው ስለ ውሃ ጥቅም ይጽፋሉ፡፡
- በተሰጠው ርዕስ ላይ ክርክር ያደርጋሉ፤
- የተሰጧቸውን ግሶች ተጠቅመው የተሟሉ አረፍተ ነገሮች ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• ምንባቡን አዳምጠው በሚና ጨዋታ መሳተፍ<br>• ክርክር ማድረግ<br>• የተሟሉ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ<br>• ቃላትን በተገቢው መንገድ መጠቀም<br>• በአረፍተ ነገር አመሰራረት ውስጥ ግስን መጠቀም | **ማዳመጥ**<br><br>የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥና በሚና ጨዋታ መሳተፍ<br><br>**መናገር**<br><br>ክርክር ማድረግ<br><br>**ማንበብ**<br><br>ዝረዝር ጉዳዮችን ለማወቅ ማንበብ<br><br>**መጻፍ**<br><br>የተሟሉ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ<br><br>**ቃላት**<br><br>ቃላትን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም<br><br>**ስዋሰው**<br><br>ግሶችን በአረፍተ ነገሮች ውስጥ መጠቀም | የሚነበብላቸውን ምንባብ እንዲያዳምጡ መንገር፤ ከዚም በኢመደበኛ ሁኔታ ውስጥ በሚደረግ የሚና ጨዋታ ማሳተፍ፡፡<br><br>ተማሪዎችን በተለያዩ ቡድኖች መከፋፈል፤ እያንዳንዱ ቡድን የየራሱ ሚና እንዲኖረው (በክርክሩ እንዲሳተፉ፣ የኮሚቴ አባል/ሊቀመንበር እና ጸሀፊ እንዲኖራቸው) ማድረግ፤ ከዚያ በተሰጣቸው ርዕስ ክርክር እንዲያረጉ ማዘዝ፡፡<br><br>ተማሪዎች እንዲያነቡ የሚያደርጓቸው ተግባራትን መስጠት( ምሳሌ፤በንባብ ጊዜ የሚደረጉ ተግባራት)<br><br>ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን መስጠትና ተገቢ ቃላትን ተጠቅመው እንዲያሟሉ ማድረግ። ቀጥሎም የራሳቸውን የተሟሉ አረፍተ ነገሮች ማሰራት፡፡<br><br>የግሶችን የያዙ ምሳሌዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ በመስጠት ለይተው እንዲጠቀሙባቸው ለማስቻል የቤት ስራ መስጠት፡፡ | በሚና ጨዋታ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ፤ ምሳሌ የውሃ ችግር ቢያጋጥም በእንሰሳት ላይ፣ በእጽዋት ላይ በራሳችሁ ላይ ምን ችግር ይደርሳል በማለት መጠየቅ፡፡<br><br>ክርክራቸውን በትኩረት በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት፤ ጥሩ ተሳትፎ ያላቸውን ማበረታታት፡፡ እያንዳንዱን አባላት በተጫወቱት ሚና መገምገም፡፡<br><br>በምንባቡ ላይ ተመስረተው የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ መጠየቅ፤<br><br>ቀጥለው ያሉትን ጅምር አረፍተ ነገሮችን እንዲያሟሉ ማድረግ፣<br><br>ምሳሌ:-<br><br>ሀ. እኛ------እንጠጣለን፡፡<br>(ውሃ/ሻይ/ወተት/ዳቦ…)<br><br>ለ. እኛ ----- እንበላለን፡፡<br>(ዳቦ/ኬክ/እንጀራ/ቡና…)<br><br>ሐ. እኛ ---- እንለብሳለን፡፡<br>(ልብስ/ጫማ/ኮት/አልጋ…)<br><br>ግሶችን ለይተው እንዲጠቀሙ ማዘዝ፡፡ |

**ምዕራፍ ስምንት፡ ድርድር (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ተራቸውን በመጠበቅ፣ ያዳምጣሉ፤ይናገራሉ
- ራሳቸውን ችለው የምንባቡን ይዘት በዝርዝር ያነባሉ፤
- ስለትምህርት ቤታቸው ደንብና መመሪያ ይጽፋሉ
- ቅጥያዎችን ከግስ ይነጥላሉ፡፡
- ቃላትን በምህፃረ ቃል ይፅፋሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ<br>ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• በሚና ጨዋታ መሳተፍ<br>• በምንባቡ ላይ ተመስርተው የሚመጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቡን<br>• ማንበብ<br>• የትምህርት ቤታቸውን ደንብና መመሪያ መጻፍ<br>• ቃላትን አሳጥሮ መፃፍ<br>• ከቃላት ቅጥያዎችን መነጠል | **መናገርና ማዳመጥ**<br>በየተራ መናገርና ማዳመጥ<br>**ማንበብ**<br>ለመረዳት ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>ስለትምህርት ቤታቸው መመሪያና ደንብ መጻፍ<br>ቃላት<br>• ምህፃረ ቃላት<br>**ስዋሰው**<br>ከቃላት ቅጥያዎችን መነጠል | እንዴት በየቦታው መግባባት እንደሚፈጠር ለተማሪዎች መንገር (በትምህርት ቤት፣ በቤት፣ በገበያ...) አዳምጠው እንደአባትና ልጅ ሆነው በሚና ጨዋታ እንዲሳተፉ እንደ መምህርና ተማሪ ወዘተ.) ቅራኔዎችን እንደሚፈቱ ማድረግ<br>የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በመስጠት የተሰጠውን ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ መልስ እንዲሰጡ ማስቻል፡፡<br>መምህር በሚሰጧቸው ምሳሌ መሰረት የትምህርት ቤታቸውን መመሪያና ደንብ እንዲጽፉ ማድረግ፤ ከዚያ በጥንድ በጥንድ ሆነው እንዲያርሙ<br>ቃላትን በምእጻር መፃፍን እና በምህፃር የተፃፍጽን ሙሉ ቃላቸውን እንዲፅፍ ምሰሌዎችን በመስጠት ማለማመድ ማድረግ፡፡**ምሳሌ** ሀ. ሁሉም ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ የደንብ ልብሱን መልበስ አለበት።<br>ለ. ሁሉም ተማሪ የቤት ስራውን በጊዜ መስራት አለበት።<br>ሐ. ሁሉም ተማሪዎች ደብተሮቻቸውንና ብዕሮቻቸውን ይዘው መገኘት አለባቸው፡፡ | የሚና ጨዋታዎችን በመምራት ወዲያውኑ ግብረ መልስ መስጠት ሲያነቡ ተከታትሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መስጠታቸውን መለየት፡፡<br>በሚጽፉበት ጊዜና እርማት በሚሰጣጡበት ጊዜ ክትትል ማድረግ፤<br>ደብተሮቻቸውን በማረም አጠቃላይ የሆነ ግብረ መልስ ለሁሉም ሰሌዳ ላይ መጻፍ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡ መገናኛ ብዙሃን (18 ክፍለ ጊዜያት)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የተቀረጹ ድምጾችን በማዳመጥ የንግግርን ፍሬ ሀሳብ ይናገራሉ፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤
- ተራ አረፍተ ነገሮችን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- መስተዋድዶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ<br>ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• የተቀረጹ ድምጾችን አዳምጠው ሀሳቡን ይናራሉ<br>• ዝርዝር ጉዳዮችን ለማወቅ ምንባቡን በግል ያነባሉ<br>• የቃላትን ፍቺ በምንባቡ ውስጥ በሚሰጡት አገልግሎት መሰረት ይሰጣሉ<br>• መስተዋድዶችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ | **ማዳመጥና መናገር**<br>የተቀረጹ ድምችን ማዳመጥና መናገር<br><br>**መጻፍና መናገር**<br>ምንባቡን በየግል በማንበብ ዝርዝር ጉዳዮችን መግለጽ፤ (በጽሁፍ)<br><br>የራሳቸውን ሀሳብ ጽፈው እንደጋዜጠኛ ማንበብ፤<br><br>**ቃላት**<br>ከምንባብ የወጡትን ቃላት ፍቺ መስጠት<br><br>**ስዋሰው**<br>መስተዋድዶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን መመስረት | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን በማዘጋጀት ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም እንዲወያዩ ማድረግ፤ ከዚያ በሚያዳምጡበት ጊዜ የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች መስጠት፡፡<br><br>የራሳቸውን ፈጠራ እንዲጠቀሙ ተማሪዎችን ማበረታታት፤ በሚወዱት ርዕስ ላይ ዜና ጽፈው በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ማበረታታት፡፡<br><br>የቅድመ ንባባብ ጥያቄዎችን መስጠትና እንዲወያዩበት ማድረግ፤ ከዚያም የንባብ ጊዜ ተጋባራትን መስጠት፤ ከዚያም ምንባቡን አንብበው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br><br>የቃላትን ፍቺ እንደአገልግሎታቸው ፈልገው እንዲያወጡ ማድረግ፡፡<br><br>ተማሪዎቹ መስተዋድዶችን በአረፍተ ነገር ምስረታ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ፤ ምሳሌ<br>ሀ.ቃላትን በደብተርህ ላይ ጻፍ፡፡<br>ለ. ያንን ብዕር ለጫልቱ ስጥ፡፡ | ተማሪዎቹ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መጠየቅ፤<br><br>የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችንም እንዲመልሱ ማድረግ፤ በስራቸው ላይ ግብረ መልስ በመስጠት ማበረታታት፡፡<br><br>ተማሪዎቹ የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መጠየቅ፤ መልሶቻቸውን በማረም ግብረ መልስ መስጠት፤<br><br>ቃላትን ከምንባብ ውስጥ በማውጣት<br><br>በአገባባቸው መሰረት ፍችን መጠየቅ፤<br><br>በአረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዶችን እንዲለዩ መጠየቅ፡፡ |

**ምዕራፍ አስር፡ ንግድ (18 ክፍለ ጊዜያት)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ምንባቡን እድምጠው በቡድን ይወያያሉ፤
- የተሰጠውን ምንባብ አንብበው የእያንዳንዱን አንቀጽ ዋና ዋና ሀሳብ ይለያሉ፤
- በተሰጠው ርዕስ ላይ ተመስርተው አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ከአንድ ፍቺ በላይ ያሏቸውን ቃላት ይለያሉ፤
- ቅጥያ ባላቸው ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡<br>• መምህራቸው የሚያነቡላቸውን አድምጠው ወይም የተተረከላቸውን አዳምጠው ዋናውን ሀሳብ ካዳመጡት ለይተው መናገር<br>• እያንዳንዱን አረፍተ ነገር አንብበው መግለጽ<br>• አጭር አንቀጽ መጻፍ<br>• በመግዛትና በመሸጥ ላይ አንቀጾችን መጻፍ<br>• ለቃላት ከአንድ በላይ ፍቺ መስጠት<br>• የተለያዩ ቅጥያ ባላቸው ቃላት በመጠቅም አረፍተ ነገሮችን መመስረት | **ማዳመጥና መናገር**<br>መረጃ መስጠት<br>**ማንበብ**<br>ምንባብን አንቀጽ በአንቀጽ ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>አጭር አንቀጽ መጻፍ<br>**ቃላት**<br>ከአንድ በላይ ፍቺ ላላቸው ቃላት<br>**ስዋሰው**<br>የተለያዩ ቅጥያዎች ያሏቸው ቃላት | ስለ ቁሳቁሶች ግዢና ሽያጭ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ለተማሪዎች ማንበብ፤ ተማሪዎቹ አዳምጠው ዋናውን ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ እንዲወያዩበት ማድረግ፤<br>ከዚያም የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ለመመለስ እያንዳንዱን አንቀጽ ማስነበብ፡፡<br>ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ቁልፍ ቃላትን ከአገባቡ እንዲያወጡ ማድረግ፡፡<br>ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በመምረጥ ተማሪዎቹ ፍቺዎችን እንዲሰጡ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎቹ የተቀናጀ አንቀጽ በመጠቀም በግዢና ሽያጭ ላይ እንዲጽፉ ማበረታታት | ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጥያቄዎችን መጠይቅ፡፡ ትረካውን እንዲያዳምጡ ማድረግና ዋናውን ሀሳብ እንዲያወጡ ማበረታታት፤ ከዚያም የማዳመጥንና የመናገርን ኪሂሎች እንዲያዳብሩ መንገር፡፡<br>በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎቹ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>ምንባቡን በየግል አንብበው የተሰጡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ መጠየቅ፤<br>የጻፉትን አንቀጽ መገምገም<br>የተለያዩ ቅጥያዎች ያሏቸውን ቃላት በመስጠት የየራሳቸውን አረፍተ ነገር መጻፋቸውን ማየት |